## ከቀውስ የሚያተርፍ ሥርአት?

ያሬድ ጥበቡ

## ንስሃ የራቀው የህወሓት መጨረሻ

## የህሊና እስረኛ



ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማህተመወርቅ


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን


በየሳምንቱ ቅዳሜ

ቅጽ 2 ቁጥር 78 ጥር 2012 ዓ.ም

ዋጋ 20.00




# ከበደኖ እስከ ደምቢዶሎ - የዘር ጥቃት ሰቆቃ!



“ደሕንነቱና ህግ አስፈጻሚው አካል ኢትዮጵያዊ እውነታችንን ነጥቆናል”

ዶ/ር አለማየሁ አረዳ



“ፊንፊኔ የእኔ ናት፣ ስትል ‘እንተላለቃለን’ የሚል ለሞቱ የቆረጠ ሰው ያስፈልጋል”

አቶ ኤፍሬም ማዴቦ

“ሀብታም ሀገር ይዘን መጠቀም እየቻልን እርስበርስ መፋጀታችን ያሳዝናል!”

ዘላለም መርዓዊ



ዜና

# አርቲስት ዓለምፀሐይ ወዳጆ የ10 ሚሊዮን ብር ቤት ተሸለመች



በሁለገብ የኪነ ጥበብ ባለሙያነቷ የምትታወቀው አገር ወዳዷ አርቲስት ዓለምፀሐይ ወዳጆ 10 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የመኖሪያ ቤት ሽልማት በያዝነው ሣምንት መጀመሪያ ተበርክቶላታል፡፡

በተለይም በምትጽፋቸው በሳል የዘፈን ግጥሞች ከፍተኛ አድናቆት ያገኘችው ዓለምፀሐይ ወዳጆ ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ለመግባት የቀናት ዕድሜ በቀሩበት በ1983 ወርሃ ግንቦት ከኢትዮጵያ ከወጣች በኋላ፣ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ አራማጁ የህወሓት መንግሥትን በፅኑ ስታቃወም በመቆየቷ፣ አገር ቤት ለመመለስ የቻለችው ከ27 ዓመት በኋላ ነበር፡፡

ረዥሮም ዕድሜዋን በስደት ህይወት ጥበብንና የአገርን ፍቅርን ስሜት አቆራኝታ በማራመድ፣ ለራሷ የሚሆን ነገር ብዙም ሳትይዝ የሰነበተችው ተወዳጇ አርቲስት አለምፀሐይ ወዳጆ ይህንን ድካምና የአገር ፍቅር ፅናቷን በተመለከቱት በናሁ ቲቪ ባለቤት አቶ ቴዎድሮስ አማካይነት ዋጋው 10 ሚሊዮን ብር የሚገመት የመኖሪያ ቤት ተሸልማለች፡፡

ይህ የዓለም ፀሐይ ወዳጆ ሽልማት በርካታ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን እና ኢትዮጵያውያንን በእጅጉ ያስደሰተ ሆኗል፡፡ ዓለም ፀሐይ ወዳጆ በአሜሪካ የሚገኘው፤ በኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራው የጣይቱ ባህል ማዕከል መሥራች መሆኗ ይታወቃል፡፡



## የመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ እርምጃ ሊወስዱ ነበር የተባሉ የሸኔ አባላት ክስ ተመሰረተባቸው

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጥር 15 ቀን ተፈሪ ባረቦሼ፣ ያደሳ ዮሴፍ፣ ቡርቃ ኩመራ፣ መሀመድ ኢሳ፣ ኤፍሬም ኢያሱ፣ አብዲ ድሪባ እና መርጋ ጉታ በተባሉ ሰባት ግለሰቦች ላይ በመሠረተው የሽብር ወንጀል ክስ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የጸረ ሽብር ችሎት ክሱን አስነብቧል፡፡

ተጠርጣሪዎች በምስራቅ ወለጋ ከሚንቀሳቀሰው ኩምሳ ድሪባ ወይም ጃል መሮ ፣ በአገር ውስጥ የሸኔ ታጣቂ እና አመራር ጋር ግንኙነት ይፈጥሩ እንደነበር የቀረበው ክስ ያስረዳል፡፡

ግለሰቦች የጦር መሳሪያ እና የገንዘብ ድጋፍ እየተደረገላቸው በአዲስ አበባ እና ቡራዩ በመንቀሳቀስ "አባ ቶርቤ" የተባለ እርምጃ ወሳጅ ቡድን ስለማቋቋማቸውም ተገልጿል፡፡ ይህ ቡድን በመንግስት የሥራ ሓላፊዎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ በያዝነው ዓመት መስከረም 1 ላይ ከምሽቱ 1 ሰዓት ተኩል ገደማ በኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ከተማ በፖሊስ  አባላት ላይ ቦምብ በመወርወር በ9 አባላት ላይ ጉዳት ስለማድረሳቸውም ተነግሯል፡፡

ዐቃቤ ህግ የእያንዳንዱን ተከሳሾች የወንጀል ድርጊት በተናጠል ያስቀመጠ ሲሆን፤ ሁሉም ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት የሽብር ድርጊት ዝግጅት በመከወን ወንጀል ፈፅመዋል ሲል ከሷል፡፡

## ጫልቱ ታከለ በድጋሚ ለእስር ተዳረገች

በምስራቅ ወለጋና በምዕራብ ወለጋ ያለውን ያለመረጋጋት፣ እየደረሰም ያለውን ጥቃት ተከትሎ መንግሥት እየወሰደ ባለው እርምጃ ወጣቷ የኦነግ አባል ጫልቱ ታከለ መታሰሯ ተሰማ፡፡

አዲስ አበባ በተለምዶ አሜሪካን ግቢ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ የተወለደችውና ረዘም ያለ የልጅነት ዘመኗን በወለጋ ያሳለፈችው ጫልቱ ታከለ፤ በህወሓት መራሹ መንግስት በኹለት ዙር (ስምንት ዓመትና ከአንድ ዓመት በላይ) በጥቅሉ አስር ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ በኦነግ አባልነት ተጠርጥራ ለእስር ከመዳረጓ ባሻገር፣ ከባድና ዘግናኝ የሆኑ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶች ተፈፅመውባታል፡፡

ለውጡን ተከትሎ ከእስር ከተፈታች በኋላ በይፋ የኦነግ አባል በመሆን፣ ወለጋ ሻምቡ ከተማ በሚገኘው የፓርቲው ጽ/ቤት ውስጥ ሥትሠራ የቆየችው ጫልቱ ታከለ፣ ባለፈው ዓመት የኦነግ ሸኔ ጦር በአካባቢው እያደረሰ ካለው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ነፍሰ ጡር ሆና ለእስር ተዳርጋ እንደነበርም ይታወሳል፡፡

ጥር 17 ቀን 2012 ዓ.ም ፖሊስ ሌሊት 11 ሰዓት ላይ ሻምቡ የሚገኘው የቤተሰቦቿን መኖሪያ ቤት ሰብሮ በመግባት፤ ጫልቱን በቁጥጥር ሥር እንዳዋላት እየተናገረ ነው፡፡ ወጣቷ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) አባል ጫልቱ ታከለ፣ መጽሔታችን ለህትመት እስከገባችባት ሰዓት ድረስ በሻምቡ ፖሊስ ጣቢያ በእስር ላይ እንደምትገኝ ታውቋል፡፡

## አምንስቲ ኢንተርናሽናል የታሰሩት 75 የኦነግ ደጋፊዎች እንዲፈቱ ጠየቀ

አምንስቲ ኢንተርናሽናል ባወጣው መግለጫ ኢትዮጵያ ውስጥ የጅምላ እስር እየጨመረ መምጣቱን ጠቁሞ፤ በተለይም በሳምንቱ መጨረሻ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ደጋፊ የሆኑ 75 ሰዎች በጅምላ መታሰራቸው አግባብ ስላለሆነ፣ በአስቸኳይ ሊፈቱ ይገባል ብሏል፡፡

እነዚህ የኦነግ ደጋፊዎችና አባላት በተለይ በምዕራብ ጉጂ ዞን ፈንጫ ከተማ፣ እንዲሁም በሻምቡ፣ ሆድሮ ጉድሩ ወለጋ ዞኖች መታሰራቸውን የጠቆመው የዓለም አቀፍ የሰብኣዊ መበት ተሟጋች ድርጅቱ በመግለጫው "ይህ ድንገቴ የጅምላ እስር የዴሞክራሲ መብቶችን የሚሸረሽር ነው፡፡ በተለይም ነፃና ገለልተኛ እንዲሆን በሚጠበቀው የመጪው ምርጫ ላይ ክፉ ጥላውን ያጠላል" ሲል አስታውቋል፡፡

ሰሞኑን የተካሄደው የጅምላ እስሮች አሳስበውኛል ያለው አምነስቲ ኢንተርናሽናል፤ ፖሊስና መከላከያ የመልሶ ማቋቋሚያ ስልጠና በሚል ከባለፈው ዓመት የካቲት ወር ጀምሮ እስር ሲያካሂድ እንደነበር በመጠቆም፤ ብዙዎቹ በተለያዩ የመከላከያና የፖሊስ ማጎሪያዎች ጊዜያቸውን ካሳለፉ በኋላ በመስረምና ጥቅምት ወር ላይ መፈታታቸውን ገልጿል፡፡

አንጋፋው የሰብኣዊ መብት ተሟጋች አምንስቲ ኢንተርናሽናል "የኦነግ አባልና ደጋፊ ናችሁ" በሚል በጅምላ የታሰሩት ሰዎች እንዲፈቱ መጠየቁ ተገቢ ቢሆንም፣ በኦሮሚያ ክልል ደምቢ ዶሎ ከተማ ከታገቱ ኹለት ወር ሊሞላቸው አራት ቀናት የቀራቸው የአማራ ብሔር ተወላጅ ተማሪዎች፤ አሳሳቢ ጉዳይ አንዳችም ነገር ትንፍሽ አለማለቱ በእጅጉ የሚገርም መሆኑን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በመናገር ላይ ናቸው፡፡

# ኢየሩሳሌም የማትከፋፈል የእስራኤል ዋና ከተማ መሆኗን ዶናልድ ትራምፕ ተናገሩ



አወዛጋቢው የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ሰላም ስለራቀው መካካለኛው ምስራቅ እፁብ ድንቅ የሆነ እቅድ ይዠለሁ ሲሉ በከረሙት መሰረት፤ “የዘመኑ ታላቅ የሰላም እቅድ” ያሉትን ሀሳብ ማክሰኞ ምሽት በቤንጃሚን ናታንያሁ ታጅበው ይፋ አድርገዋል፡፡
ትራምፕ ባደረጉት ንግግር ላይ፤ የፍልስጤሙ መሪ መሀመድ አባሽ በጭራሽ በቦታው አልነበሩም፡ ፡ በተጨማሪም ፍልስጤማውያኑን የሚወክል አካልም በቦታው አልተገኘም፡፡ የኦማንና የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ ተወካዮች በታዛቢነት ተገኝተው ሊሆን ይችላል እየተባለ ነው፡፡
በርካቶች ለእስራኤል ያደላ ነው ያሉት ይህ “የክፍለ ዘመኑ የሰላም እቅድ” የዓለምን ትኩረት ስቦ አምሽቷል፡፡ የዶናልድ እቅድ ነፃ የፍልስጤምን አገርን የሚፈቅድ ቢሆንም፣ ለእስራኤል ህገ ወጥ ይዞታዎች በስፋት እውቅና የሚሰጥ ሆኗል፡፡ “ይህ እኔ ያመጣሁት እቅድ ካልሠራ ሌላ ምንም ነገር ሊሠራ አይችልም” ሲሉ ትራምፕም ተናግረዋል፡፡
በአንፃሩ የፍስልጤሙ ፕሬዝዳንት መሐመድ አባስ “አሻጥር ነው” ሲሉ የሰላም ሰነዱን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርገውታል፡፡ የሰነዱን ይፋ መሆን ተከትሎ ፕሬዚዳንት አባስ በራማላህ ባደረጉት ንግግር “ለትራምፕና ናታንያሁ የምለው አለኝ፤ ኢየሩሳሌም ለገበያ አትቀርብም፤ መብቶቻችን ለሽያጭ አይቀርቡም” ብለዋል፡፡
ትራምፕ በምጣኔ ሐብት ለተንኮታከተችው ፍልስጤም፤ በታሪኳ አይታም ሰምታም የማታውቀው የኢንቨስትመንት ገንዘብ እንሰጣታለን ማለታቸውን ተከትሎ ነው መሐመድ አባስ ከላይ የሰፈውን ሀሳብ የሰነዘሩት፡፡ አሜሪካ ፍልስጤም ሀሳቡን (ዕቅዱን) ከተቀበለች 50 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ይሰጣታል ነው የተባለው፡፡
“የክፍለ ዘመኑ የሰላም ሰነድ”ን ዶናልድ ትራምፕ በበላይነት ሲያረቁ ከነበሩት ሰዎች መሀል የትራምፕ ሴት ልጅ ኢቫንካ ትራምፕ ባል ጄርድ ኩሽነር ግንባር ቀደሙ ነበር፡፡ የሰላም ሰነዱ ይፋ መሆንን ተከትሎ በበርካታ የአረብ ከተሞች የተቃውሞ ሰልፍ የተካሄደ ሲሆን በጋዛ ሰርጥ ፍልስጤማውን የትራምፕ ምስል ሲያቃጥሉ ውለዋል፡፡


# በሶማሌ ክልል ህገ ወጥ መሣሪያ ሲያዘዋውር የነበሩ ተያዙ

በሶማሌ ክልል ውስጥ ህገ ወጥ የጦር መሳሪ ሲያዘዋውሩ የነበሩ ተጠርጣሪዎች ማክሰኞ ጥር 19 ቀን በቁጥጥር ሥር መዋላቸው ተሰማ፡፡ የሶማሌ ክልል ልዩ ኃይል ከጅግጅጋ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኘው መጋሎ ቃረን መቆጣጠሪያ ጣቢያ ባደረገው ድንገተኛ ፍተሻ በቶጎ ውጫሌ ድንበር በኩል በህገወጥ መንገድ በተሽከርካሪ ተደብቆ ሊገባ የነበረ 39 ሽጉጥ ከተጠርጣሪዎቹ ጋር መያዙ ተገልጿል፡፡
ህገወጥ መሳሪያውን ይዘው የነበሩት ሦስት ተጠርጣሪዎች እና አንድ ተሽከርካሪ መያዙንም የክልሉ ልዩ ኃይል አረጋግጧል፡፡

# “ኢትዮጵያ ትበታተን” ያሉት የኦብፓ አባል እንግሊዛዊ ሆነው ተገኙ

የመከላከያ ሠራዊትን ከድተው ኦነግን፣ ኦነግን ጥለው ወደ ኦዴፓ በመከረባበት፣ የኦሮሚያ ክልል የፀጥታ ቢሮ ሓላፊ በመሆን ተሹመው የነበሩት ብ/ጄነራል ከማል ገልቹ በመሰረቱት ኦብፓ ፓርቲ ውስጥ በአባልነት የተመዘገቡ አንድ ሰው ዜግነታቸው እንግሊዛዊ መሆኑን ምርጫ ቦርድ አስታወቀ፡፡
በተጠቀሰው ፓርቲ ውስጥ በአባልነት የተመዘገቡት አቶ ሊበን ዋቆ ምርጫ ቦርድ በብ/ጀነራል ከማል ገልቹ ለሚመራው ፓርቲ በፃፈው ደብዳቤ ላይ ግለሰቡ ዜግነታቸው እንግሊዛዊ መሆኑ ስለተደረሰበት፤ ፓርቲው ይህንን አምኖ በመቀበል አቶ ሊበን ዋቆን ከፓርቲ አመራርነት በማንሳት በሌላ አመራር እንዲተካ አሳስቦ ነበር፡፡
ፓርቲውም ከምርጫ ቦርድ የተላለፈለትን ትዕዛዝ በመቀበል ግለሰቡን ከነበራቸው ሓላፊነት በማንሳት በሌላ ሰው ተክቷል፡፡ ምርጫ ቦርድም ይህን ማረጋገጡ ታውቋል፡፡
እንግሊዛዊ ዜግነት የያዙት አቶ ሊበን ዋቆ፤ በቅርቡ “ኦሮሞ ነፃ እንዲወጣ ከተፈለገ ኢትዮጵያ ትበታተን፡፡ ኢትዮጵያ የኦሮሞ ዕዳ ነች” ዓይነት መልዕክት ማስተላለፋቸው አይዘነጋም፡፡

# የጃዋር ዜግነትን በተመለከተ እስከ ጥር 29 ኦፌኮ ምላሽ እንዲሰጥ ለ2ኛ ጊዜ ተጠየቀ



በቅርቡ በመረራ ጉዲና የሚመራው ኦፌኮ (ኦሮሞ ፌደራላዊ ኮንግረስ) ፓርቲን የተቀላቀለው የጃዋር መሐመድን ዜግነት በተመለከተ ፓርቲው በአስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጥ ምርጫ ቦርድ ለኹለተኛ ጊዜ ደብዳቤ እንደፃፈ ተሰማ፡፡
በወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ የሚመራው ምርጫ ቦርድ፤ አሜሪካዊ ዜግነት ይዞ በኢትዮጵያዊነት ኦፌኮን እንዲቀላቀል የተደረገው ጃዋር መሐመድን በተመለከተ ለኦፌኮ በድጋሚ በፃፈው ደብዳቤ እስከ ጥር 29 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ፣ የጃዋር መሀመድን የዜግነት ጉዳይ ኢትዮጵያ ለመሆኑ በማስረጃ ካላቀረበ እርምጃ እንደሚወስድ አሳስቧል፡፡
ኦፌኮ በበኩሉ በህጉ መሠረት ከአባልነት እንሰርዘዋለን እያለ ነው፡ ፡ ጉዳዩን በተመለከተ ቪኦኤ ጃዋርን ለማነጋገር ጥረት ቢያደርግም ጃዋር መሀመድ ግን “በዚህ ጉዳይ ላይ ኢንተርቪው አላደርግም” ሲል ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ጃዋር በቅርቡ የእርሱን ሃሳብ በማስተጋባት በሚታወቀው ኤልቲቪ ከቤተልሄም ታፈሰ ጋር ባደረገው ቆይታ፣ ዜግነቱን በተመለከተ ለቀረበለት ጥያቄ “የዜግነቴ ጉዳይ በዚህ ሳምንት ውስጥ የሚያልቅ ነው” የሚል ምላሽ መስጠቱ አይዘነጋም፡፡

# ከቀውስ የሚያተርፍ ሥርአት?



ያሬድ ጥበቡ

50 በመቶ ሴት ሚኒስትሮች ባላት ኢትዮጵያ፣ ፕሬዚዳንቷ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰብሳቢዋ፣ የምርጫ ቦርድ ኮሚሽነሯ ሴቶች በተደረጉበት ሀገር ላይ፣ 17 ልጃገረዶች ታፍነዋል። መንግስት ተብዬው ሀይልም እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ መረጃዎች እየለቀቀ ደንታቢስነቱንና ጭካኔውን እያሳየ ይገኛል። ይህ ሁሉ አበሳ የሚደርስብን ለምን ይሆን ብዬ ራሴን ደጋግሜ ጠየቅኩ። ከዚህ ቀውስ አትራፊውስ ማነው ብዬ አእምሮዬን አስጨነቀኩ። ያገኘሁት አንድ የይሆናል መልስ ብቻ ነው። አውዳሚ ካፒታሊዝም የኢትዮጵያን በሮች እያንኳኳ መሆኑ። በሀሳብ ተከራክሮና አሳምኖ መግባት ስላልደፈረ በጓሮ በር፣ በገበያ ግርግር ማንቁርታችንን ለመያዝ እየሠራ ነው።

ወደኋላ ተመልሼ የከተብኳቸውን የመፅሀፍት ማስታወሻዎች ማገላበጥ ጀመርኩ። ናኦሚ ክላይን ስለሻክ ዶክትሪን የፃፈችውን አገኘሁ። አውዳሚ ካፒታሊዝም ከቀውስ የማትረፍ ልምድ አለው። በቺሊ በ1970ዎቹ፣ በ1999 በዩጎዝላቪያ፣ በ2001 በአሜሪካ፣ በ2003 በኢራቅ፣ በ2004 በስሪላንካ ወዘተ አውዳሚ ካፒታሊዝም ከቀውስ የማትረፍ ተግባራት ላይ ተሰማርቶ የነዚህን ሀገር ህዝቦች ንብረት ወደ አነስተኛውና የዓለምአቀፍ ትስስር ያለው ባለሀብትና መንግስታዊ ሸሪኮቹ አስተላልፏል።

በቺሊ በ1970ዎች መጀመሪያ ላይ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠውን የሳልቫዶር አየንዴን መንግስት በጄኔራል ፒኖቼ በመገልበጥ ከፍተኛ አፈናና ፍጅት ካካሄደ በኋላ፣ ህዝቡ በፍርሀትና ተስፋ መቁረጥ በተዋጠበት ቅፅበት፣ የቺሌ ህዝብ በታሪኩ ያጠራቀማቸውን ሀብቶች ለግል ባለሀብቶችና ለዓለምአቀፍ ሽርካዎቻቸው እንዲተላለፉ በማድረግ፣ የሀገሩ ድሀ ከመንግስት ያገኝ የነበሩትን ማህበራዊ ጥቅሞችና ፕሮግራሞች በማውደም ቺሌን አመሳቀለ።

በ1999 ኔቶ በዩጎዝላቪያ ላይ ያወረደውን የሚሳይሎች ጥቃት ተከትሎ በደረሰው የህዝብ መደናገጥና ተስፋ መቁረጥ ማግስት በ50 ዓመታት የሶሻሊስት ልምድ የተሰባሰበውን የህዝብ ሀብት ለግል ባለሀብቶች ካዘዋወረ በኋላ፣ በየጓሮው በተነሱት የማንነት ጥያቄዎች ጭምብል ሀገሩን አፈረሰ።

በ2001 በአሜሪካ የመንትያ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች በአልካይዳ መፍረስን ተከትሎ በተፈጠረው መደናገጥና ቀቢፀ ተስፋ መሀል የቡሽ አስተዳደር "በሽብር ላይ ጦርነት" ካወጀ በኋላ፣ ከጦርነት የሚጠቀምና የሚያተርፍ አዲስ የኢኮኖሚ መዋቅር ዘረጋ። የጦርነቱም አበጋዞች የግል ድርጅቶች እንዲሆኑ ተደረገ። እነዚህም የግል ድርጅቶች ለአንዲት ቆርቆሮ ኮካኮላ 8 ዶላር የአሜሪካንን መንግስት በማስከፈል የታክስ ከፋዩ ንብረት ወደነርሱ እንዲተላለፍ አደረጉ።

በጣም እንግዳ በሚመስል መንገድ ከመከላከያ ሚኒስትሩ ዶናልድ ራምስፌልድና ከምክትል ፕሬዚዳንቱ ጋር ቁርኝት ያላቸው ሀሊበርተንና ቤክተል የተሰኙ ካምፓኒዎች በተቋራጭነት ከለላ በቢሊዮኖች ዘረፉ። የመንግስት ሥራ በመሆን የሚታወቁ ተግባራት በሙሉ ለወታደሮች የጤና አገልግሎት ከማቅረብ ጀምሮ፣ እስረኞችን እስከመመርመር የግል ተቋራጮች (ኮንትራክተሮች) ሥራ ሆነ። ይህን ዓይነት መረን የለቀቀ ለውጥ ሲደረግ በሽብርተኝነት የደነገጠው የአሜሪካ ህዝብም ሆነ ምክርቤቱ አንዲትም ቃል አልተነፈሱም።

የዚህ "በሽብር ላይ ጦርነት" አዋጅ ገፈት ቀማሾችም ኢራቅና አፍሃኒስተን ሆኑ። በጥቅምት 2006 ከሶስት ሺህ ሰባት መቶ በላይ ኢራቃውያን ሲሞቱ፣ ሀሊበርተን ግን 20 ቢሊዮን ዶላር አተረፈ። በ2003 የአሜሪካ መንግስት 3512 ኮንትራቶችን ሰጥቶ ነበር፣ የኢራቅ ጦርነትን በጀመረ በ22 ወራት ውስጥ ግን በነሀሴ 2006 የተሰጡት ኮንትራቶች ብዛት ወደ 115 ሺህ አሻቀበ። ለሀገር ደህንነት የሚደረገውም ወጪ በ2006 ዓም በቤተሰብ ሲሰላ 545 ዶላር በዓመት ደረሰ። አሁን የአሜሪካንን ጦር መመገብ፣ ማከም፣ ማዝናናትና መጠበቅ የግል ተቋራጮች ሥራ በመሆኑ፣ ከቀውስ የሚያተርፉ ካምፓኒዎች ቁጥር የትዬለሌ ነው።

ኢትዮጵያችን ተመሳሳይ ቀውስ ውስጥ ልትገባና ሠላም አስከባሪ ሆነው የሚመጡላት ጦሮችና ከቀውስ አትራፊ የግል ኩባንያዎች አለመኖራቸውን ርግጠኞች ነን? የኢትዮጵያ መንግስት ከማን ጋር ነው የቆመው? ሴት ልጆቻችን ታግተው የመንግስታችን ግዴለሽነትና የውሸት መረጃዎች ፍብረካን ምን አመጣው? ሀገሪቱ ወደሙሉ ቀውስ እንድትገባ እየተሠራ ነውን? እኛ ተናጠልና ትንንሽ የሚመስሉ ቀውሶች ላይ ልቦናችን ተመሳቅሎ ሳለ በአባይ ግድባችንና በኢኮኖሚያችን ላይ የሚደረጉት ደባዎች ምንድን ናቸው? የመከላከያ ሚኒስትሩ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጣሉ ብለን ወሬ ስናሳድድ፣ የሚኒስቴሮች ምክርቤት በህዝብ ሀብት ላይ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ምንድን ናቸው? እኛ በሴት ተማሪዎቻችን እገታ ላይ ተጨንቀን ሳለ በአባይ ላይ የሚደራደረው መንግስታችን በማን ይሁንታ ነው? የኢኮኖሚውን አቅጣጫ ለመቀየርም ሆነ በአባይ ላይ ለመደራደር በመጀመሪያ በህዝብ ፍላጎት የተመረጠ መንግስት አያስፈልገንምን? ተቃዋሚ ነን የሚሉት ፓርቲዎችስ አገር በጠራራ ፀሀይ ወደ ቀውስ ሲገፋ ዝምታቸው ከወንጀል ትብብር ያነሰ ነውን?

30ሺህ የማይሞሉ አደሬዎችን እወክላለሁ የሚል የክልል መንግስት በተዋህዶ ክርስትያን ታቦትና ቀሳውስት ላይ አስለቃሽ መርዝና ጥይት ሲተኩስ ዝም ብሎ የሚያይ ጠቅላይ ሚኒስትር ከቀውስ ለማትረፍ እየሠራ አይደለም ብሎ አፍን ሞልቶ መከራከር ይቻላል? የዓለምአቀፍ ሚዲያውም በናይጄሪያ ወጣት ሴቶች እገታ ላይ ያን ሁሉ የሚዲያ ሽፋን እንዳልሰጠ ሁሉ በኢትዮጵያውያኑ ላይ መጨከኑ፣ ወይ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በተሰጣቸው ቃል መተማመኛ አግኝተዋል፣ አለበለዚያም ኢትዮጵያን ወደቀውሱ ጥግ ለመግፋት የሚረዳ አንድ ክንዋኔ ስለሆነ ለመፃኢው አውዳሚ ካፒታሊዝም አስፈላጊ ግብአት ነው ተብሎ ከአርኪቴክቶቻቸው ተነግሯቸዋል።

እነዚህ ትናንሽ ቀውሶች እየተበራከቱና እየጨመሩ ሲመጡ፣ አንድ ነጥብ ላይ እንዳንንበረከክ እፈራለሁ። ፈርተን ግን እጃችንን አጥፈን መቀመጥ የለብንም። ኢትዮጵያን ያህል ሀገር በአንድ ሰው ትከሻና በአንድ ሰው መልካም ምግባር ላይ ተማምነን መተው ከስንፍናና ፍርሀትም ያለፈ ወንጀል ነው። ሽግግር ላይ ነን። ያሻግረናል ተብሎ የታመነበት አስኳል ተፈርክሶ፣ የሀገራችን እጣ በአንድ ሰው መዳፍ ውስጥ ወድቋል። እንዴት በሥራ የሚረዱት ጎበዞች ጨምረንለት፣ በሽግግሩ ወቅት የሚሠሩትንም ተግባራት ወስነን፣ ሽግግሩን የተረጋጋና ዘላቂ መፍትሄ የሚያመጣ እናድርገው ብሎ አንድ ህዝብ ሳይወያይ እንዲሁ በፍርሀት ወደ አውዳሚ ካፒታሊዝም እቅፍ ውስጥ ይወድቃል? መጥኔ!

# ከበደኖ እስከ ደምቢዶሎ የዘር ጥቃት ሰቆቃ !

በዝግጅት ክፍሉ

## መንደርደሪያ

ዘርን መሰረት ያደረገው የፌደራሊዝም ስርዓት ብሔርን መሠረት ያደረገ ጥፋትና በግፍ የተሞላ ጉዳት ሲያደርስ ረዥም አመታት ተቆጥረዋል፡ ፡ ወታደራዊውን ፣ መንግስት በጠመንጃ ጥሎ ኢህአዴግ በትረ ሥልጣኑን ሲረከብ የዘር ጥቃት ሰቆቃ አብሮ ተወልዷል። በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ ብሔር ተኮር "ጥላቻ እና መከራ" ግን ከሆነው ሁሉ የበለጠ ግዘፊት ይይዛል።

"ኢትዮጵያዊነትን ይጠያል" ሲባል የኖረውና ራሱን የኦሮሞ ህዝብ ነፃ አውጪ ነኝ የሚለው አክራሪ ቡድን የዘር ጥቃት ከፍቶ በአማራ ተወላጆች ላይ መከራ ማዝነብ የጀመረበት ጊዜ ሩቅ ነው። የበደኖ እና አርባጉጉ የዘር ፍጅት ታሪክ የብሔር ጥላቻና የጭካኔ ጥቃት "የመነሻው መቼት" በግልጽ ይተርክልናል። አሳዛኙ ነገር ይህ ሁኔታ ዛሬም ድረስ አለመለወጡና እንዲያውም እየባሰበት መምጣቱ ነው።

በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ የሚደርሰው ዘመናትን የተሻገረ ዘር ተኮር ጥቃት በተለያየ ጊዜ መልክና ቅርፁን እያቀያየረ ብዙ ውድመት አስከትሏል። መቶ ሺዎችን ከኖሩበት ቀዬ ከማፈናቀል ባሻገር እጅግ በርካታ አማሮችን ለሞት እና አካል ጉዳት እንዲሁም በላባቸው ያፈሩትን ጥሪት አጥተው ሜዳ እንዲወድቁ አብቅቷል።

በ27 ዓመቱ የወያኔ ዘመን "የመንግስት ድጋፍ ጭምር ነበረው" የተባለለት ጥቃት ከለውጡ በኂላም ተባብሶ የመቀጠሉ ሁኔታ ግን ከመቼውም ጊዜ በላይ አሳሳቢ ነው። በቅርቡ ከደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎች ጠለፋ ጋር ተያይዞ እየሆነ ያለው ነገርም ጉዳዩ የት ላይ መድረሱን አመላካች ነው። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ እንዴት ያለች አደገኛ ምድር እየሆነች መሆኗንም የሚናገር ነው።

በጃል መሮ የሚመራው የኦነግ ሸኔ ሀይል አግቷቸዋል በተባሉት የአማራ ተወላጅ ሴት ተማሪዎች ጉዳይ ላይ የሚያተኩረው ይህ የግዮን ፊቸር ከጠለፋው ጋር የተያየዙ ዙሪያ ገብ ጉዳዮችን በዝርዝር ለመቃኘት ይሞክራል።

## አጋቹ ማነው?

ተማሪዎቹን ያገታቸው የትኛው አካል እንደሆነ በይፋ ባይነገርም፤ ጃል መሮ የሚመራው የኦነግ ሸኔ ኃይል ስለመሆኑ ብዙዎች ግምት አላቸው። ምንም እንኳ የጠቅላይ ሚንስትሩ የፕሬስ ሴክሬታሪ ኃላፊ አቶ ንጉሡ ጥላሁን በጥር 2 ቃለ-ምልልሳቸው ታግተው ከነበሩ አብዛኞቹ ተለቀዋል ቢሉም፤ ተማሪዎቹን ያገታቸው ማነው? ከተለቀቁ የት ነው የሚገኙት? ከወላጆቻቸው ጋር ለምን እንዲገናኙ አልተደረገም? ለሚሉ እና ለሌሎች ጥያቄዎች በመንግስት በኩል ምላሽ አልተሰጠም።

ከተማሪዎቹ መታገት በኂላ ከቢቢሲ ጋር ቃለ-ምልልስ አድርጎ የነበረው በምዕራብ ኦሮሚያ የሚንቀሳቀሰው የቀድሞ የኦነግ ጦር አዛዥ ዲሪባ ኩምሳ ወይም ጃል መሮ "ይህን ለመጀመሪያ ጊዜ እየሰማሁ ያለሁት ከእናንተ ነው። የትግል ዓላማችን ከተማሪዎች ጋር አይገናኝም። በተማሪዎቹ ላይም ይህን የተባለውን አይነት ተግባር አልፈጸምንም። እንደተለመደው የእኛን ስም ለማጉደፍ የተወራ ነው እንጂ በፍጽም እንዲህ አይነት ተግባር አሁንም ወደፊትም እንፈጽምም" ሲል አስተባብሏል።

ዩኒቨርስቲው ያጋጠመን አለመረጋጋት ሸሽተው ወደ መጡበት ሲመለሱ ባልታወቁ ወገኖች ተይዘው ደብዛቸው የጠፋው ተማሪዎች ጉዳይ ከመገናኛ ብዙሃን ርዕስነት አልፎ ለሰልፎቹ መካሄድ ምክንያት ሆኗል።

## እገታው ያስነሳው ህዝባዊ ቁጣ

ባለፈው ማክሰኞ ጥር 19/2012 በአማራ ክልል ርዕሰ ከተማ በተካሄደው የተማሪዎቹን መታገት በሚያወግዘው ሰልፍ ላይ በርካታ ቁጥር ያለው የከተማው ነዋሪ ተሳታፊ ሆኗል። የአማራ ክልል የሰላምና የህዝብ ደህንነት ጉዳዮች ቢሮ በክልሉ የተካሄዱት ሰልፎች ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ መጠናቀቃቸውን አስታውቋል። ቢሮው ይህን ይበል እንጂ በባህር ዳር በተካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የክልሉ ባለስልጣናት በባህር ዳር ዓለም አቀፍ ስታዲየም ለተገኘው ህዝብ መልዕክት ለማስተላለፍ ሲሞክሩ የተቃውሞ ድምጽ ተሰምቶ ዝግጅቱም መቋረጡን ለማወቅ ተችሏል። ከክቡር ትሪቡን አቅጣጫ ድንጋይ የተወረወረ ሲሆን፣ ከስታዲየም ውጪም የተኩስ ድምጽ ሲሰማ ነበር።

ከባህር ዳር ከተማ ውጪ ደብረማርቆስ፣ ወልዲያ፣ ቆቦ፣ዋድላ፣ ሸዋ ሮቢት፣ ዱር ቤቴ፣ ዳንግላ፣ ደብረ ብርሃን፣ ፍኖተ ሰላም፣ እና በሬ የተቃውሞ ሰልፎቹ የተካሄዱባቸው ከተሞች ናቸው። በተቃውሞ ሰልፎቹ የተሳተፉ ሰዎች መንግሥት የታገቱትን ተማሪዎች ጉዳይ ችላ ማለቱንና ተገቢውን መረጃ ባለመስጠቱ ወቀሳ ከማቅረባቸው በተጨማሪ፤ ታጋቾቹ ተለቀዋል ተብሎ የተሰጠው መግለጫን "ሐሰተኛ" በማለት ምላሽ እንዲሰጥበት ጠይቀዋል።

ድርጊቱን ለማውገዝ በተለያዩ የአማራ ክልል ከተሞች ውስጥ ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉት ሰዎች መንግሥት ስለታገቱት ተማሪዎች ተገቢውን መረጃ እንዲሰጥ፣ ተማሪዎቹ እንዲለቀቁ፣ መንግሥት በአጋቾች ላይ እርምጃ እንዲወስድና በጉዳዩ ውስጥ እጃቸው አለበት የሚባሉ አካላትም በሕግ እንዲጠየቁ ጥሪ አቅርበዋል። በሁሉም ቦታዎች በተካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎች ላይ በደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ሲማሩ የነበሩና ለወራት የደረሱበት ያልታወቁት ተማሪዎች ያሉበት ሁኔታ እንዲገለጽ እንዲሁም በቶሎ ተለቀው ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ እንዲደረግ በአጽንኦት ተጠይቋል። ታግተዋል የተባሉት ተማሪዎች ቁጥር 17 እንደሆነ የተነገረ ሲሆን ከመካከላቸው 13ቱ ሴቶች መሆናቸው ተጠቅሷል። በዚህም መሰረት ባለፉት ሳምንታት በማሕበራዊ የመገናኛ መድረኮች ላይ "እህቶቻችንን መልሱ" በሚል ርዕስ ዘመቻዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል።

## እነማን ምን ጻፉ?

በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ፈጥነው ሀሳባቸውን ከሚሰነዝሩ ኢትዮጵያውያን መካከል አንዷ የሆነችው መስከረም አበራ የተማሪዎቹን እገታና ይህንኑ ተከትሎ በተፈጠሩ ሁኔታዎች ላይ የሚከተለውን ጽፋለች፡-…የታገቱ ተማሪዎችን ለማስለቀቅ የሃገሪቱ መንግስት በበቂ ሁኔታ እየሰራ እንዳልሆነይሰማኝ ነበር። አቶ ላቀ አየለ የተባሉ የአማራ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድርም ይህንኑ ሃሳቤን ቃል በቃል ደግመውታል ቢቢሲ አማርኛ እንደዘገበው።ከልብ ያለቀሰ መንግስት እንኳን ከጀማሪ ሽማቂ ቀርቶ አሜሪካን ሳይቀር ብርክ ከሚያስይዘው ከዝነኛው አለማቀፍ አሸባሪ ቦኮሃራም እንኳን ዜጎቹን አስለቅቋል።

ልጅ የወለደ ሰው፣ ከሴት የተፈጠረ ሰው መንግስት ሲሆን፣ፖለቲከኛ ነኝ ሲል ከሰው የሚያዋስነው ባህሪ ለምን እንደሚርቀው ሳስብ በጣም ያሳዝነኛልም ይገርመኛልም!

ቢቢሲ በዘገባው የጃል መሮ ኦነግ ልጆቹን እንዳላገተ እንደተናገረ ዘግቧል። ሽማቂዎች እንዲህ ያለውን ነገር "ለአቴንሽን" ማግኛነት ስለሚፈልጉት ጃል መሮ ቢያግት ኖሮ አግቻለሁ እንደሚል አስባለሁ።

ጃል መሮ ሃላፊነቱን ካልወሰደ ልጆቹን በማገቱ ሊጠረጠር የሚችለው ሌላ ቡድን የጃዋርን እግር ተከትሎ የተመሰረተው "አባ ቶርቤ" የተባለው ገዳይ ቡድን ሊሆን ይችላል። ይህ ቡድን የአሜሪካ ፓስፖርት ባለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ እንደተመሰረተ እና እንደሚመራ በአንድወቅት የጃዋር አጋር የነበረው አቶ ገረሱ ቱፋ ከትቂት ወራት በፊት የተናገረበትን ዘገባ እንዳነበብኩ አስታውሳለሁ።

ይህ አባ ቶርቤ የተባለው ቡድን በአክራሪነቱ ከኦነግ የባሰ በመሆኑ የክረቱ መድረሻም መነሻም የአማራ ጥላቻ መሆኑን፣ ልጆቹ ደግሞ አማራ መሆናቸውን ሳስብ በልጆቹ ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ እገምታለሁና እጅግ የሚቀፍ ስሜት ይሰማኛል!!!! ለዚህ ሁሉ ሰቆቃ የነ በቀለ ገርባ የአደባባይ ድንፋታ፣የነ ሊበንዋቆ ድፍድፍ የጥላቻ ሰበካ፣ የጃዋር መሃመድ "Ethiopia out from Oromoiya" መፈክር፣የፀጋዬ አራርሳ የጥላቻ እብደት፣የለማ መገርሳ "የህዝቤ ጥያቄ ተጠለፈ" ቁጭት፣የሽመልስ አብዲሳ "ስበር በለው"ንግግር…. ሁሉ አስተዋፅኦ አለው! ከሁሉም በላይ ግን አስተዋፅኦ የሚያደርገው የመንግስቱን ግማሽ ለሽማቂ አስረክቦ "እዛ መሄድማ እኔንም ያስፈራኛል" እያለ ኢትዮጵያን እንደሚያስተዳድር የሚሰማው የዶ/ር አብይ አስተዳደር ነው። "እኔ የሰፈር ሚሊሻ አይደለሁም" የሚሉት አብይ ምን እየሸሹ እንደሆነ ግልፅ ነው። የሰፈር ሚሊሻ ባይሆኑም ጠንካራ የሰፈር ሚሊሻ እንዲኖር የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው መንገር ያስፈልግ ይሆን? ለራሱም እየፈራ እንደሆነ ሲናገር የማያፍረው የአብይ አስተዳደር ቀስ በቀስ አንድ ሰሞን ሞቃድሾ ኮሽ ሲል ወደ አንጋሹ መለስ ቤተ-መንግስት እያለከለከ የሚሮጠውን የሱማሌ መንግስት እንዳይሆን ስጋት አለኝ። ለዛውም የሚሮጥበት ከተገኘ ነው! ይህ አስተዳደር የሚያስተዳድረው ከጃል መሮ፣ ▶

ከአባቶርቤ፣ከህወሃት፣ ከጃ-war እና ቁሮዎቹ የተረፈውን ሃገር ነው። ሁለት መንግስት አለ ሲባል የገረመን ለዛውም አሳንሶ የነገረንን ነው ለካ! መንግስትማ ከሁለት በላይ ነው።

## አባሸ ያጣው የወላጆች እንባ

ሥር የሰደደውን የብሄርተኝነት መንፈስ ተከትሎ ወደለየለት ጥቃትና ግድያ ያመራውን የዩንቨርስቲዎች እንቅስቃሴ በመስጋት፣ የትምህርት ገበታቸውን ጥለው ወደ ቀዬአቸው በመመለስ ላይ የነበሩት የደምቢዶሎ ዩንቨርሲቲ የአማራ ክልል ተማሪዎች በታጣቂ ኃይሎች ከታገቱበት ጊዜ አንስቶ ወላጆች ይህ ነው በማይባል ከፈተኛ ጭንቀት ውስጥ ነው የሰነበቱት።

ላለፉት ሀምሳ አምስት ቀናት ሽርፍራፊ ሰከንዶችን ጭምር በልጆቻቸው ሕይወት ላይ የተጋረጠውን ፈታኝ አደጋ በማሰብ በስጋት ውስጥ የከረሙት የታጋች ተማሪ ወላጆች "ግዙፉን ስህተት" በሠራው መንግሥተ በኩል "መንግሥት ከታገቱት ተማሪዎች መሀል አብዛኞቹን እንዳስለቀቀ እና ቀሪዎቹንም በእጁ ለማስገባት ድርድር እያካሄደ እንደሚገኝ በገለፁበት ወቅት በደስታ ቢያነቡም ሀሰተኛው የፕሮፓጋንዳ መግለጫ ሲጋለጥ ግን ዳግም በሀዘን ለማሰንበት ተገደዋል።

በህወሓት መራሹ ዘመን በአቶ በረከት ስምዖን እርቃናቸው የተጋለጠ ውሸቶች ይፈበረኩበት የነበረውን አሠራር በዚህ ወቅት ይዞ ብቅ ያለው የጠ/ሚኒስትሩ ፕሬስ ሴክረተሪያት ቢሮ በአቶ ንጉሡ ጥላሁን አማካይነት ያሠራጨው መልዕክት 24 ሰዓት ሳይሞላው ከእውነት የራቀ መሆኑ ተረጋግጦ መላው ኢትዮጵያውያን አንገት ካስደፋ በኋላ፣ ስራውን በአግባቡ ባልቻለው መንግሥት ላይ ቅሬታን ያስተጋቡ ተማሪዎቹም በፍጥነት እንዲለቀቁ የሚጠይቁ ሰላማዊ ሰልፎች በአማራ ክልል የተለያዩ ርዕስ ከተሞች ተካሂደዋል።

ሆኖም ይህ መጽሔት ለህትመት እስከገባበት ረቡዕ ጥር 20 ቀን 2012 ዓ.ም እኩሌ ሌሊት ድረስ ህግና መንግሥት አለባት በሚባልበት አገር ላይ በታጠቁ ኃይሎች ለሁለት ወር ለሚጠጋ ጊዜ የታገቱት ተማሪዎች የመለቀቃቸው ዜና አልተሰማም። አጋቾቹም እስካሁን ድረስ "ተማሪዎቹን ለመልቀቅ ይሄ ይደረገልኝ" ብለዋል የሚል ግልፅ የሆነ ጥያቄ መቅረቡን የሚያመለክት መግለጫ በመንግሥት በኩል አልቀረበም።

ነገሮችንና እውነታው ባልጠሩበት በዚህ ሂደት ውስጥ ግን አሁንም እነዛ ምስኪን አርሶ አደሮች በችግርና በመከራ ውስጥ ያዳደጓቸው ልጆቻቸውን ዳግም በሕይወት መታቀፍ ይችሉ እንደሆን በማሰብ በየደቂቃው በራፋቸውን ሲመለከቱ ውለው ያድራሉ። ወላጆቹ በተስፋ መቁረጥ ድባብ ውስጥ ሆነው ቸርነቱ የማያልቀው ፈጣሪ ደግ ደጉን እንዲያወጣላቸው እየተመኙ ነው።

ከታገቱት ተማሪዎች መካከል አብዛኞቹ የጎንደሯ አዲስ ዘመን ከተማ ነዋሪዎች መሆናቸውን ተከትሎ ቢቢሲ ወደ ሥፍራው በመንዝ የታገቱ ወላጅ ቤተሰቦችን ለማነጋገር ሞክሮ ነበር። በከፍተኛ ሁኔታ የሃዘን ድባብ ባጠላበት አነስተኛዋ ታሪካዊት ከተማ ያሉ ወላጆች መጨረሻው ባልለየለት የልጆቻቸው እገታ ከሀምሳ አምስት ቀናት በላይ በሰቀቀን ውስጥ መሰንበታቸው መታዘብ ተችሏል። የተማሪ በላይነሽ መኮንን ወላጅ እናት ወ/ሮ ማሬ አበባ ልጃቸው ከመታገቷ በፊትም ቢሆን ረዘም ላለ ጊዜ አላገኛትም ነበር። ለዚህ ደግሞ በምክንያትነት ያስቀመጡት የእጅም ሆነ የቤት ስልክ የሌላቸው መሆኑን ነው። "የሆነውን ሁሉ የምሰማው ከሰው ነው የምሰማው ያሉት እናት ልጃቸው የደረሰባትን ካወቁ በኋላ በእርጅና ዘመናቸው አገሬ በሚሏት ኢትዮጵያ፤ ተስፋና እምነት የጣሉበት መንግሥት ብቅ ብሎ ነበር በሚሉበት ሰዓት እንደዚህ ዓይነት ነገር መከሰቱ በእጅጉ አስደንግጧቸዋል።

‹‹ጉዴን ከሰማሁ በኋላ እህል አልበላ፤ ሌት ተቀን አየ ገድ እያልኩ እያልኩ ነው። እግዜር ቢሰማን መንግሥትም ቢራራልን፣ ልጆቻችን ቢሰድልን እያልን ነው›› ያሉት ወ/ሮ ማሬ አበባ "አሳድጌ፣ አሳድጌ ልጅ የለኝም ማለት ነው? ሲሉ ዱብ ዕዳው ያመጣባቸውን ስጋት ጥያቄ ከማቅረባቸው ባሻገር ተማሪዎቹን መንግሥት እንዳስለቀቃቸው በሰሙበት አጋጣሚ ተደስተው እንደነበር ጠቁመው፤ ተማሪዎቹ ተለቀዋል ቢባልም "ወሬው ወሬ ሆኖ ከመቅረቱ ውጪ ከልጄ ጋር መገናኘት አልቻልኩም" በማለት እውነታውን ገሀድ አውጥተዋል። ከሴቶቹ ተማሪዎች በተጨማሪ ከታገቱት ወንድ ተማሪዎች ውስጥ አንዱ የሆነው የግርማ ሀብቴ ወላጅ አባት አቶ ሀብቴ አማኙ ልጃቸው ከታገተ በኋላ በሶስተኛው ቀን በአጋጆቹ ስልክ ደውሎ የነበረበትን አከባቢ ባይገልፅላቸውም በደፈናው "ደህና ነኝ" ማለቱን ይናገራሉ።

"ተስፋዬ የነበረው እሱ ነው። እናቱ ቤተ ክርስቲያን እየተንፏቀቀች ቀን ከሌት ፈጣሪን እየለመነች ነው። እኔም የምሠራው መላ ቅጡ ጠፋኝ። ልጄ የሚያውቀው ነገር የለም። የቤት ልጅ ነው፤ እንኳን የሰው አገር የራሱንም አያውቀውም ። እናቱም የእሱን ሁኔታ አይታ በቤት ውስጥ ያሉትን ልጆች ልትመራልኝ አልቻለችም" የሚሉት አባት ሀብቴ ‹‹የማደርገው ጠፋኝ፤ ከፍ ብል ሰማይ፣ ዝቅ ብል መሬት ሆነብኝ የእሱን መከራ ሳላይ ብሞት አይቆጨኝም ነበር" ሲሉ በእንባ እየታጠቡ ስቃያቸውን ለህዝብና መንግሥት አድርሰዋል። የአቶ ሀብቴ እማኙ ተስፋ መቁረጥና ከባድ ሀዘን ያጠላበት በእንባ የራሰ ፊት የሚስተዋልበት ፎቶ ሰሞኑን በማህበራዊ ሚዲያዎች አማካይነት በስፋት መለቀቁ እና የበርካቶችን ትኩረት መሳቡ አይዘነጋም።

ጥር 2 ቀን በመንግሥት በኩል የተደረገው መግለጫ ልጃቸው ተለቆ የማየት ተስፋቸውን በእጅጉ አለምልሞት እንደነበር ያስታውሱት መሪጌታ የኔነህ አዱኛ የተማሪ ግርማነሽ የኔነህ አባት ናቸው። ‹ እስካሁን ድረስ ከልጆቻችን ጋር አልተገናኘንም መንግሥትም ያለን ነገር የለም። ገድለውብን ይሆን ብለን በፍርሃት ውስጥ ነን። በዚያ ላይ ልጆቹ አይተውት የማያውቁትን ነገር ሲያዩ ይደነግጣሉ ብለን እናስባለን። ሞተውም ከሆነ እውነቱን ነግረውን ከቤተሰብ ጋር ተላቅሰን እርማችንን ብናወጣ ይሻለናል። እንዲህ በየቀኑ ምን ሆነው ይሆን? እያልን በሰቆቃ የምንኖረው እስከመቼ ነው? የሚሉት መሪጌታ የኔነህ የልጃቸው መታገት በቤተሰባቸው ላይ ከፍተኛ ጫና ማሳደሩን ተከትሎ ባለቤታቸው ጭንቅላታቸው ክፉኛ በመጨነቁ ደባል ወስደው እንዳከረሟቸው በሀዘን ስሜት ገልፀዋል።

የሁሉም ተማሪዎች ወላጅ ፍርሃትን ስጋት ተመሳሳይ ነው። ይህን ያህል ጊዜ አግቶ የሚንቀሳቀሰው ታጣቂ ኃይል ቀጥተኛና ብሔር ተኮር የሆነ እገታ በማድረጉ የልጆቹ ሕይወት ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል እርምጃ ይወስዳል የሚል። ከምንም በላይ ደግሞ ተስፈኛ ተማሪዎቹን መታገታቸውን ከአንደ ወር በላይ ለመናገር ያልደፈረው መንግሥት አርፍዶም ቢሆን ሐሰተኛ መግለጫ ማሰራጨቱ፣ በሂደት የታየውም እንቅስቃሴም ተስፋ ሰጪ አለመሆኑ ሥልጣን ያለው አካል ህግ የማስከበርና የዜጎችን መብት የማስጠበቅ አቅሙን እንዲጠራጠሩ አድርጓቸዋል።

## የተማሪዎች ስጋትና ተስፋ

ማክሰኞ ጥር 19 ቀን 2012 ዓ.ም ከማለዳው ጀምሮ በአማራ ክልል የተለያዩ ከተሞች እህቶቻችን መልሱልን" በሚል መርህ የድጋፍ ሰልፍ የተካሄደላቸው ተማሪዎች አሁን በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንዳሉ አይታወቅም። የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳር አቶ ላቀ አያሌው ደምቢዶሎ ላይ ከታገቱት ተማሪዎች ወላጆች መካከል የተወሰኑትን አነጋግሬያለሁ ብለዋል። ም/ርዕሰ መስተዳደሩ እንደ አገር ተማሪዎችን ለማስለቀቅ የሚደረገው ጥረት አናሳ መሆኑን ተከትሎ የሚፈልገው መፍትሄ ሊገኝ እንዳልቻለና ተማሪዎቹ በስጋት ጣሪያ ውስጥ ተከልለው እንደሚገኙ ይፋ አድርገዋል። በተለይም አከባቢውን የሚያስተዳድረው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት እና የፌደራሉ መንግሥት ትኩረት መሥጠትና ተማሪዎችን ማስለቀቅ አለባቸው ሲሉ አስጠንቅቀዋል። አገር ውስጥ በውጭ የሚገኙ አንዳንድ ሚዲያዎችን ጨምሮ ባልተረጋገጠ መልኩ በታጉቱት ሴት ተማሪዎች ላይ የሰብዓዊ ጥቃት (በተለይም የመደፈር ተግባር) ተፈፅሟል እያሉ ናቸው። ይህ መረጃ ታጋቾቹ ተለቀው በአንደበታቸው እስኪያረጋግጡት ድረስ በቅድመ ግምት ወይም መላ ምት የሚቀመጥ ቢሆንም በእገታ ውስጥ የሚገኙት ወንድም ይሁን ሴት ተማሪዎች ለከባድ የስነ ልቦና ችግር መጋለጣቸው አይቀሬ ነው።፤

በተለይም ተማሪዎች ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 21 የሚደርስ መሆኑ ደግሞ በለጋ እድሜያቸው ላይ የተጋረጠውን ከባድ የስለልቦና የሕይወት የመኖር ፈተና እንዴት ያልፉት ይሆን? የሚል ጥያቄን ያጭራል። ከደምቢዶሎ ወደ ጋምቤላ በአውቶቢስ ተሳፍረው ሲጓዙ ከነበሩት ሰዎች መሀል "ሱዲ" በምትባው ትንሽ ከተማን አለፍ እንዳሉ በሚገኘው በረሃ ላይ በታጣቂዎቹ የአማራ ተወላጅ የሆኑት ተማሪዎች ብቻ ተለይተው ከአውቶቢስ እንዲወርዱ ተደርገው በተወሰዱበት ቀን በጫካ ውስጥ መሰወር የቻለቸውና ህይወቷን ያተረፈችው ወጣት ተማሪ አስመራ ሹምዬ እገታው እንኳን ለተማሪዎች ሁኔታውን ለገለጽኩላቸው ፌዴራል ፖሊሶች ጭምር አስፈሪ ነበር ብላለች።

ተማሪዎቹ በታገቱ ሶስተኛ ሳምንታቸው ሳምራዊት የተባለች ጓደኛዋ ስልክ ደውላላት ደህንነቷን ከመግለጽ ውጪ በነፃነት ልታወራት እንዳልቻለች ጠቁማ የፃፈችላት ቴክስት ላይ ግን "ጫካውን ከሰዓት ሰዓት ይቀይሩታል" ዛሬ ያደርንበትን ጫካ ነገ አናድርበትም። ሽራ ላይ አንጥፈው ያሳድሩናል። ምግብ ከፈለጉ ይሰጡናል፤ ሳይፈልጉ ይሰጡናል። ለምንድን ነው የፈለጋችሁን? ስንላቸው ከእናንተ ጋር ጠብ የለንም። ጠባችን ከመንግሥት ጋር ነው። የአማራ ህዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርግ፤ ያን ገጊዜ መንግሥትን ልጆቻችን ታግተውብናል ብሎ ሲጠይቅ እኛ ጥያቄያችንን ለመንግሥት እናቀርባለን የሚል ሀሳብ መኖሩን ገልፃለች።

አጋቹ ኃይል ይህን ይበል እንጂ ማክሰኞ ዕለት መላው የአማራ ክልል ከተሞች በሰላማዊ ሰልፍ ቢጥለቀለቁም ተማሪዎቹን ያገተው ቡድን እስካሁን "የምፈልገው ይሄን ነው" ብሎ ለመንግሥት ያቀረበው ጥያቄ የለም። በአንፃሩ ከምስኪኑ አርሶ አደር ማህበረሰብ መሀል የወጡት ተማሪዎች የታገቱበት የአማራ ክልል ልጆቹን ለማስለቀቅ ዳተኝነት ይታይበታል ነው የሚባለው። ለተማሪ አዝመራ ሹምዬ በሶስተኝነት የደረሳት የታጋጆቹ የጽሑፍ መልዕክት (ሚሴጅ) አጋቾቹ ወጣቶችን አስረው እንደሚያንገላቷቸው፣ ሴቶቹን ደግሞ እንደሚደፍሯቸውና እንደሚደበድቧቸው ያሣያል። ሕዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም የታገቱት ተማሪዎች ጉዳይ በተመለከተ ባህርዳር ከተማ ድረስ ሦስት የተለያዩ መ/ቤቶች በመሄድ ስለ እገታው ያስረዳቸው ይህች ወጣት በክልሉ መንግሥት ሀላፊዎች በኩል ያገኘችው ምላሽ ተስፋ እንዳስቆረጣት ገልፃለች።

‹‹ፖሊስ ኮሚሽን ላይ ያገኘሁት ሰው እኔን ለመሳደብና ለማሸማቀቅ ሞክሯል። የተፈጠረውን ነገር ስነግረው፤ አትዋሺ! አንቺ የምታድጊ ልጅ አይደለሽ? አትውጡ እየተባላችሁ እናንተ በመብታችሁ ነው ወጥታችሁ የመጣችሁት›› የሚል ከሚወክለው ሕዝብ ተቆርቋሪነት የራቀ አሳፋሪ አስተያየት መስጠቱን ይፋ ያደረገችው ከእገታ ያመለጠችው ተማሪ እየሆነ ያለውን ▶

ልጆቹ ያሉበትን ስቃይ ለክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን አመራ አባል ለማስረዳ ብትሞክርም ከማዳመጥ ይልቅ ደጋግሞ በሚሳደበው ፖሊስ ድርጊት ተናዳ ክፍሉን ለቅቃ መውጣቷን ተናግራለች።

በዚህን ዓይነቱ የተዘበራረቀ እና የያገባኛል እምነት በጠፋበት አሰራር ውስጥ ላለፉት 55 ቀናት በደምቢዶሎ ጫካ ውስጥ የሚንከራቱት፣ ተስፋቸውን ከመንግሥጠስ ይልቅ በፈጣሪ ላይ ያደረጉት የታገቱ የአማራ ተወላጅ ተማሪዎች መጨረሻ ምን ይሆን? አብረን የምናየው ቢሆንም ለወላጅም ይሁን ለሕዝብ እግዚአብሔር ቸር ወሬ እንዲያሰማን መልካም ምኞታችን ነው።

## የመንግሥት እርምጃና አካሄድ

ሁለት ዓመታትን ሊደፍን ከሁለት ወራት በላይ ያልቀረው የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት ያለፈውን አንድ ዓመት በዜጎች መከራና የከፋ ስቅየት ለማሳለፍ ተገድዷል። በየክልሉና አከባቢው የሚፈጠሩ የእርስ በርስ ግጭቶችና ሻገር ሲሉም የለየላቸው የሚመስሉ ፍጅቶች ህዝቡ በጭብጨባ የተቀበለውን መንግሥት በጨበጣ እንዲወርድ እስከመመኘት እንዳደረሰው የተለያዩ አስተያየቶችን ዋቢ አድርጎ መግለፅ እየተለመደ ነው። ዜጎች የዜግነት ዋስትናቸውን ከመቼውም ጊዜ በላይ ማጣታቸው በፍርሃት ጠለል ውስጥ ህይወታቸውን እንዲመሩ አስገድዷቸዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ከጊዜ ጊዜ አቅሙ እየላሸቀ የመጣው የመንግሥት የህግ የበላይነትን የማስፈን ቁርጠኝነትም ትልቅ ፈተና ሆኖ በሙሉ ኃላፊነት የሚመራቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የግምት ቀጠናነታቸው አይሏል። ከአዳማ እስከ ድሬድዋ፤ ከመደወላቡ እስከ ደምቢዶሎ፣ ከደብረ ማርቆስ እስከ ደብረ ብርሃን በሚቆጠሩ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ፈንቅሎ የወጣውም ይህ የማይታበል ዕውነታ ነው። ተቋማቱ ከምናብ ልህቀት ይልቅ የአስደንጋጭ ህልፈት ዜናዎች መከሠቻ መሆናቸው ደግሞ የበርካቶችን ዕንባ አራጭቷል፤ የብዙዎችንም ልብ ሠብሯል።

በነኚህ አስደንጋጭና ተደጋጋሚ ሁነቶች ላይ አስተያየታቸውን እንደሚሰጡ ግለሰቦች ዕምነት ደግሞ የችግሩ ምንጭ ወደ አንድ ጠገግ ይሄዳል። በተቋማቱ ውስጥ በግላጭ የሚታየው ብሔረሰብንና ዋልታ የረገጠ ፖለቲካዊ አቋምን ዋቢ ያደረገ እሰጥ አገባ የአጠቃላይ ሀገሪቱ መዋቅራዊና ተዋስያዋዊ ሽኩቻ ነፀብራቅ ነው። በባላንጣነት መጠራጠሩና "እኛ" እና "እነርሱ" የተቀየደው የመሃሉና ዳሩ ፖለቲካ በተማሪዎቹ አቋምና ስብዕና ላይ ገፍቶ ያሳደረው ተፅዕኖ በቀላሉ የሚገለፅ አይደለም። ይህ በአንድ ሀገር ዜጋ በሆኑ ተማሪዎች ዘንድ የሚስተዋል የተንፈራቀቀ ልዩነት ደግሞ ከ "መቻቻል" እና "መመካከር" ገገር ስሌቶች ያፈነገጠ መሆን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱን የሥጋት ንፍቀ ክበብ አድርጓቸው ቆይቷል፤ አሁንም ቀጥሏል። በሀገር ደረጃ ያለው የፖለቲካ አለመግባበት በሰከነና በሰለጠነ መንገድ መመራት ያለመቻሉ ውጤት ደግሞ መንግሥትን (በተቋማቱ የጊዜው በሚሰሙ መሪር ሀዘኖችን ምክንያት) ወደ ሙሉ ቁጥጥር እንዲገባ ገፊ ምክንያት እንደሆነው ይታመናል። ለዚህ አብነት የሚሆነው ደግሞ ከአንድ ወር በፊት ሁሉም የሚገኙ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች በፌዴራል ፖሊስ ጥበቃ ሥር እንዲገቡ በከፍተኛ የሳይንስ ትምህርት ሚኒስቴር መወሰኑ ነው።

ውሳኔው ሙሉ በሙሉ ገቢራዊ ሆኗል ሊባል ባይችልም፤ በተማሪዎች ላይ የሚደርሰው ሠቆቃ ግን እየባሰ ስለመምጠቱ መናገር ይቻላል። በተለይም ደግሞ ሠሞኑን ትልቅ አጀንዳ የሆነው በደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ላይ ነው። "ሀገራችን ነው፤ መንግሥትም ይጠብቀናል" ብለው በትምህርት በወጡ ዜጎች (በተለይም ሴቶች) ላይ ይህ አይነቱ አደጋ መፈጠሩ ብዙዎች ጉዳዩን ከመንግሥትና መንግሥት ጋር ብቻ አያይዘው የዳተኝነቱ መግለጫ አድርገው እንዲቆጥሩት አስገድዷል። በታገቱት ተማሪዎች ዙርያ በፌደራልና ክልል መንግሥታት፣ በክልል እና ክልል መንግሥታት መካከል የተስተዋለው ዳርና ዳር የወጣ የመረጃና የአቋም መደበላለቅ እንደብዙዎች ዕምነት ከሆነ ሀገሩ ላይ ለዜጎች ህይወት ደህንነትና ዋስትና መስጠት የሚችል መንግሥት ላለመኖሩ በቂ ማስረጃ ነው።

የአቶ ተመስገን ጥሩነት ተደበላልቆ የመጣ መረጃ

በደምቢ ዶሎ የተማሪዎች መታገትን ከአንድ ወር ቀደም ብለው ለህዝብ ያጋለጡ የማኅበራዊና ሜይን ስትሪም ሚዲያዎች የነበሩ ቢሆንም ቁጥራቸው ግን ጥቂት ነበር። በዚህም ምክንያት ጉዳዩ ተገቢ ትኩረትም ሆነ የሚዲያ ሽፋን ሳይሰጠው ቆይቷል። የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ የ ‹‹እንኳን አደረሳችሁ›› መልዕክት ለማስተላለፍ ወደ ቴሌቪዥን ብቅ ያሉት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ግን በአያሌ ጉዳዮች መግለጫቸው ውስጥ አንድ አጀንዳን ወደፊት አመጡ። ርዕሰ መስተዳደሩ በክልሉ ውስጥ ከተፈጠረው የሞጣው መስጊድ ቃጠሎና የታዳጊ ህፃናት ግድያ ጋር አያይዘው በኦሮሚያ ክልል አራት ያህል ተማሪዎች ስለመታገታቸው መረጃው እንዳላቸው ገለፁ። እነኚህን የታገቱ ተማሪዎች ለማስለቀቅም ከአከባቢው ሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎችና የፀጥታ አካላት ጋር ንግግር እየተደረገ ስለመሆኑ አስታወቁ። ይህ የአቶ ተመስገን ጥሩነህ የሳሳ ጥቁምታ ቀደም ሲል የተማሪዎቹን መታገት አስመልክቶ በስሱ ሲሰጥ የነበረው የማሕበራዊ ሚዲያ ሽፋን ቢያጎላውም ርዕሠ መስተዳድሩም ሆነ የክልሉ መንግስት በታገቱት ተማሪዎች ቁጥርም ሆነ የደረሰውን አስደንጋጭ ሁነት ለብቻው ይፋ ለማድረግ የሰነፈበት አካሄድ አስተዛዛቢ ሆኖ እንዳገኙት የገለፁ ነበሩ። ከምንም በላይ ጉዳዩን ምፀት ያደረገው ግን ርዕሠ መስተዳድሩ "ታገቱ" ያሏቸውን ተማሪዎች ለማስለቀቅ በጥምረት እንቅስቃሴ እያደረግን ነው ብለው ከገለጿቸው የኦሮሚያ ክልል አመራሮች ቀናትን ተከትሎ የተሰጠው ምላሽ ነው።

## የማኅበራዊ ሚዲያ ግፊትና የመንግሥት አካላት አቋም መዛነቅ

መንግሥት በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ከታገቱ ሁለት ወራት እንደሆናቸው የሚነገረውን ተማሪዎች ጉዳይ ፈልጎ ሳይሆን ተገድዶ ምላሽ ለመስጠት የደፈረ ይመስላል። እንደ በቢሲ አማርኛ ያሉ የመገናኛ አውታሮች ከታጋቾቹ ያመለጠች አንድ እንስትን ማነጋገራቸው ተከትሎ መጠኑ እየሰፋ የመጣው የማህበራዊ ሚዲያ ተቃውሞም በተለያዩ ደረጃ ባሉ የመንግሥት ባለሥልጣናት ዘንድ ፍፁም ተቃራኒና ተፃራሪ ሊባል የሚችል መግለጫን አሰምቷል። ከፍ ሲል የተጠቀሱት የአማራ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳደር ጉዳዩን አስመልክተው ለመጀመርያ ጊዜ ጥቁምታ መስጠታቸውን ተከትሎ የክልሉ ፀጥታና ደህንነት ቢሮ ደጅ ያንኳኳው የመገናኛ ብዙኃን ጥያቄ ግን በቢሮው ኃላፊ አቶ አገኘሁ ተሻገር በኩል ምላሽ ሳያገኝ ቀርቷል። የበረታውን የግል መገናኛ ብዙሃንና ማኅበራዊ ትሥሥር ገፆች ግፊት ተከትሎ ታዲያ ወደ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ስቱዲዮ ያመሩት የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፕሬስ ሴክሬተርያት ሃላፊ አቶ ንጉሱ ጥላሁን "ከታገቱት ተማሪዎች መካከል 21ዱ ተለቅቀዋል፤ ቀሪ ስድስት ተማሪዎች ለማስለቀቅ እየተደራደርን ነው" ማለታቸው ለቀናት የውዝግብ መነሻ ሆኖ ሰንብቷል።

ይህን ተከትሎ ክስተቱ በቀጥታ የሚመለከተውን የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ለማነጋገር ሲሞከር የተገኘው ምላሽ ግን እጅጉን ግራ አጋቢ ነበር። በተለይም ደግሞ በደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ የሴት ተማሪዎች ላይ እገታ መፈፀሙን ተከትሎ በክልሉ ፀጥታና ደህንነት ኃላፊው እና በክልሉ ኮሚኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ በኩል የተሰጠው ምላሽ ለብዙዎች ‹‹ተፈጠረ›› በተባለው ሁነት ላይ ‹‹ድራማ ነው›› እስከማለት ለደረሰ አስተያየት ተጋብዘዋል። የፀጥታና ደህንነት ኃላፊው ኮ/ል አበበ ገረሱ ከቢቢሲ አማርኛ ጋር በነገሯቸው ቆይታ ‹‹እገታ ስለተባለው ነገር መረጃው የለኝም›› በማለት ለጉዳዩ እንግዳ መሆናቸውን ከመግለፃቸው በላይ የኮሚዩኔኬሽን ቢሮው ኃላፊ አቶ ደረሰ ተረፈ ‹‹ታፍኖ የተወሰዱ ተማሪዎች የሉም›› እስከሚል እርግጠኝነት የደረሰ ምላሽ መስጠታቸው የነገሩን አሳሳቢነት ጨምሮት ሰንብቷል። ይህ በሆነ በቀናት ውስጥ ደግሞ ኮ/ል አበበ ገረሱ ‹‹የታገቱት ተማሪዎች ተለቅቀው ወደ ዩኒቨርስቲ ተመልሠዋል›› የሚል ሌላ መግለጫ መስጠታቸው ከታገቱት ተማሪዎች ቤተሰቦች ‹‹ልጆቻችሁ የታሉ?›› የሚል ጥያቄ ገፍቶ ወደፊት እንዲመጣ ምክንያት ሆኗል።

## አንገት ያስደፋው የፌዴራል ፖሊስና መከላከያ ምላሽ

በፌደራልና ክልል መንግሥታት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት አማካኝነት ታግተው ወራት ባስቆጠሩት ተማሪዎች ዙርያ የተሰጡት መግለጫዎች እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ነበሩ። በጉዳዩ ላይ ያላቸው መረጃም ሆነ ስለተፈጠረው ክስተት ያላቸው ቀረቤታም እንዲሁ የተራራቀ እንደነበር ይፋ ካደረጓቸው ንግግሮች መረዳት ይቻላል። በዚህም ምክንያት ለጉዳዩ ሰፊ አፅንኦት የሰጡ ብዙሃን መገናኛዎች የፌደራል ፖሊስና መከላከያን መረጃ ለመጠየቅ ጥረት አድርገዋል። የተገኘው ምላሽ ግን አሁንም ግራ አጋቢና አሳዛኝ ነው። አሥራት ቴሌቪዥን ያነጋገራቸው የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ጀይላን አብዲ ‹‹መንግስት ተለቀቁ ያላቸውን ተማሪዎች በተመለከተ ያለው መረጃ የት ደረሰ?›› ተብለው ሲጠየቁ ‹‹እሱን የተናገረው ሰው ነው የሚያውቀው›› የሚል መልስ በመስጠት መንግስት በአቶ ንጉሱ ጥላሁን በኩል ‹‹ተለቀዋል›› ስላላቸው 21 ተማሪዎች ጉዳይ ፌደራል ፖሊስ ባዕድ መሆኑን ገልፀዋል። ይህ የዳይሬክተሩ አቶ ጄይላን ንግግር አነጋጋሪ በሆነ ቀናት ውስጥ ዳግመኛ ጥያቄው የቀረበለት የፌደራል ፖሊስ መልስ በአቶ ጄይላን አንደበት ‹‹መረጃውን ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት አስገብተናል›› በማለት ዝርዝርን ነገር ከመግለጽ ተቆጥበዋል። በዚህ ሁሉ የታጋች ተማሪዎች ወላጆች ሀዘንና እንባ በሚፈራረቅበት ዐውድ ውስጥ ከፌዴራል ፖሊስ ባሻገር የሀገር መከላከያ ‹‹ጉዳዩ እኔን አይመለከትም›› ማለቱ የበርካቶችን አንገት አስደፍቷል።

### መውጫ

ከማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ግፊት የተሻገረው፤ ይህ ኹለት ወራትን ያስቆጠረ የተማሪዎች ዕገታ፣ በታዋቂ ግለሰቦች፣ አክቲቪስቶችና አያሌ ሚዲያዎችም ሽፋን እያገኘ መሄዱ ‹‹መንግሥት›› የተባለው አካል ላይ መልከ ብዙ ጫና እንዲያርፍ አስገድዷል። ይህን ተከትሎ በሠላም ሚኒስትሯ ሙፈሪያት ካሚል መሪነት ከፌደራል ፖሊስ፣ ብሔራዊ ደህንነትና መከላከያ ሰራዊት አባላት ያሉት ዓቢይ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ሥፍራው አቅንቷል። (ይህ መጽሔት ማተሚያ ቤት እስከገባበት ጊዜ ድረስ) በጉዳዩ ላይ የተገኘና ይፋ የተደረገ ውጤት ያልነበረ ሲሆን ድርጊቱንና የመንግሥትን የበዛ ቸልተኝነት በመቃወምም በበርካታ ከተሞች የተቃውሞ ሠልፎች ተካሂዷዋል።

# ሕግ ለወደደው ታጋሽ፣ ለጠላው ተናካሽ አይደለም !

ኢትዮጵያ ዘመናትን ከተሻገሩ አዕማዷ መካከል ሥርዓተ መንግሥቷን ያፀኑ ሕጎቿ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ሺህ ዓመታት ወደ ኋላ በሚመተረው የታሪክ ገመዷ ከፍትሐ ነገሥት እስከ ፍትሐ ብሔር የሚቆጠሩት መዝገቦች ያነበሩት የሕግ ልዕልና በአስረጅነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ከዚህ ዘለግ ካለው የፍትሕና የርትዕ ሥርዓት መነሻነትም ህዝብ ለሕግ የሚሰጠው ዋጋ ግዘፍ ነስቶ ይታያል፡፡ በ“ሕግ አምላክ” እና “አደራ ሴራ” የተሰኙት ተለምዷዊ ተማጽኖዎችም ከዚህ የሚፈልቁ አብነቶች ናቸው፡፡ ነባሩ እውነታ ይኸ ቢሆንም ከንጉሣዊው አገዛዝ ውድቀት በኋላ በተተካው ወታደራዊ መንግሥትም ሆነ  ዛሬን በዋጀው ጠርዘኛ ኃይል ግን ሌላ መልክና ብየና እያስፈለገው ይመስላል፡፡ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችን ባነሱ ዜጎች ላይ ገቢራዊ ሲደረግ  ከቆየው ፍርደ ገምድልነት አንስቶ የፍትሕ ሥርዓቱ በጥቂቶች አዛዥ ናዛዥነት ሥር እስከ መውደቁ ድረስ “ሕግ”  ከሰገነቱ ላይ ተደጋግሞ ሲፈጠፈጥ አይተናል ፤ ታዝበናልም፡፡

በሀገራችን መልከ ብዙ ፖለቲካዊ ጥያቄዎችና ፍላጎቶች ማኅበረ - ፖለቲካዊ ትግሉን ከተቀላቀሉ በኋላ የተወለዱት እንቅስቃሴዎች የህግን ልዕልና አብዝተው የፈተኑ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ የሕወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ህግን “የጠሉትን መምቻ” ለማድረግ የሄደበት ርቀት ደግሞ ዜጎች ከተከበረው ችሎት ፍትሕን እንዳይጠብቁ ገፊ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይኸ ሕግና አዋጅን ታክኮ ንጹኃን ዜጎችን እንባ ሲያራጭ የኖረ ሥርዓት ግን  ጽዋው ሞልቶ በሕዝብ ትግል “በቃህ” ሲባል በኣናቱ የተተካው መንግሥት ደግሞ በዜጎች ለቅሶ የሚነግድ ነውረኛ ሆኖ መከሰቱ “ለውጥ” ለተባለው ሁነት ትልቅ ምጸት ነው፡፡ ድፍን ሁለት ዓመትን ሊያስቆጥር ጥቂት ወራት በቀረው በዚህ የዐቢይ አሕመድ አሥተዳደር፤ በመንጋ በተደራጁ ወጣቶች የደቦ ፍርድ ዜጋ በሀገሩ ላይ ተዘቅዝቆ ተሰቅሏል፤ በኦሪት ዘመን ያለን እስኪመስለን ድረስ ንጹሃን በድንጋይ ተወግረዋል፡፡ ሰማንያ ሰባት ኢትዮጵያውያን በሜንጫ፣ በዱላና በጥይት በአደባባይ ተገድለዋል፡፡ መንግሥት ከነዚህ ሁሉ አስደንጋጭ ሁነቶች በኋላ ታዲያ ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር የሄደበት እርምጃን ለተመለከተ እጅግ አሳዛኝም አስፈሪም ስሜት ውስጥ መግባቱ አይቀርም፡፡ ለግጭቶቹም ሆኑ ዘግናኝ ፍጅቶቹ የወዲያው ምክንያት (immediate cause) እና መሠረታዊ መነሾ (fundamental cause) የሆኑ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ለይቶ ፍትሕን ከማስፈን ይልቅ በቸልታ ያለፈበት ሁናቴ ደግሞ ለዚህ ምስክር ነው፡፡

ሰሞኑን ከኦሮሚያ ክልል የተሰማው ዜናም የዚህ ተቀጥላ ተግባር አንድ አካል ነው፡፡ በምዕራብ ወለጋ ያለፉትን ሃምሳ ያህል ቀናት ታግተው የሚገኙት ሴት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የደረሱበት አለመታወቅ የሁላችንንም ልብ ሰብሯል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ተማሪዎቹ ላይ ለማሰብ የሚከብዱ አደጋዎች የተጋረጠባቸው መሆኑ፣ አገዛዙ ለዜጎች ሕይወት ያለውን ቦታ ደግመን ደጋግመን እንድንመረምር ያስገድደናል፡፡ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን ያለውን የላሸቀ ቁርጠኝነትነትም እንድንታዘብ ዕድል ሰጪ ነው፡፡ መንግሥት ያለፉትን ወደ ሁለት የተጠጉ ዓመታት የታጠቁና “ዱር ተከትተናል” ያሉ አማጺያን ኃይሎች በሚንቀሳቀሱበት የምዕራብ ኢትዮጵያ ክፍል ለሚገኙ ዜጎች አስተማማኝ የደህንነት ከለላ መስጠት አልቻለም፡፡ ይባስ ብሎ ሥፍራው ወደሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚላኩ ተማሪዎችን ሠላምና ደህንነት ማስጠበቅ አቅቶት ይኸ አሳዛኝ ሁነት መፈጠሩ ደግሞ “ፍላጎቱ ምንድ ነው?” እስከሚለው ድረስ እንድንጠይቅ ይገፋናል፡፡

በሀገሪቱ አንዱን ወገን በ “ውሃ ቀጠነ” ሰበብ የማሠርና የማሳደድ አዝማሚያዎች በግልጽ እየታዩ ባለበት፤ በሌላ ወገን ደግሞ ሀገር አለን ብለው ለትምህርት በወጡ ዜጎች ላይ እንዲህ ያለ ዘግናኝ እገታ ሃምሳ ላለፉ ቀናት ሲፈጸም በዝምታ ማለፍ፣ ሕዝብ በመንግሥት ላይ ያለው አመኔታ በእጅጉ እየተሸረሸረ፤  ሕግ ለወደዱት ታጋሽ፣ ለጠሉት ተናካሽ የመሆኑን አሳፋሪ እውነታ ያጸናዋል፡፡ ከዚህ በኋላ “ለምጣዱ ሲባል አይጧ ትለፍ” የሚለውን ከመርህ የተፃረረ ተረት ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ ኢትዮጵያዊ ግን የለም፡፡ ይኽንን አለማወቅም የበዛ ተላላነት ነው፡፡ ከእንግዲህ ሁላችንንም በዜግነታችን የሚያውቀን፣ አውቆም የሚያኖረን መንግሥት እንጂ፤ የፖለቲካ መጠነ ሙቀቱን እየለካ ዥዋዥዌ የሚጫወት አገዛዝ  በኢትዮጵያ ፖለቲካ መድረክ ህልውናው ሊቀጥል የሚችልበት ዕድል መክኗል ፤ አይኖርምም፡፡


**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ
ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ኄኖክ ገለታው

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
አለማየሁ ባዘዘው

**አዘጋ**
ብሩክ መኮንን
ፍቅርተ ተሾመ
ሙሉጌታ አክሊሉ

**አምደኞች**
ተረፈ ወርቁ
ሁሴን ከድር

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 22 76 61
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013



SIRAK Advertising & Printing
+251- 911 50 33 22



በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506

# ንስሃ የራቀው የህወሓት መጨረሻ



ቀጸላ ክፍሌ

‹‹ግንቦት ሃያ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሦስት ዓ.ም›› ይኽ በበርካቶቻችን ስዕለ ኅሊና ውስጥ በሾካካ ጨኽትነቱ መከራችንን ያዋለድንበት የ"ድል አድራጊው" ቡድን የመጀመሪያ ድምጽ ነው። ህወሓት ወያኔ በሙሉ እግሩ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት ዕለት ያስማን መሪር ቃና። በጊዜው ከመጣው አዲስ መንግሥት ጋር ተያይዞ ወግ ነውና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓተ ማኅበር በጨቋኞች መቃብር ላይ ስለመቆሙ "ተበሰረ"። ኢህአፓና የዘመን ተጋሪዎቹ በአደባባይ የረገፉለት የ"ህዝባዊ መንግሥት ይመስረት" ጥያቄ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መመለሱ ተነገረ። ቀላል የማይባሉ ተስፈኞችም አመኑ። ባለባንኩም ባለታንኩም ለመሆን በለስ የቀናው ህወሓት ግን የሚመስሉትን የብሔረሰብ ጭቃ ሹሞች እንደዳቦ ጠፍጥፎ በመስራት "ኢህአዴግ" በሚባል ጭምብል ራሱን አንግሶ ተቀመጠ። በዚህ ልብጥ ማንነቱም ሃያ ሰባት ዓመታቱን የይስሙላ ምርጫ እያካሄደ "ዴሞክራሲያዊነቱ"ን አስመሰከረ። ረብጣ ዶላሮች ከምዕራባውያኑ በእርዳታና ሰብዓዊ መብት ሥም አስፈሰሰ። ዜጎችን እርስ በርስ እያቀራቀሰ ጠፍጥፎ በሰራቸው የብሔረሰብ ወኪሎቹ "እሺ ባይነት" የየክልሉን ሀብት እስኪበቃው አጋፈፈ። የሀገሪቱን ሁሉንም መገናኛ አውታሮች ቀፍድዶ ለሩብ ክፍለ ዘመን ጸረ ኢትዮጵያ ፕሮፖጋንዳውን ሳያሰልስ ነዛ፤ ለፈፈ።

ይህ አፋኝና ዘረኛ ቡድን ምንም እንኳ ያሻውን በማድረግ በሀገሪቱ የፖለቲካ ቁንጮ ላይ ረጅም ዓመታትን መቆየት ቢችልም፤ ጭቆና ያንገሸገሸው ሰፊው የኢትዮጵያ [ወጣት] ህዝብ ግን "ሃምሳና ስድሳ ዓመት" ሊነግስበት ከቋመጠው ዙፋን ገና በግሚሱ ገንድሶ በአርባ አራት ዓመቱ ደደቢት መልሶታል። ይህን ተከትሎም ‹‹ሕዝባዊያን ኃይሎች›› ወደ ሥልጣን ለመምጣት በቅተዋል። ነገር ግን ይህ አርባ ዓመታትን በፖለቲካ ግልሙትና ያሳለፈ ግንባር በሠመመን ሳለ በደረሰበት ዱብ ዕዳ ከንስሃ ይልቅ ነውጥ የየዕለት ግብሩ ሆኖ ሀገሪቷን ሰላም ከመንሳት ለመቆጠብ የፈቀደ አይመስልም። በተለይም በሀገሪቱ በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ (በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ) እየደረሰ ላለው ቀውስ ሚናው ከፍተኛ እንደሆነ ሰሞነኛውን የሳይንስና የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሪፖርት ልብ ማለት ይበቃል። ድርጅቱ ከአፈጣጠሩ ጀምሮ ‹‹ሌሎች›› ያላቸውን በመጥላት ላይ የተመሰረተና የተንሸዋረረ የፖለቲካ መስመርን በመከተል የተካነ መሆኑ በሀገሪቱ ላይ ጥላቻ የፍቅር ያህል እንዲገነን ከማስፋፋቱም በላይ እርሱን የሚያስንቁ ቡድኖችና ድርጅቶች እንዲፈለፈሉ መንገድ ጠርጓል። እነዚህ በአምሳሉ የተሰሩ ‹‹ጥላቻ ወልድ›› ድርጅቶች ታዲያ የፖለቲካ ጥያቄያቸውን የሚጀምሩት ልክ እንደ ጡት አባታቸው ህወሓት ሁሉ የሀገሪቱን የሃገረመንግስት ነባራዊም ሆነ ታሪካዊ ካስማዎችን በመነቅነቅ መሆኑ የዓላማም ሆነ የዒላማ አንድነታቸው ፍንትው እንዲል አስችሏል።

ለአብነትም የሀገሪቱ የህልውና ካስማዎች ተብለው የሚታሰቡትን እንደ ባንዲራ፣ ጥንታዊ የሥነመንግሥትነት ታሪክ፣ ብሔራዊ ጥቅም (የባህር በር/ የቀጠናው ጂኦፖለቲካ) እና መሰል አንገብጋቢ ጉዳዮችን መቃወምና መካድ የትግላቸውም የትርክታቸውን መጀመርያ ነው። በርግጥ ይኽ የተለመደና የተደጋገመ ዕሳቤ ብዙዎች እንደሚያምኑት ሀገር በቀል ሳይሆን ከታሪካዊ ጠላቶቻችንና ከቅኝ ገዥዎች የዘመናት ሴራ የተቀዳ መሆኑ ግልጽ ነው፡ ፡ የራስን የበታችነት ስሜት ለመደበቅ ሲባል በ"ነጻ አውጪነት" ሥም የሚደረግ ሀገር የማፍረስ ተልዕኮ መሆኑም የታወቀ ነው። በሂደቱ እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች የሀገሪቱን የሃገረ መንግሥትነት ታሪክ ወደ መቶ ሃምሳ ዓመት በማውረድ ሊያጣጥሉና ሊዘባበቱበትም ይሞክራሉ። የጉዳዩ ምጸትነት ፍንትው የሚለው ግን ኢትዮጵያውያን በወል መረዳታቸው (Common Understanding) ውስጥ የተቀበሉት የኢትዮጵያ የሦስት ሺህ ዓመታት ሥልጣኔ (አክሱም) ህወሓት ‹‹ተገለልሁበት›› ከሚለው ስሜት የሀገራችን ክፍል የሚነሳ ሆኖ ሳለ በታሪካችን ላይ ቀዳሚ ዘማች ሆኖ መገኘቱ ነው። ‹‹ይህ ቡድን ስለምን በዚህ አፍራሽ የፖለቲካ ፍኖት መንገዝን መረጠ?›› የሚለው ጥያቄ ዛሬም ለብዙዎች ግራ አጋቢ ሆኖ ቀጥሏል። እንደ ህወሓት ተደጋጋሚ ዲስኩር ‹‹የመረረ የብሔር ጭቆና ወለደን›› የሚል ምላሽ ባያጣም ፤ የብዙዎቻችን ዕምነት ግን ቀጣዮቹ ሁለት መላምቶች ላይ ሳያነጣጥር አይቀርም።

## መላምት አንድ፡-

ትግራይ [እንደ መልከዓምድር] ቀዳሚና ነባር የኢትዮጵያ ግዛት ስትሆን ሕዝቡም ለኢትዮጵያ ሃገረ መንግሥት ምስረታ ታሪክ ወሳኝ ሚናን የተጫወተ መሆኑ ይታወቃል፡ ፡ ይህ የማይታበል እውነት የመሆኑን ያህል ግን "ከአብረኪ የወጡ ኃይሎች ስለምን የተገንጣይነት መንፈስ ተጠናወታቸው" ለሚለው ጥያቄ በአካባቢው የፖለቲካ ልሂቅ ዘንድ የተፈጠረው የበታችነትና የመጠቃት ስሜት እንደሚሆን አያጠራጥርም። ለዚህም እንደዓብይ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው የአድዋ ጦርነትን ተከትሎ በአንዳንድ አካባቢዎች የተፈጠረ ዘልማዳዊ "የባንዳነት/ ሀገር ከድነት" ምች ነው። ይህ በሽታ ከመላው ትግራዋይ አንጻር ሲታይ የጥቂቶች መሆኑ በግላጭ ቢታወቅም፣ አንዳንዴ የመሃልና የዳር ፖለቲካው አልገጥም ሲል በሚስጥ ጥራዝ ነጠቅ ፍረጃና ትችት፣ የሚፈጠረው ቅሬታና የመገፋት ስሜት የተጠቀሰውን ችግር አበጅቶ እንዳይሆን ያስጠረጥራል። መነሻው ምንም ይሁን ምን ይኽ የበታችነት ስሜት ግን በተለያየ ጊዜያት በአስካሪነት ከጠላት ጋር ከማበር ዘልሎ በማዕከለ መንግሥቱ ላይ እስከ ማመጽ በደረሰ ሙከራ ተፈትኗል። በራስ ገዝነት ጥያቄ ሰበብ የቀሳራውያን ኃይሎች ፍላጎትን ለመፈጸም እስከ መውተርተርም ተደርሷል(በርግጥ የኤርትራን መነጠል በማየት ዓላማው በከፊል መሳካቱን ማመን ይቻል ይሆናል)። የሁለተኛውን የጣሊያን ወረራ ተከትሎ የተመሰረተው ቀዳማይ ወያኔ ‹‹ዓላማው ምን ነበር? ማንስ አቋቋመው? ምንስ ለዚያ አመጽ አነሳሳው?›› የሚሉት ጥያቄዎችም እንዲሁ ለተነሳንበት ጥያቄ ከሚኖራቸው ትርጉም አንጻር መዘንጋት የሚኖርባቸው አይደሉም።


## መላምት ሁለት፡-

የትግራይ የፖለቲካ ሊሂቃን አሁን ባለው የዘውግ ፌደራላዊ አወቃቀር ባላቸው የብሔረሰብ ቁጥር አነስተኛ መሆን ሳቢያ ሁሉም ላይ አዛዥ ናዛዥ ሆኖ መቆየቱ የማያዋጣ ስሌት መሆኑን ይረዳሉ። ይኽ መረዳታቸው ደግሞ "ደም የገበርንለት ነው" የተባለውን ድል ማንም ኃይል በዴሞክራሲ ሥም እንዳይነጥቃቸው የለየለት አፈናና እመቃ ውስጥ መግባት ምርጫቸው ሆኖ ቆይቷል። ጽዋው ሞልቶ ታሪክ ከተቀየረ በኋላ ግን ህወሓትና ልሂቃኑ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ንዋይና ሥልጣን በኮታቸው ከሚያድለው የሕገ መንግሥቱ ክፍል ይልቅ በራሳቸው አድራጊ ፈጣሪ የሚያደርጋቸው አንቀጽ[39] ላይ ዓይናቸው መፍጠጥ ከጀመረ ሰነባብቷል። በርግጥ ሃሳቡ ለህወሓት ቤት እንግዳ አይደለም። የተጻፈና የተመከረ የዘመናት ውጥን ነው። አስገራሚው እውነታ ግን አጀንዳውን ከማገብት/ተሀሓት አባራ አራግፎ ከአርባ አምስት ዓመት በፊት በነበረ ድምጸት ለማስጮህ የሚደረገው ሙከራ ነው፡ ፡ በዚህ ዙሪያ የክልሉ ሚዲያ ዕለት ከዕለት የሚነዛቸው የጥላቻ ቅስቀሳዎችን ለተመለከተ ትግራይን ደርግ እንጂ ህወሓት እያስተዳደረው ያለ አይመስልም። በጥቅሉ ግን በኢትዮጵያ ፍርስራሽ ላይ ሀገር የመሆን ተምኔት የትግራይ ልሂቃንና የከሰሩ ፖለቲከኞች ህልም ሆኖ እንደተኖረለት ሊረሳ አይገባውም።

በአጠቃላይ የህወሓት መንገድ ሁሌም በደም የጨቀየ ከመሆኑ አንጻር የፌደራል መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ጥብቅ ክትትል ሊያደርግበት ይገባል። በተለይም ደግሞ ሰሞነኛውን በክልሉ እየታየ ያለውን የህዝብ ተቃውሞ ማዕከላዊ መንግስቱ ፌዴራላዊ ሥልጣኑን ሳያዛባ የሕዝቡ ጥያቄ እንዲመለስና ጠያቂው ወገን እንዳይጎዳ ኃላፊነቱን በተጠና መንገድ በመወጣት ለዚያ ታሪክ ሰሪ ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ውለታ ሊውል ይገባል የሚል ዕምነት አለኝ። ያ ካልሆነ ግን በተለይ ህወሓት ራሱን ከእሕት ድርጅቶቹ ከነጠለ ወዲህ እየሄደበት ያለው መንገድ የአጥፊና ጠፊ በመሆኑ እንደ ሀገር ኪሳራችንን እንዳያበዛው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

ምልከታ

# ምርጫው ወደ ነሐሴ የዞረበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል?


መታሰቢያ መልአከህይወት

## መላምት ቁጥር አንድ፡-

እንደሚታወቀው የነሐሴ ወር ክረምቱ የሚጠነክርበትና ወንዞች የሚሞሉበት ከፍተኛ የሆነ ጭቃ የሚኖርበት ወቅት ነው። የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ከቱሪስቶች ጋር እሰራ በነበረበት ወቅት የተመለከትኩት አንድ አስገራሚ ነገር ነበር። ከጎንደር ወደ ደባርቅ ስንጓዝ በመንገዱ መካከል ከሶዬ የምትባል የገጠር መንደር አለች። እዚህ ቦታ ያለው አምባ ከፍታው ከ3800 ሜትር በላይ በመሆኑ በክረምት ወቅት መንደር ሙሉ በሙሉ ከሁለት ወር በላይ በደመና ተሸፍና ነው የምትቆየው ነገር ግን ጥቅጥቅ ያለ ደመናው ከሁለት ደመናና ቅዝቃዜ ቢኖርም ገበሬዎች ሥራቸውን አያቆሙም። የሚያርሰውን በሬ በማያዩበት ሁኔታ የእርሻ ሥራቸውን ያከናውናሉ።

እንዲህ ዓይነት የክረምት ሁኔታ በበርካታ የአገሪቱ ክፍሎች ፈልጎ ማግኘት ይቻላል። ገበሬው በዚህ ወቅት የእርሻ ስራውን ከመሥራት ውጭ ለሌላ ለምንም ጉዳይ ጊዜ አይሰጥም። በመሆኑም በከፍተኛ ደረጃ የኢትዮጵያ አርሶ አደር ወደ ምርጫ ጣቢያ ይመጣል ብሎ ማሰብ የሚቻልበት ሁኔታ የለም። በመሆኑም ምርጫው ካልተካሄደ የዶ/ር ዐቢይ መንግሥት "PLAN B" ብሎ ያዘጋጀው ነገር እስከ አሁን አልተገለፀም።

በእኔ እምነት ሊከሰት የሚችለው ነገር ሁሉም ክልሎች ‹‹በቃ ማዕከላዊ መንግሥት ከአሁን በኋላ ሕገወጥ ስለሆነ ሁላችንም የራሳችንን መንግሥት እንመሰርታለን" የሚሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። የውጭ ኃይሎችም የራሳችንን ደግሞ በተለይ ኢትዮጵያ ፈራርሳ ማየት የሚፈልጉ ኃይሎች ጓዛቸውን ይዘው ወደሚፈልጉት ክልል በመግባት አዲስ መንግሥት እንዲፈጠር በቂ ድጋፍ ለማድረግ የሚሯሯጡ ይመሥለኛል።

## መላምት ቁጥር ኹለት፡-

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ እስከ ሕወሓት ሥልጣን መጨረሻ ድረስ ፈላጭ ቆራጭና ሥልጣኑን ለማስጠበቅ አቅም ያለው መንግሥት የነበራት ሲሆን ፣ በዶክተር ዐቢይ የሚመራው መንግስት ግን በአንጻሩ እጅግ ልፍስፍስና ተደብቀው የራሳቸውን ሰይጣናዊ አጀንዳ ለማፈፀም የሚሯሯጡ ኃይሎችን ያቀፈ መንግሥት በመሆኑ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አንድነት ለማስጠበቅ አቅም ያለው መንግስታዊም ሆነ ወታደራዊ አቅም የለም። በመሆኑም መጪው ጊዜ እጅግ ውስብስብ እንደሚሆን መገመት ሞኝነት አይደለም።

በነሐሴ ወር ምርጫ ለማድረግ ሲሞከር በርካታ ምክንያቶች ምርጫው እንዳይካሄድ እንቅፋት ስለሚሆኑ ይህንን ክስተት አስታኮ "በቃ ምርጫ ማካሄድ አልተቻለም" በማለት አገሪቱ አምባገነናዊ ሥርዓት ውስጥ እንድትገባ የታሰበ ነው ብሎ መውሰድ የሚቻልበት ሁኔታ ይኖራል ብሎ ማሰብም ይቻላል።

## መላምት ቁጥር ሦስት፡-

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በሚቀጥለው ክረምት የዓባይ ግድብን መሙላት ትጀምራለች። በዚህ ምክንያት አገሪቱ ሌላ ተጨማሪ ውጥረት ውስጥ መግባቷ አይቀርም። ታዲያ የ2012ን ምርጫ ከዓባይ ሙሌት ጋር አንድ ላይ እንዲሆን ያብራሩ ሲሆን አሁን የምክር ቤቱ የሥልጣን ዘመን የመጨረሻው ዓመት በመሆኑ ከሰኔ 30 በኋላ ምክር ቤቱ ለአስቸኳይ ጉዳይ እንኳን ሊጠራ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም። በመሆኑም የ2012 ምርጫ ሲደረግ የአገሪቱ ትልቅ የሥልጣን አካል ከሥራ ውጭ ሆኗል ማለት ነው።

በተጨማሪም አንቀጽ 58/3 ላይ እንደተደነገገው የምክር ቤቱ ሥልጣን ሰኔ 30 የሚጠናቀቅ ከሆነ አዲስ የፓርላማ አባል ከአንድ ወር በፊት መመረጥ አለበት። ይኸ ማለት ምርጫው ቢበዛ ከግንቦት 30 ማለፍ የለበትም።

ይህ ማለት አሁን ሊካሄድ የታሰበው የነሐሴ 10 ምርጫ ምንም ዓይነት ሕጋዊ መሠረት የለውም ማለት ነው። በጣም የሚገርመው ወ/ሪት ብርቱካን ይህንን የምርጫ ሰሌዳ ስታሳውቅ በቦታው ተገኝተው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ስለ ሕገ መንግሥት መጣስ ትንፍሽ ያሉት ነገር አለመኖሩ ስለ ሕገ መንግሥቱ በቂ ግንዛቤ እንደሌላቸው ማሳያ ነው።

ሌላው በሕገ መንግሥቱ ላይ የተቀመጠው አስቂኝ አንቀጽ 60/1 ነው። አንቀጹ ‹‹ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በምክር ቤቱ ፍቃድ ምክር ቤቱ እንዲበተን ለማድረግ ይችላል›› ይላል። እስቲ ተመልከቱ በምን ተዓምር ነው የምክር ቤት አባላት "በትኑን" ብለው ለጠ/ሚኒስትሩ አቤቱታ የሚያቀርቡት?!

በእኔ ዕይታ በአሁኑ ወቅት የዶ/ር ዐቢይ መንግሥት በአምስት አቅጣጫና ገመድ ተወጥሯል። አንደኛው ውጥረት በዶ/ር ዐቢይ ዙሪያ የተሰለፉት ጽንፈኛ ኦሮሞዎች ዶክተሩን አላላውስ ብለው ወጥረው ይዘዋቸዋል። በተጨማሪም ዶ/ር ዐቢይ እነዚህን ስብስቦች ላለማስቀየም እየሰሩ ነው። ሁለተኛው ውጥረት መቀሌ የመሸገው ኃይል በተጠናከረ መንገድ ዶክተር ዐቢይ እንደፈለጉ እንዳይንቀሳቀሱ እያደረገ ነው። ሦስተኛው ውጥረት የአንድነት ኃይሉ በየራሱ መንገድ ዶ/ር ዐቢይ ለአንድነት ብቻ እንዲሰሩ ተፅዕኖ እየፈጠረ ነው። አራተኛው ውጥረት ዶ/ር ዐቢይ በየቀኑ የሚቀርብላቸው በኢኮኖሚው ላይ ያለ ችግር፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ፈተና ነው። በአምስተኛ ደረጃ ደግሞ ከፍተኛ ገንዘብ መድበው የራሳቸውን ፍላጎት ለማስፈፀም የሚጥሩ የውጭ ኃይሎች በዶ/ር ዐቢይ ላይ እያሳደሩ ያሉት ተጽዕኖ በራሱ ትልቅ ተግዳሮት ነው።

ታዲያ አንድ መሪ ይህ ሁሉ ውጥረት ውስጥ ሆኖ አገር መምራት እንዴት ይቻላል? ዶ/ር ዐቢይ ቢያንስ የተወሰኑትን ችግሮች ፈተና እንዳይሆኑባቸው እስከ አሁን ባለው ጊዜ ተግተው በመሥራት ሊቀርፏቸው ይገቡ ነበር።

ምርጫው ሲደርስ ደግሞ ሌሎች ፈተናዎች መጨመራቸው አይቀርም። አገር ከፈራረሰች ደግሞ እንኳን የብሔር አጀንዳ ለማስፈፀም የመኖር ሕልውናንም ማስጠበቅ አይቻልም። ከላይ እንደተጠቀሰው በነሐሴ ሊደረግ የታሰበው ምርጫ በራሱ ከፍተኛ የሕግ ጥሠት ሲሆን ዶ/ር ዐቢይ ኢህአዴግን አፍርሰው ብልፅግና ፓርቲን ሲመሠርቱ ከሄዱበት አካሄድ በምንም መልኩ አይለይም።

በመጀመሪያ ኢህአዴግ ተመርጦ የስልጣን ዘመኑን ሳያጠናቅቅ ማፍረስ ሕገ ወጥነት ነው። ሲቀጥል ኢህአዴግ ፈርሶ ብልፅግና ሲመሠረት የኢህአዴግን ዙፋንና ሐብት መውረሱ ትክክል የሚሆነው በንጉሳዊ እንጂ ዴሞክራሲን እከተላለሁ በሚል ሥርዓት አይደለም።

ምክንያቱም ሥልጣን በምርጫ ካርድ እንጂ ከአባት ወደ ልጅ እንደሚተላለፍ ርስት አይደለም። የኢህአዴግ ገንዘብም ንብረትም ኢህአዴግ ሲፈርስ ለገንዘብ ሚንስትር ነበር ገቢ መደረግ የነበረበት።

ኢህአዴግ በሆነ ምክንያት የሥልጣን ዘመኑን ሳያጠናቅቅ ቢፈርስ ሕጉ ባስቀመጠው መሠረት አገሪቱ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ውስጥ ሆና እስከ ሚቀጥለው ምርጫ መቆየት ነበረበት። ከላይ የተጠቀሱት መሠረታዊ የሕግ ጥሰቶች አገሪቷን ለማፍረስ ለሚፈልጉ ኃይሎች እጅግ ሰፊ ዕድል ይሰጣቸዋል።

የንጉሱን ሥርዓት ታግለን የጣልነው ዋናው ምክንያት ሥልጣን በውርስ ሳይሆን በብቃት፣ በጉልበት ሳይሆን በዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲገኝ ለማስቻል ነው። በተጨማሪም የሚቀጥለው ምርጫ ምናልባት ከተካሄደ አሁን በሥልጣን ላይ ያሉ ኃይሎች ምርጫው ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸው አይቀርም። በሌላ አነጋገር ተመልሰን ወደነበርንበት ብልሹ ሥርዓት እንገነባለን ማለት ነው።

አሁን ደግሞ የሕዝቦች ብሶት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰ በመሆኑ አስከፊ ሁነት በማንኛውም ወቅት ሊከሰት ይችላል። በመሆኑም ቢያንስ የዶ/ር ዐቢይ መንግሥት እራሱ የፃፈውን ሕገ መንግሥት እንኳን ቢያከብር መልካም ነው። እኛ "ሕገ መንግሥቱ ይታረም" ስንል ድምፃችንን እያሰማን፣ እንኳንስ ልታርሙት ያለውና ሕግ እየጣሳችሁ አገሪቷን ወደ ከፋ አቅጣጫ እየወሰዳችኋት መሆኑ አሳዛኝ ነው።

በአጠቃላይ የሚቀጥለው ምርጫ፤ የአየሩ ሁኔታ አመቺ አለመሆን፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በብዙ ጉዳዮች መግባባት ላይ አለመድረሳችን፣ የተካሄዱ የሕግ ጥሰቶች በመኖራቸው፣ ጽንፍ የረገጡ አስተሳሰቦች በመበራከታቸው፣ የውጭ ኃይሎች አጀንዳቸውን ለማስፈፀም የሚያደርጉት ሩጫ መብዛት፣ ወዘተ… ምክንያቶች ሊሳካ እንደማይችል በእርግጠኝነት ቀድሞ መናገር ይቻላል። ድንኳን ሲወጠር ቤት ይሆናል።

አገር ግን ስትወጣጠር ለዜጎችዋ ሲያል ነው የምትሆነው። በመሆኑም ከስሜታዊነት ወጥተን ረጋ ብለን ብናስብ ለሀገር የሚበጅ መንገድ ማግኘት ይቻላል እላለሁ።


## አንደበት

"በአሁኑ ወቅት አገሪቷ ላይ ያለው የሃይል አሰላለፍ ምን ይመስላል? እነማን ናቸው ከፍተኛ ሕዝብ አንቀሳቅሰው ምርጫው እንዲራዘምም እንዳይራዘምም የማድረግ ፖለቲካ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችሉት? የሚለው መታየት ያለበት ይመስለኛል፡፡ ምርጫው ሕግንም ቢሆን ሽሮ መሸጋገር አለበት የሚሉት ጥቂት ናቸው፡ ፡ በስምም ይታወቃሉ፡፡ እነ አቶ ልደቱ... እነ ኢንጅነር ይልቃል ናቸው፡፡ ከእነሱ ውጪ ያለው ሀይል፣ ምርጫው እንዲካሄድ የሚፈልግ ነው፡፡ በተለይ የኦሮሞ የፖለቲካ ሀይሎችና ህወሃትን የመሳሰሉት ምርጫው በጊዜው ይካሄድ እያሉ እየወተወቱ ነው፡፡ እነዚህ ሀይሎች ብዙ ህዝብ እናንቀሳቅሳለን ብለው የሚያስቡ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ምርጫው ሕግንም ቢሆን ሽሮ ይራዘም የሚሉት ደግሞ ብዙም እንቅስቃሴ የሌላቸው፣ የምርጫ ወረዳቸው በጣም ውስን የሆኑ ሀይሎች ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የትኛው ድምፅ ነው የበለጠ ሊሰማ የሚችለው? የሚለውን ማየት ይገባል"



**ዮናታን ተስፋዬ(የፖለቲካ ተንታኝና አክቲቪስት)**
**አዲስ አድማስ ጋዜጣ ጥር 16 ቀን 2012 ዓ.ም**

"ይህ ሁኔታ ከምን ክስተት ጋር ተዛምዶ እንደነበር ለመመልከት፣ እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ የአፍሪካ አገሮች ከአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ነፃ በወጡ ጊዜ፣ አፍሪካ ምንም ቢደረግ የማያልፍለት አህጉር ነው የሚል ሥነ ልቦናዊ ዘመቻ ይካሄድ ነበር፡፡ አፍሪካ የራሱን ፖሊሲ በራሱ መቅረፅ እስካልቻለ ድረስ እውነትም አያልፍለትም፡፡ እስከ ዛሬም ድረስ በርካታ የአፍሪካ አገሮች ይህንን ማድረግ አልቻሉም፡፡ ኢትዮጵያ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ዕድሉ ነበራት፡፡ አሁን ግን በውጪ ተፅዕኖ መረብ ወስጥ ገብታለች፡፡ ... ቅኝ የተገዙ አፍሪካውያንንም ሆኑ ሌሎችን አገሮች ለመያዝ እንደ ድሮው ጦር ማዝመትና አገሩን መቆጣጠር እንደማያስፈልግ፣ ይልቁንም የተማረውን ኃይል በመጠቀም በእጅ አዙር የኢኮኖሚና የሌላውንም ፖሊሲ እንደ እንግሊዝ ፍላጎትና ጥቅም እንዲቀርፅ ማድረግ ስለሚቻልበት መንገድ ጽፎ ነበር፡፡ በአጭሩ በአገራችን አሁን ያለው አካሄድ ይሄ አይነቱ ጥላ ያንዣበበት ነው፡ ፡ ፖሊሲዎቻችን በእኛ መንገድና በእኛ አመለካከት መቀረጽ አለባቸው፡፡ በአዲሱ መጽሐፌም እንደ ጠቀስኩት፣ የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት በሰፊው ይታያል"



**ደምስ ጫንያለው (ዶ/ር) የኢኮኖሚ ባለሙያ**
**ሪፖርተር ጋዜጣ ጥር 17 ቀን 2012 ዓ.ም**

"ባልተለመደ ሁኔታ በሀገራችን ሆኖ በማያውቅ መልኩ ኢትዮጵያውን ታግተው ከሀምሳ ቀን በላይ ድምፃቸው ሲጠፋ እናቶች ሲያለቅሱ ዶክተር ዐቢይ የት ነው ያሉት?" በሌላ በተለያየ ምክንያት በየጊዜው እየወጡ የሚነግሩን ጠቅላይ ሚኒስትር በዚህ ጉዳይ ላይ ምነው እንደ ሌላው ጊዜ በዚህ ጉዳይ መረር ያለ ቆፍጠን ያለ መግለጫስ መስጠት ተሳናችሁ? ለውጡ ሲመጠና ስትነግሩን የጥላቻ መሠረት በውጪ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ድልድዩን ለመገንባት የሚያስችል ሁሉንም ነገር አቅርበናል፡፡ ዛሬ ግን በአንድ በኩል የጥላቻ ግንብ እየተገነባ፣ በሌላ በኩል እናንተ የምትሉንን ፍቅር ስብከት እያደመጥን አገራችን ወደላስፈላጊ ጠርዝ እየተገፋች መሆኑን እናውቃለን"



**አርቲስትና አክቲቪስት ታማኝ በየነ በማኅበራዊ ሚዲያ**

"ውድ ወዳጆቼና አድናቂዎቼ እባካችሁ ጌታን ደጋግማችሁ አመስግኑልኝ፡፡ ቃላትም አነሰኝ፣ ምን ልሁን? እግዚአብሔር ዘንድሮ አጠገቤ እጁን ይዞ እያሻገረኝ ነው፡፡ የማታ እንጀራዬን አራሰው፣ እኔ ምንም ንብረት በሀገሬ የሌለኝ ሴት ነኝ፡፡ ዕድሜን ሙሉ በስደት ጥበብ ስል ለልጆቼ እንኳን ምንም ሳልተው የኖርኩ ሰው ነኝ፡፡ አሁየ በናሁ ቴቪ ባለቤት አማካይነት የ10 ሚሊዮን ብር ቤት ተሸለምኩ፡፡ የእናንተም ደስታና ድል ነው፡፡ ለፈጣሪ ምን ይከፈላል? ወዳጆቼ እየዘመራችሁ፣ እየጮሃችሁ አመስግኑልኝ፡ ፡ ሀሌሉያ! ክብሩን እግዚአብሔር ይውሰድ! ውድ አቶ ቴዎድሮስ ስለ ስጦታህ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ እግዚአብሄር ይስጥልኝ! ፈጣሪ ጤናህን፣ ፀጋህን፣ ሰላምህን ያብዛልህ! ይህ ስጦታ ለእኔ ይሁን እንጂ የሚለው የሙያ መመህራኖቼና ጓደኞቼ የሙያ ድካም፣ ውጤት ነው"

**አርቲስት ዓለምፀሐይ ወዳጆ**

## ግጥም

### የተካደ ትውልድ

የተካደ ትውልድ
አይዞህ ባይ የሌለው
ታዳጊ የሌለው
ወይ ጠባቂ መላክ፣ ወይ አበጀ በለው
ደርሶ ከቀንበሩ የማይገላግለው፣

የተካደ ትውልድ
አብዝቶ የያመ፣ ተግቶ የፀለየ
ጥቂት መና ሳይሆን፣ ጥይት ሲያዘንብ ያየ
እድሜ ይፍታህ ተብሎ፣ የተወለደ ለት
አምባሩ ካቴና፣ ማተቡ ሰንሰለት
ምቾትን የማያውቅ፣ ረፍት የተቀማ
አልጋው ያጋም እሾኅ፣ መኝታው የሳማ፣

የተካደ ትውልድ
ሞቶ እንኳን ሬሳው፣ አይላላለት ቀንበር
በዘብ እጅ ተገድሎ፣ በሹም የሚቀበር
ከጡት አስጥል በላይ፣ ኑሮ የመረረው
እንዳይሄድ ጎዳናው፣ የተደናገረው
ድል ያልሰመረለት፣ ትግል ሳይስቸግረው፣

የተካደ ትውልድ፣ በሥጋ በነፍሱ
በቀልቡ በገላው
ኧረ ምንድን ይሆን?
ምንድን ይሆን መላው?
የማለዳ ድባብ በእውቀቱ ስዩም


## አባባል

- መዋሸት እውነታው እንዳይታወቅ ሳይሆን እንዲዘገይ ብቻ ነው የሚያደርገው፡፡
- የምታየው ለማየት የምፈልገውንና የመረጥኩትን ብቻ ነው፡፡ ከፊትህ ጀርባ ብዙ የማታውቀው ነገር አለ፡፡
- ስለ ትልልቅ ነገሮች ከማውራት ይልቅ ትንንሽ ነገሮችን መረዳት መጀመር በራሱ የብስለት ምልክት ነው፡፡
- ጨለማው አትፍራ፣ ከዋክብቱን የምታየው ሲጨልም ነውና!
- በአምላክህ ላይ ተስፋ አትቁረጥ፣ እሱ በአንተ ላይ ተስፋ አልቆረጠምና፡፡
- አንድ ሰው በቀን 4 ጊዜ፣ በዓመት ደግሞ 1,460 ጊዜ ... በአጠቃላይ 60 ዓመት እስኪሞላው ድረስም 88,000 ጊዜ ይዋሻል፡፡ ከዚህ ውስጥም በጣም የተለመደው ውሸት "ደህና ነኝ" የሚል ነው፡፡

## ቶማስ ኤዲሰን

ቶማስ ኤዲሰን (ከ1847 - 1931) አሜሪካዊ የፈጠራ ሰውና ነጋዴ ሲሆን በዘመናዊ ህይወት ውስጥ በርካታ ቁልፍ የሆኑ የፈጠራ ሥራዎችን የፈጠረ ሰው ነው፡፡ የኤዲሰን የኤሌክትሪክ ኩባንያ ለዲሲ ነዋሪዎች ቀጥታ የኤሌክትሪክ አቅርቦት በማቅረብ ቀዳሚው ነው፡ ፡ ከ1000 በላይ ለሚሆኑ የተለያዩ ፈጠራዎች የአዕምሮ ፈጠራ መብት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ በተለይም በመላው አሜሪካ ለሚገኙ ቤቶች የቴክኖሎጂ ፈጠራዎቹን በዝቅተኛ ዋጋ አቅርቧል፡፡ ጠቃሚ ከሆኑ ፈጠራዎቹ መካከል የኤሌክትሪክ አምፖል፣ ፎቶግራፍ፣ ተንቀሳቃሽ ምስል ካሜራ፣ የኤሌክትሪክ መኪናና የኤሌክትሪክ ኃይል ዝርጋታ ይጠቀሳሉ፡፡ መደበኛ ትምህርት የተማረው ለሶስት ወር ብቻ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ጥያቄና የአስተማሪዎቹን መመርያ ስለማይቀበል መምህራኑ ይናደዱበት ነበር፡፡ በትምህርት ቤት ደስተኛ አልነበረም፣ አብዛኛውን ትምህርት ያገኘው ራሱን በማስተማር በንባብ ነው፡፡ በቤተመጽሐፍት ውስጥ ያሉትን መጽሐፍት ያነብብ ነበር፡፡ በወጣትነቱ በርካታ ያልተለመዱ ስራዎች በመስራት ሕይወቱን ይደግፍ ነበር፡፡ ከሥራዎቹ መካከል ከረሜላ፣ አትክልትና ጋዜጣ መሸጥ ይጠቀሳሉ፡ ፡ ኤዲሰን የመጀመርያ ባለቤቱ ሜሪ ስቴልዌል መየምትባል ሲሆን በ1884 ከሞተች በኋላ፣ ወደ ዌስት ኦሬንጅ ኒውጀርሲ በማምራት ከሚና ሚለሪን በ1886 ትዳር ሊመሰርት ችሏል፡፡ ሶስት ወንድና ሶስት ሴት ልጆችን ትዳር ዘመኑ ያፈራው ቶማስ ኤዲሰን ጥቅምት 19/1931 በስኳር በሽታ ህይወቱ ሊያልፍ ችሏል፡፡

# በሕዳጣን መብትና ህልውና ላይ የቆመው የዘውግ ፖለቲካ



በኮኪ አቤሴሎም

በአሁኑ ሰዓት የዐቢይ አስተዳደር ከሁሉ በፊት ቅድሚያ ሰጥቶ ሊሰራው የሚገባ አንገብጋቢ ስራ ቢኖር ፣ ጠንካራ የመገናኛ ብዙኃን ተቋም መገንባትና ውጤታማ የህዝብ ግንኙነት ስልት መቀየስ ናቸው። መንግሥት የተሳለጠ መረጃ አቅርቦት ስልትን አለመከተሉ፣ አፍራሽና ችግር ፈጣሪ አክቲቪስቶች የፓሊሲ ውይይቱን እንዲቃኙት፣ እንዲመሩትና ብሎም እንዲቆጣጠሩት መንገድ ከፍቷል። የእነዚህ ክፍሎች ትርክትም በዋናነት መገናኛ ብዙኃኑን በዋናነት የተቆጣጠረ አጀንዳ እንዲሆን አድርጓል። እነዚህ አፍራሽ አክቲቪስቶች ዓላማቸውን ለማሳካት በፍጹማዊ ታታሪነት፣ ጉልበትና ብቃት ማህበራዊ መገናኛውን ሲናኙበት አስተውለናል። የሚያሳዝነው መንግስት ራሱ በበላይነት ሊቆጣጠረው እና ሊመራው ሰፊ ዕድል የነበረውን መድረክ በዝምታ አስረክቦ የተከላካይነትን ሚና ሲጫወት መስተዋሉ ነው። ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ፣ የአንድነት ኃይሎች (ብልጽግና፣ ኢዜማ ...) ፣ የአገራችን ፖለቲካ ኃይላት አሰላለፍ በግርድፉ "አሃዳውያን vs ፌደራሊስቶች" ጋር እሚያደርጉት ትግል እንደሆነ በዘውጌ ፖለቲከኞች ሆን ተብሎ ከተሰመረው ገዳቢ ምደባ ውስጥ መዳከር ወጥተው፣ የትርክቱን አቅጣጫ የዜጋ ፖለቲካን ጽንሰ-ሐሳብ ከመተንተንና ማስረጽ አንጻር በመቃኘት መንቀሳቀስ ይገባቸዋል።

የዚህ ጽሁፍ ዓላማም በዋነኛነት "ፌደራሊስት ወይስ አሀዳዊ" የሚለውንና በዋናነት በኦሮሞና ትግሬ ዘውጌዎች የተቀመረውን ፖለቲካዊ ሙግት ወደ "ለህዳጣን ኅሳዎች ፍትሐዊ እና አቅም ፈጣሪ የሆነ ፌደራላዊ አስተዳደር ወይስ የህዳጣኑን ጥቅም ጨፍላቂ የሆነ ፌደራላዊ አስተዳደር" ወደሚል የውይይት መድረክ ማሸጋገር ነው። ይህ ደግሞ የአሮሞና ትግሬ ጎሰኛ የፖለቲካ ሀይላት ሀሳዊ ትርክትን ራቁቱን በማስቀረት፣ ድብቁን ዓላማ፣ ማለትም በሌላው ጎሳ ዳፋ ራሳቸውን ለማፈርጠም የሚያደርጉትን ዘመቻ ይፋ ያወጣዋል። ወደ ዋናው ጉዳይ ከመግባቴ በፊት ሁለት ማሳሰቢያዎችን ላስቀምጥ። "ብሔር" ከሚለው ስያሜ ይልቅ "ጎሳ"፣ እንዲሁም "ክልል" ከማለት ይልቅ "የጎሳ ግዛቶች" የሚሉትን ስያሜዎች ለምን እንደምጠቀም በማብራራት ልጀምር።

አንደኛ፣ የብሔር/ዘር ፖለቲካ ሲበሰብስ፣ እጅግ ኋላ ቀር ወደሆነ ጎሳዊ አስተሳሰብ ይወርዳል። ይህም ሲባል ፍጹም ኋላ ቀር የሆነውን የጥንታዊ ሰው ጎሳዊ ማንነትና መስተጋብር ያንጸባርቃል። እውነቱን ለመናገር ከብሔር ወርደን ወደ ጎሳ አስተሳሰብ ከገባን ቆየን። በአሁኑ ሰዓት ፍጹም ጎሳ-መር ወደ ሆነ ሀገረ መንግስት የመዘቀጥ አፋፍ ላይ ነው የምንገኘ ። ለዚህም አንዱ አስረጅ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ወደ ኋላ-ቀር ጎሰኞች ዋሻ ተቀይረው ደም የተጠሙ ጎሰኞች መጫወቻ መሆናቸው ነው። ሁለተኛ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ ጎሳ ፖለቲካ በኦሮሞ፣ አማራ፣ ሶማሌና ትግራይ ጎሳዊ ኃይላት ፍላጎትና ስሜት የሚበየን ሆኗል። ትኩረቴን በዋናነት በኦሮሞና ትግሬ ፖለቲካ ኃይላት ላይ ይሆናል። የአማራን ጎሰኛ ፖለቲካ ማንሳት አያስፈልገንም ምክንያቱም በአሁኑ ሰዓት ከማንኛውም ህዳጣን ጎሳ የተሻለ የተጽዕኖ ፈጣሪነት ሚና ሊጫወት የሚችልበት አቅም ላይ አይደለም። የሶማሌንም እንዲሁ አላነሳም ምክንያቱም ራሱን ከጎሳ ፖለቲካ መንቻካ ጥልፍልፍ እያላቀቀ በመሆኑ።

ለኋላ ቀሩ ጎሳዊ ስሜታችን መጋጋል ቁልፉን ሚና የሚጫወተው፣ ከጅምሩ የትግራይን የበላይነት ለማስጠበቅ ሲባል ተወላግዶ የተነደፈውና በውጤቱ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ህልውና አፍርሶ ለኦነግና ኦነጋዊ አስተሳሰብ አራማጅ ኦሮሞ ልሂቃን አሳልፎ የሰጠው ሕገ-መንግሥት ነው። የትግራይ ጎሰኞች ህገ-መንግስቱ ውስጥ የሰነቀሯቸው አንቀጾች፣ የኢትዮጵያ ህልውና በኦሮሞ ጎሰኞች ፍላጎት እንዲወሰን የሚያስችል ህጋዊ ማዕቀፍን ፈጥሯል።

## የኢትዮጵያ የጎሳ ፌደሬሽን ችግር ምንድነው?

እስኪ ከህንድና ከአሜሪካ ጋር እያነጻጸርን እንየው፣ ሁለቱም ፌደራላዊ አስተዳደርን የሚከተሉ ሀገሮች ናችው። በአሜሪካ ህገ-መንግስት መሰረት ግዛቶቿ የሀገረ-መንግስቱን ህልውና ለጥያቄ የሚያቀርቡበት/ማፍረስ የሚችሉበት ቀዳዳ የለውም። ህንድ ደግሞ ግዛቶቹን የፌደራል መንግስቱ ሊያፈርስ፣ ሁለት ሶስት አድርጎ መልሶ ሊያዋቅር ወይ ብዙዎቹን ወደ አንድ ሊሰበስብ ወዘተ .. .ስልጣን ያለው ሲሆን የሀገረ-መንግስቱ ህልውና ግን ለድርድር አይቀርብም። ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ግን ተቃራኒውን ነው የምናየው። በአንቀጽ 39 መሰረት የኢትዮጵያን ሀገረ መንግስት ግዛቶቹ ካልፈለጉ ሊያፈርሱት ይችላሉ። የኦነግ ዘመናትን የተሻገረው ኢትዮጵያን አፈራርሶ በፍርስራሹ ኦሮሚያ የምትባል ሀገረ-መንግስት መመስረት ወይም በኦሮሞ ቁጥጥር ስር የምትተዳደር ኢትዮጵያን ለመፍጠር በዚህ ህገ-መንግስት መሰረት ተቋማዊ እውቅና ተሰጥቶቷል።

በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 8 ቁጥር 1 እንዲህ የሚል ነገር ሰፍሮ እናገኛለን። "የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች ናቸው" በመቀጠል ቁጥር 2 ላይ "ይህ ህገ-መንግስት የሉዓላዊነታቸው መገለጫ ነው" ይላል ነገር ግን የሀገረ-መንግስቱ ሉዓላዊነት ተጽፎ አናገኝም። በነገራችን ላይ በዓለም ላይ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ብቻ ነው የአንድን ሀገር ህዝብ "ህዝቦች" ብሎ የሚገልጸው። "ህዝቦች" የሚለው ቃል በህገ-መንግስቱ ሰነድ ላይ ከዘጠና ጊዜ በላይ ተደጋግሞ ይገኛል። ይሄ እንግዲህ ኢትዮጵያ የተለያየ ዜግነት ወይም ንዑስ ዜግነት ያላቸው ህዝቦች ስብስብስ ነች ለማለት እንዲያመች መሆኑ ነው። ከኢትዮጵያ ውጭ ባለ የተቀረው ዓለም ግዛቶች፣ ክልሎች፣ ክፍለ ሀገሮች፣ የዘር ከባቢዎች ወዘተ በአንድ ሀገር ውስጥ ይኖራሉ፣ እንደየአስተዳደሩ ቅርጽ የሉዓላዊነት ባለቤት የሚሆኑት እንደ አገሪቷ ዜጋ እንጂ እንደ ጎሳ፣ ብሔረሰብ ወይም ህዝብ አይደለም። እያንዳንዱ የህዝብ መብት ወይም ስልጣን የሚቀዳው ከዜጋዊ ማንነቱ ነው። የኢትዮጵያ ግን በዘጠኝ ሉዓላዊ የጎሳ ግዛቶች የተከፋፈለ ግብስብስ ህላዌ ውስጥ የምትገኝ ሀገር ነች። እንደ ሀገር፣ ኢትዮጵያ የማይደፈር ሉዓላዊ ማንነትም ይሁን ሊያፈራርሳት ከሚፈልግ ጎሳዊ ኃይል የሚጠብቃት ህገ-መንግስት የላትም።

ለምሳሌ የኦሮሞ ጎሳ ኢትዮጵያን ማፍረስ ይችላል። ህገ-መንግስቱ የህዝቦችን ሉዓላዊነት የሚያንጸባርቅ ነውና። ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል እንይ እስኪ። እንበል እና አንቀጽ 39 ባጎናጸፈው መብት መሰረት የኦሮሞ ግዛት እገነጠላለሁ ብሎ ቢነሳ፣ ጋምቤላንና የደቡብ ክልል ህዝቦችን በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጣቸው ምክንያት ከተቀረው ኢትዮጵያ የግድ ይነጥላቸዋል። ይህ ለኦሮሞ ጎሰኞች በዓይነቱ ልዩ የሆነ የመደራደር አቅም ይፈጥራል፤ ይህም የአገሪቷን ዋና ከተማ ጨምሮ ለመገንጠል በሚኖራቸው መብት ብቻ ሳይሆን መገንጠሉ ሁለት ሌሎች ክልሎች ከተቀረው አገሪቷ መነጠል የሚችል ክስተት በመሆኑ ነው። የኦሮሞ ጎሰኞች ከኢትዮጵያ መገንጠል ቢወስኑ፣ ስራ ላይ ባለው ህገ-መንግስት መሰረት ጋምቤላና ደቡብን እንደ መደራደሪያ አድርገው መያዝ የሚችሉበት እድል ተፈጥሮላቸዋል። የደቡብ ክልል ህዝቦችም ሆነ ጋምቤላ እንደ አገር ሊያቆማቸው የሚችል የኢኮኖሚ መሰረት ስለሌላቸው፣ በኦሮሚያ መገንጠል ምክንያት ከእናት ምድራቸው በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ምክንያት ከተለዩ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ የሚሆነው ከኦሮሞ ጋር በፌደሬሽን ወይም በኮንፌደሬሽን ተሳስሮ መቀጠል ይሆናል።

የትግራይ ጎሰኞች "የብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠልን" ሲያጸድቁ እንደ እንጀራ እናት ጡጦ በባዶው ኦነግን ለመደለል እንጂ መቼም በተግባር ሊተረጎም አይችልም በሚል ታሳቢ ነው። ሆኖም ግን የትህነግ ከሥልጣን መወገድ፣ የፖለቲካ ምህዳሩ ዴሞክራሲያዊ መሆን፣ እንዲሁም አሁን ያለው አመራር ህገ-መንግስቱን ሙሉ በሙሉ ማክበሩ፣ ለኦነግና መሰል ርዕይ አራማጆች የህዳጣን ጎሳዎችን መደራደሪያ የሚያደርጉበትን አቅም ፈጥሮላቸዋል። የኦሮሞ ጎሳ ኃይሎች፣ የብሔር ህገመንግስቱ ተሻሽሎ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በሚያስመልስበት መልኩ እንደገና ይቃኝ ቢባል፣ ህገ-መንግስታዊ መብታቸውን በመጠቀም ውድቅ እንደሚያደርጉት ለመናገር ማንም አይቀድማቸውም። ጎሰኞች የኢትዮጵያዊነትን ጽንሰ-ሐሳብ የሚቀበሉት ሉዓላዊነት ከአገር ተገፎ ሙሉ በሙሉ ለጎሳዎች በሚቀነበብበት አግባብ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ይበልጥ ግልጽ ▶

የሚሆነው ጀዋር መሐመድ “ህብረ ብሔራዊ ፌደራሊዝም በአሁኑ ህገ-መንግስት በተጻፈው መሰረት ጸንቶ የሚቆይ ነው፤ እንኳን ለድርድር ሊቀርብ ቀርቶ ለውይይት እንኳ የሚታሰብ አይሆንም ፣ በእንዲህ ዓይነት ህልም የተሳከረ ማንኛውም ኃይል ከቁም ቅዠቱ መንቃት ይኖርበታል” ሲል የተናገረውን ስናስተውል ነው፡፡ እንደ ጃዋር አገላለጽ ከሆነ እንግዲህ የኦሮሞ ጎሳ ክልል ሉዓላዊነት መቼም ቢሆን ሊገሰስ የማይችል ሁነት ነው፣ ምንም እንኳ የመገንጠሉን መብት ማክበሩ በደቡብ እና ጋምቤላ ጎሳዊ መሬት ላይ የሚኖሩ ህዝቦችን ህገ-መንግስታዊ መብት የሚጥስ ቢሆንም፣ ይህም ሲባል ከእናት ምድራችው ኢትዮጵያ መነጠልን ለማለት ነው፡፡

“የአንድ ሰው ህገ-መንግስታዊ መብት የሚያልቀው የሌላኛው ሰው የሚጀምርበት ቦታ ነው” የሚለው የተለመደ ብሂል ቅቡል ነው ካልን፣ በኦሮሞ ጎሳ ምድር የሰፈረው ነዋሪ በጋምቤላና ደቡብ ጎሳዎች ምድር የሚገኘውን ነዋሪ መብት የመጣስ ህገ-መንግስታዊ መብት ሊኖረው የሚችልበት አመክንዮ በመሰረቱ መኖር የለበትም ማለት ነው፡፡ አሳዛኙ ነገር፣ ይህ ሙግት በዛሬው የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት መሰረት ተቀባይነት አይኖረውም፣ ምክንያቱም በዚህ ህገ-መንግስት አገሪቱም ይሁን ዜጎቿ ሉዓላዊ ህልውና የላቸውም፡፡ ችግሩን ለመፍታት ሦስት አማራጮች አሉን፡፡

ሀ) የመጀመሪያው “የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል” የሚለውን አንቀጽ መሰረዝ ነው፡፡ ነገር ግን ማንኛውም የኦሮሞም ይሁን የትግሬ ጎሰኛ ይህን መቀበል አይፈልግም፡፡ ህገ-መንግስቱም ይህን የሚያስፈጽሙበት ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት ሰጥቷቸዋል፡፡ በተለይ የኦሮሞ ልሂቃን አቋም ለመረዳት የሚከብድ ነው፡፡ በየትኛውም አገር በብዛት ትልቁ ጎሳ መገንጠልን እንደማታገያ ስልት ይጠቀማል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ አንቀጽ 39 የጎሳ ግዛቶችን ከፌደራል መንግስቱ ተጽዕኖ፣ መስፋፋት ወዘተ የሚጠብቅ የመጨረሻው መተማመኛ እንደሆነ ይሰብካሉ፡፡ ዋናኛው ምክንያታቸው ግን በህገ-መንግስት የተረጋገጠላቸው፣ በመልክዓ-ምድራዊ ሁኔታ የተመቻቸላቸው የማስገደጃ ስልት እንደሆነ መገንዘባቸው ነው ፡፡

ለ) ሁለተኛው የጉዳቱን መጠን መቀነስ ነው፡፡ ይኸውም የጎሳ ግዛቶችን፣ የትኛውም ጎሳ ድንገት መነጠል ቢፈልግ፣ የተቀረው ክፍል መልክዓ-ምድራዊ ትስስሩ በማይናጋበት መንገድ እንደገና ማስመር ነው፡፡ የኮምፒውቴሽናል ጂኦሜትሪ (Computational Geometry) ባለሙያዎች ይህን እንዲያጠኑልን መጠየቅ ይገባል፣ የሚቻለን ከሆነ፡፡ በዘርፉ ባለሙያ ባልሆንም ግን የውስጤ ግንዛቤ የሚያስረዳኝ ነገር ቢኖር፣ ችግሩ መልክዓ-ምድራዊ ተግዳሮትም ይሁን በህገ-መንግስቱ ብልሹነት ምክንያት መፍትሄ እንደማይሆን ነው፡፡

ሐ) ሦስተኛው አማራጭ ፣ የህዳጣን ጎሳዎችን የውሳኔ ሰጭነት አቅም በህገ-መንግስት የሚጸናበትን አግባብ በመፍጠር ከብዙሃን አምባገነንነት መታደግ ነው፡፡ ይህ በተለይ የብሔር ፌደራሊዝሙ ጠበቃ ነን የሚሉትን የኦሮሞና ትግሬ ጎሰኞችን እንዲመልሱ ማስገደድ ያለብን ጥያቄ ነው፡፡

የቡድን (ጎሳ) መብት እንደ እጅ አዙር የግለሰብ (ዜጋ) መብት ማስከበሪያ በሚውልበት አገር ውስጥ ከ84ቱ ጎሳወች 70ዎቹ ጎሳዎች እንኳን በህገ-መንግስቱ ውስጥ ስማቸው አይጠቀስም፡፡ በፖለቲካና ህግ ተቃርኖ ውስጥ ተዘንቀው የሚገኙ ምድሮች ሆነዋል፡፡ በአንዳንድ የአገሪቷ ክፍል ደሞ ሰው አ'ዳኝ በሆኑ ጎሰኞችና ጊዜያዊ ሰፋሪዎች ምክንያት በፍርሃት ይኖራሉ፡፡ ህገ መንግስቱ ሙሉ በሙሉ የማይታደስ ከሆነ፣ ቢያንስ የሚከተሉትን ማሻሻያዎች በማከል አሁን ያላቀፋቸውን ማንነቶች በተሻለ አቅፎና አሳትፎ እንዲሄድ ማድረግ ይቻላል፡፡

- ሁሉም ጎሳ ህገ-መንግስቱን ዕውቅና እንዲሰጠው ማድረግ
- ህገ መንግስቱ 84ቱንም ጎሳዎች በሁለቱም ምክር-ቤቶች በተገቢው እንዲወክል አድርጎ መከለስ
- የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (የታችኛው ምክር ቤት) ውክልናን በጎሳዎች ብዛት ማዋቀር፡፡ በቅርቡ የሶማሌ ጎሳ ግዛት ፕሬዚዳንት እንዳስታወቀው፡፡ እዚህ ምክር ቤት ውስጥ የሶማሌ ጎሳ በብዛቱ መጠን አልተወከለም፡፡ እንደሚታወቀው በብዛት የሶማሌ የሚበልጥ ሆኖ ሳለ በተወካዮች ምክር ቤት ወንበር ብዛት ግን የትግሬ ጎሳ ይበልጣል (35 ትግሬ ፣ 24 ሶማሌ)፡፡ መቼም ወንበሩን ማን እንዳከፋፈለው አትስቱትም፡፡
- አሁን ባለው አሰራር፣ ፌደሬሽን ምክር ቤት (የላይኛው ምክር ቤት) እዚህ ግባ የሚባል ሥልጣን የለውም፡፡ ህግ ሲያጸድቅ ወይም ውድቅ ሲያደርግ የሚችልበትን አቅም ማጎናጸፍ ያስፈልጋል፡፡ ልክ እንደ አሜሪካ የህግ መወሰኛው ምክር ቤት የጎሳን ቁጥር ከግምት ሳይከት፣ ከ84ቱም ጎሳወች 2 አባላትን ወስዶ ይቋቋማል ማለት ነው፡፡
- ለምሳሌ በአሜሪካው የህግ መወሰኛ ምክር ቤት 40 ሚሊዮን ህዝብ ያለው ካሊፎርኒያ ግዛትና 578,000 ህዝብ ብቻ ያለው የዋዮሚንግ ግዛት እኩል 2 ድምጽ ነው ያላቸው፡፡ በዚህ አሰራር መሰረት የላይኛው ምክር ቤት ጥቂት ህዝብ ብዛት ላላቸው ጎሳዎች ጥበቃ ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ጎሳ እኩል ድምጽ አለውና፡፡ የታችኛው ምክር ቤት በቁጥር አናሳ የሆኑትን ጎሳዎች ጥቅም የሚጎዳ ህግ ቢያረቅ የላይኛው ምክር ቤት ውድቅ ያደርገዋል ማለት ነው፡፡

ይህ አሰራር ሙሉ በሙሉ በእኛ አገር ከተተገበረ ህዳጣን ጎሳዎችን አቅም በማጎልበት ብቻ የሚያቆም ሳይሆን፣ የጎሳ ፖለቲካን ያዳክማል ወይም ሙሉ በሙሉ ከመድረኩ ያሰናብታል፡፡ እንዴት? ለህዳጣን ጎሳዎች እኩል ውክልና መስጠቱ፣ አሁን የሚስተዋለውን የጥምረት አቀጣጫ ወደ ሀገራዊነት አቀንቃኝ ፓርቲዎች እንዲያጋድል ያደርገዋል ምክንያቱም እነዚህ ጎሳዎች በብዙ ምክንያት ጥቅማቸውን የሚያስከብረው የዜግነቱ ፖለቲካ ኃይል ስለሚሆን ነው፡፡

 በመጀመሪያ በቁጥር ብዙ ያልሆኑ ጎሳዎች እንደ ሀገር ለመቆም የሚያስችል ቁመና ስለሌላቸው ነጻና የበለጸገ ማህበረሰብ የመፍጠር ዕድላቸው የሚወሰነው ከሌላው ጎሳ ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር ነው፡፡

 ሁለተኛ፣ በቁጥር ብዙ የሆኑ ጎሳዎች መገንጠል ለእነሱ ኢኮኖሚያዊ እድገት አደጋ እንደሆነ አሳምረው ያውቃሉ፡፡ እንደ ህዝብ በኢኮኖሚ የማደግና መበልጸግ እድላቸው የሰፋ የሚሆነው ከተኮማተረችና ከተዳከመች ኢትዮጵያ ይልቅ በትልቋ እና ጠንካራዋ ኢትዮጵያ ሥር ቢሆን እንደሆነ በግልጽ ይረዳሉ፡፡

 ሦስተኛ፣ በተባበረ፣ አንድነቱ በተጠናከረ ፣ ዴሞክራሲያዊ በሆነ ከባቢ መኖር በትልልቅ ጎሳዎች ከመዋጥ፣ የድርድር ማስያዣ (hostages) ከመሆን ይታደጋቸዋል፡፡ በቅርቡ እንኳ ጋሞ እና ጌድኦ ጎሳዎች ላይ የደረሰውን የምናስታውሰው ነው፡፡

በመጨረሻም የአገራችን ፓለቲካ ማጠንጠኛ በታችኛውና በላይኛው ምክር ቤት መካከል የሚኖረው የፓለቲካ ሙግት የሚያምቅበት እንጂ የጎሳዎች መካረር የሚተረክበት ከመሆን በሂደት ይወጣል፡፡ የህገ-መንግስቱን መሻሻል የሚቃወሙት የኦሮሞ ጎሳ አባላት ብቻ አይደሉም፡፡ ትግራይ የመሸጉ የአግዜር ታናሽ ወንድሞች ነን ባዮቹም ሽንጣቸውን ገትረው ህገ-መንግስቱ እንዳይነካ ይወተውታሉ፡፡ የእነሱ ምክንያት ግን ወዲህ ነው፡፡ አሁን በስራ ላይ ያለው ህገ-መንግስት የአማራን ጎሳ ለም መሬት ቆራርጠው እንዲወስዱ አድርጓቸዋል፡፡ ህገ-መንግስቱ እንዳይነካ የሚፈልጉት መሬቶቹን ለባለቤቱ ላለመመለስ ነው፡፡ የዘረፉትን መሬት እንደማይነጠቁ ቃል ከተገባላቸው፣ ንጉሳዊ ይሁን አሀዳዊ ወይም ሌላ በየትኛውም የፖለቲካ ርዕዮ በደስታ ይስማማሉ፡፡ እነሱም ህገ-መንግስቱ እንዳይነካ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብታቸውን የሚጠቀሙት ከአማራ ጎሳዊ ግዛት የዘረፉትን መሬት ህጋዊ ከለላ የሚሰጠውን ህገ-መንግስት ለማስጠበቅ ነው፡፡

በስተመጨረሻ መረዳት ያለብን የትግራይም ይሁን ኦሮሞ ጎሰኞች ስለ ብሔር ብሔረሰብ መብት ፈጽሞ አይጨነቁም፡፡ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ፖለቲካዊ ተሳትፎአቸውንና በአገር ጉዳይ የውሳኔ ሰጭነት ሚናቸውን የሚያጎላ ሥርዓት ይቀርጹ ነበር፡፡ የዐቢይ አስተዳደርና የዜግነት ፓለቲካ ኃይሎች “ፌደራሊስት ወይስ አሀዳዊ” የሚለውን ፖለቲካዊ ሙግት ወደ “ለህዳጣን ጎሳዎች ፍትሐዊና አቅም ፈጣሪ የሆነ ፌደራላዊ አስተዳደር ወይስ ህዳጣኑን ጨፍላቂ የሆነ ፌደራላዊ አስተዳደር” ወደሚል የውይይት መድረክ ማሸጋገር አለባቸው፡፡

**…የትግራይ ጎሰኞች “የብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠልን” ሲያጸድቁ እንደ እንጀራ እናት ጡጦ በባዳው ኦነግን ለመደለል እንጂ መቼም በተግባር ሲተረጎም አይችሉም በሚል ታሳቢ ነው፡፡ ሆኖም ግን የትህነግ ከሥልጣን መወገድ፣ የፖለቲካ ምህዳሩ ዴሞክራሲያዊ መሆን፣ እንዲሁም አሁን ያለው አሰራር ህገ-መንግስቱን ሙሉ በሙሉ ማክበሩ፣ ለኦነግና መሰል ርዕዮ አራማጆች የህዳጣን ጎሳዎችን መደራደሪያ የሚያደርጉበትን አቅም ፈጥሮላቸዋል…**

# “ደሕንነቱና ህግ አስፈጻሚው አካል ኢትዮጵያዊ እውነታችንን ነጥቆናል”

## “በነገደ ብሔርተኝነት ተጠልፎ በጎጡ የቀረ ፖለቲከኛ ነው ያለው”

**ዶ/ር አለማየሁ አረዳ**

**ዶ/ር አለማየሁ አረዳ የተወለዱት በቀድሞው አሩሲ ጠቅላይ ግዛት በ1942 ዓ.ም ነው ። ወላጅ አባታቸው በመምህርነት ይሠሩ ስለነበር በሁሉም የአሩሲ አካባቢዎች ተዘዋውረው ለመማር ችለዋል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኬሚስትሪ የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ፣ “ባዮ ኬሚስትሪ” በተባለ የትምህርት ዘርፍ ደግሞ ከዩንቨርስቲ ኦፍ ለንደን ፒ ኤች ዲአቸውን አግኝተዋል። አብዛኛውን ጊዜያቸውን በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመምህርነት አገልግለዋል፤ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፣ ደብረዘይት ኮሌጅና አዳማ ዩንቨርሲቲ ደግሞ ካስተማሩባቸው መሃል ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።**
**በጅማ እርሻ ኮሌጅ በዲንነት እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥም በሓላፊነት የሠሩት ዶ/ር አለማየሁ፤ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲን ካቋቋሙት ሙያተኞች መካከል አንዱ ቢሆኑም ከአራት ዓመታት በላይ በዩኒቨርሲቲው ግን አልቆዩም። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ከኢህአፓ እስከ ቅንጅት ከፍተኛ ተሳትፎ የነበራቸው ዶ/ር አለማየሁ አረዳ፤ ኢትዮጵያዊነትን በማቀንቀን እና ጽንፈኛ ብሔርተኝነትን በማውገዝ ይታወቃሉ። እኚህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ማን ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ይሆን ዘንድ የግዮን ጋዜጠኛ ሮቤል ምትኩ በወቅታዊና ተዛማጅ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያደረገውን ሠፋ ያለ ቆይታ እንደሚከተለው ያስቃኘናል።**

**ግዮን፡- “የኢሕአዴግ ካድሬዎች ማምረቻ ነው” በሚል የሚተቸውን ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ (አሁን ዩንቨርሲቲ) ካቋቋሙት ምሁራን መሀል አንዱ እርስዎ ቢሆኑም፣ ከአራት ዓመት በኋላ ተቋሙን ለቀዋል፣ ምክንያትዎ ምን ነበር?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ መጀመሪያ የተቋቋመበት ዓላማ፤ በብሔር አደረጃጀት ላይ የተመሠረተው ፌዴራሊዝም ሲመጣ፣ ትልቅ የሰው ኃይል ክፍተት ነበር፤ በየክልሎቹ ውስጥ የየብሔረሰቡ ልሂቃን ወይም በመንግሥት መ/ቤት ውስጥ ተሹመው መሥራት የሚችሉ ሰዎች ቁጥር አናሣም ነበር። ያንን ክፍተት ለመድፈን፣ በተጨማሪም በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥ ብቃት፣ ጥራት ምናምን የሚሉ ሀሳቦች በወሬ ደረጃ ተይዘው ስለነበር ከነዚህ ነጥቦች በመነሣት ነው ኮሌጁ እንዲቋቋም የታሰበው።

ኮሌጁ ከተቋቋመ በኋላ ግን በረሃ የነበሩ የሕወሓት፣ የኢህዴን (ብአዴን፣ ኦዴፓ)ና የሌሎቹ ድርጅቶች አባሎች ከዩንቨርስቲና ከ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አቋርጠው ስለነበር በርሃ የሄዱት፣ እነዚህ ሰዎች የመማር ዕድል ፈላጊ ሆነው መጡ። ሰዎቹ ከቤተሰብ ርቀው በርሃ የኖሩ ስለሆኑ፤ ተምረናል ከማለት በስተቀር መማራቸውን የሚመሰክር ትክክለኛ መረጃ ማቅረብ የሚችሉ አልነበሩም። ግን ብዙዎቹ እዛው ይተዋወቃሉ።



ስለዚህ እነዚህን ሰዎች በዋናው የዩኒቨርስቲ ሥርዓት ውስጥ አስገብተህ ለማስተማር አስቸጋሪም ነበር። የመጀመሪያና ሁለተኛ ዙር ሲቪል ሰርቪስ ከተማሩ ሰዎች ውስጥ አብዛኞቹ ከታጋዮቹ መሃል የመጡ ናቸው። በተለይ በመንግሥት መ/ቤት ውስጥ ይሠሩ ነበሩ። ከዛ በኋላ ደግሞ ከአፋር፣ ከሶማሌ፣ ጋምቤላ የሚመጡትን ደግሞ በነበረው የኮታ ሥርዓት መሠረት ነበር የምናስገባቸው። በጊዜው ከትምህርት ማስረጃ ባሻገር የመግቢያ ፈተና ሰጥተን 60 በመቶ ያመጡትን ይገባሉ ብለን ነበር ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅን ስንመሰርት ያቀድነው፤ ግን እንደዛ እንደታቀደው ማስኬድ ግን አልቻልንም።

**ግዮን፡- ለምን? የፖለቲካ ተፅዕኖ ነበረባችሁ?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- ግልፅ የሆነ የፖለቲካ ተፅዕኖ ነበር። ሁሉም ድርጅት የራሱ ሰው እንዲማርለት ስለሚፈልግ ብዙ ዓይነት ስህተቶች ተፈፅመዋል። ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ውስጥ ሆኜ ሰዎች “ካድሬ ነው እንዴ የምታስተምሩት?” ሲሉኝ፤ ካድሬ እኮ የትም ይማራል፣ በሌሎች ተቋም ውስጥም እየተማረ ነው። በርግጥ የኢህአዴግ አባላት የሆኑ በብዛት ይማራሉ፣ ለምሣሌ የአፋር፣ የሶማሌ፣ የጋምቤላና የቢኒሻንጉል ልጆች እኮ የኢህአዴግ አባላት አይደሉም እያልኩ ምላሽ እሠጥ ነበር። የኮሌጁ አመሠራረትና ዓላማው፣ አነሳሱ ጥሩ ነበር። እኔ የገባሁት ለማቋቋም ነበር፤ ሦስት ፋካልቲዎች፣ ስድስት ዲፓርትመንቶች፣ ትልልቅ ላይብረሪዎች፣ የሥነልሳን ቤተሙከራ፣ የኮምፒውተር ማዕከሉ ሁሉ በጥሩ ሁኔታ ነበር የተቋቋመው። ካደረጀን በኋላ ግን አራት ዓመት ብቻ ነው ያገለገልኩት።

**ግዮን፡- የለቀቁት ከኢሕአዴግ ጋር ስላልተግባቡ እንደሆነ በወቅቱ ሲነገር ነበር።**

ዶ/ር አለማየሁ፡- እኔ ከባህሪዬም ሆነ ከነበረኝ ዓላማ አንፃር እዛ ለዘላለም መቆየቱን አልፈለግኹም። ከኢሕአዴግ ቤት እለቃለሁ ስትል ትንሽ ችግር አለው። በዛ ላይ አባል ሁን ተብለህ እምቢ ካልክ መልቀቅህ ችግር ያመጣል። ያም ቢሆን እኔ ግን ማመልከቻዬን አቀረብኩ። በወቅቱ ጠ/ሚ/ር የነበሩት መለስ ዜናዊ “ከሓላፊነትዎ በጠየቁት መሠረት ተነስተዋል፤ ኮሌጁን ስላቋቋሙ እናመሰግናለን” የሚል ጥሩ ደብዳቤ ጽፈውና ፈርመው ሰጥተውኝ ነው የለቀቅኹት። አንድ ሠው ከመንግሥት መ/ቤት ሲነሳ፣ በተለይ ለኢሕአዴግ የሠራ ሰው ከሆነ ብዙ ጊዜ እንደወንጀለኛ ነው የሚታየው። እኔ ለምሣሌ የሲቪል ሠርቪስ ኮሌጅ ዓላማውን ስለማውቀውና ስለማምንበት ነው በምስረታው ላይ የገባሁበት። አሠራሩ ችግር ነበረው ወይ? ከተባለ ስም አልጠራም እንጂ እንኳን አዲስ አበባ ላይ፣ የትም ቦታ ችግር ነበር።

**ግዮን፡- ከዛ በኋላ ወዴት ሄዱ?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- ለሁለት ዓመታት ያህል በአንድ የጀርመን ድርጅት ውስጥ የፕሮጀክት ማኔጀር ሆኜ ሠርቻለሁ። ከዛ በኋላ በቅጥር ሥራ መጓዙ ስላልተመቸኝ፣ እንዲሁም በኤንጂኦ ሴንተር ውስጥም አክቲቭ ስለነበርኩኝ፤ የበጎ አድራጎት ሥራ የምሠራበት “ቸር ኢትዮጵያ የሰብዓዊና የልማት ማኅበር” የተሰኘ ድርጅት መሰረትኩ። እ.ኤ.አ በ2008 አዋጁ እየከረረ ሲመጣና ለመሥራት አስቸጋሪ ሲሆን ነው የዘጋነው።

**ግዮን፡- የወጣትነት ዘመን የፖለቲካ ተሳትፎዎን እስኪ ወደ ኋላ መለስ ብለው ያጫውቱን፤ የቅርብ ጓደኞችዎ ኢህአፓ እንደነበሩ ይናገራሉና።**

ዶ/ር አለማየሁ፡- በ1960ዎቹ መጀመሪያና አጋማሽ ወደ ዩንቨርስቲ ስገባ በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ወደድክም ▶



ጠላህም ተሳታፊ የምትሆንበት ሁኔታ ስላለ እኔም ተሳትፊያለሁ። የአፄ ኃይለስላሴ መንግሥት በ1967 ዓ.ም ሲወድቅ እኔ ሦስተኛ ዓመት የዩንቨርሲቲ ሰርቪስ የሚባለውን የማስተማር ሥራ እየሠራሁ ነበር።

ከዛ ስንመለስ ዘመቻ ሆነ፡፡ በአጋጣሚ ኢህአፓም የተመሠረተው በ1967 ዓ.ም ስለነበር፣ ኢህአፓ ውስጥ ከተራ አባልነት በዛ አካባቢ ተመልምዬ በመቀጠል በዞን፣ በክልል እያልኩ በድርጅቱ ውስጥ የራሴን አስተዋፅኦ አድርጊያለሁ ብዬ አስቢያለሁ። ብዙ ጓደኞቼን በትግል ውስጥ አጥቻለሁ። እሡ በጣም ይፀፅተኝ ስለነበር በ1991 ዓ.ም ከሲቪል ሠርቪስ እንደለቀቅኹ የመጀመሪያ ሥራዬ አድርጌ የያዝኩት ቀደም ሲል በኢህአፓ ውስጥ እንተዋወቅ የነበርን፣ በልዩ ልዩ ደረጃ የሚሠሩ ሰዎችን በማሰባሰብ፤ የራሣችንን የፖለቲካ ድርጅት እንድናቋቁም፣ መሥራች ሆኜ በመንቀሳቀስ፤ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሊግን (ኢድሊ) መሥርተን የድርጅቱ ሊ/መንበር ሆኜ ሠርቻለሁ።

**ግዮን፡- ኢ.ዲ.ሊ እንደተመሠረተ ወዲያውኑ ነበር ከቅንጅት ጋር የተጣመረው፤ ይህ እንዴት ነበር የሆነው?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- አዲስ ፍቃድ ከማግኘቱ በፊት ፕሮግራሙን እንዲያዩትና ሀሳብ እንዲሰጡን ለተወሰኑ ሰዎች ሰጥቼ ነበር። ያ ፕሮግራም መኖርያ ቤታቸው የተገኘ ኹለት አንጋፋ ምሁራን ታሠሩ። በቴሌቪዥንም "የኢትዮጵያ ዴሞክራያዊ ሊግ" የሚባል ሕገ - ወጥ ድርጅት ሲያቋቁሙ ደርሰንባችዋል ተብሎ ዜና ተሠራባቸው፤ መግለጫም ወጣባቸው።

**ግዮን፡- ካልተሣሣትኩ እነዛ ኹለቱ ምሁራን ፐ/ር መስፍን ወ/ማርያምና ፐ/ር ብርሃኑ ነጋ ናቸው መሠለኝ?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- ትክክል ነህ። እነርሱ ሲታሠሩ የነበረኝ አማራጭ በቅድሚያ ሰዎቹ መፈታት ስለነበረባቸው፣ በ1994 ዓ.ም አዲሱን ፓርቲ በአዲስ አበባ ደረጃ የክልል ድርጅት አድርገን መሠረትነውና ሰርተፍኬቱን ወሰድን። የእነዚህ ምሁራን መታሰር ወደ ፊት እንድንራመድ ከመግፋቱ ባሻገር በፍጥነት ህጋዊ መሆን ካልቻልን ነገሮች የበለጠ አስቸጋሪ እንደሚሆኑ አሣየን። በ1996 ዓ.ም ደግሞ በአገር ዐቀፍ ፓርቲነት ደረጃ ተመዝግበን ኹለቱንም ሰርተፍኬቶች አግኝተናል።

ከላይ በገለፅኩት ምክንያት ለእስር የተዳረጉት ፐ/ር መስፍን ወ/ማርያምና ፐ/ር ብርሃኑ ነጋ መጀመሪያ ላይ አዲስ ፓርቲ ማቋቋም አያስፍልግም ብለው ነበር የሚከራከሩት። አንዳንድ ሰዎች ከዚህ በመነሳት ለምን ወደ ኢዴፓ አትገባም ? በማለት ሲመክሩኝ ነበር፡፡ እኔም ከጓደኞቼ ጋር መሥራት የጀመርኩት ነገር ስላለ በዛ ነው የምሄደው ብዬ ስለነበር፤ ኹለቱ ምሁራኖች ከእስር ሲፈቱ የተቀየረና አዲስ ሃሳብ ይዘው መጡ።

**ግዮን፡- ምን ዓይነት?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- መኢአድ፣ ኢዴፓም አዲስ ሆኖ ብቅ ያለው የእኛም ፓርቲ አገራዊ አጀንዳ እስካላቸው ድረስ ለምን አንድ ላይ አንሆንም? የሚል ጥያቄ አቀረቡ። ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ ከእነ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ጋር በዝርዝር ተነጋግረንበት፤ አብረን መቀጠል ከቻልንና ለአገራችን የሚበጅ ከሆነ እኛ ለመግባት ዝግጁ ነን ባልነው መሠረት፣ እነሱ "ቀስተ ደመና" ፓርቲን መሠረቱ። በኋላ አራቱ ፓርቲዎች አንድ ላይ ሆነን ቅንጅት ተፈጠረ ማለት ነው።

**ግዮን፡- ቅንጅት በምርጫ 97 ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ቢችልም ፓርላማ ሳይገባ ቀርቷል፤ ያንን ጊዜ ወደ ኋላ መለስ ብለው ቢያስቃኙን?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- ቅንጅት ይዋሃድ ሲባልና እንዲዋሃድ ጥረት በምናደርግበት ሰዓት ላይ በርከት ያሉ የራሱ ችግሮች ነበሩት። እነዛን ችግሮች በተመለከተ በመጽሐፍ የተለያየ ርዕስ እየተሰጣቸው ወጥተዋል። እኔ አንድ ዕምነት አለኝ፤ የጋለ ብረት ይዘህ ሄደህ አመድ ውስጥ ብትከተ ፍም መፍጠር አትችልም። እሱ የሞተ ጉዳይ ነው፤ ያለበት ቦታ ላይ ፓርክ አድርገን መሄድ መቻል አለብን። "ምሁሩ" የተሰኘውን መጽሐፌን ስጽፍ ቅንጅት ብዬ አልጥራ እንጂ፣ የኢትዮጵያን ፖለቲካና የምሁሩን ሁኔታ በተወሰነ ደረጃ ለመግለፅ ሞክሪያለሁ።

ፓርላማ አለመግባታችን በጣም ትልቅ ስህተት ነበር፤ ይሄ መጀመርያ ላይ የወሰድኩት አቋም ነው። ብንገባ ጥሩ ነበር፤ ለስለስ ያለ ሁኔታ ይፈጠር ነበር ብዬም አስባለሁ። ከዛ በኋላ ግን የባላንጣነት ፖለቲካው ሊረግብ አልቻለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢህአዴግ ሰልችቶት ስለነበረ ቅንጅት በወቅቱ ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቷል። በተገቢ ደረጃ፣ በተገቢ ብቃት፣ በራሳችን ውስጥ ከነበረው ጭቅጭቅ ባሻገር ሄደን፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ መሠረታዊ ችግሮች፣ ወጥረው የያዙትን የዕለት ተዕለት ችግሮችን በአጀንዳ ቀርፀን፣ ባወጣነው ማኒፌስቶ አውቆንና ተረድቶን ነው ሕዝብ የወደደን? ወይስ ከዚህስ ይኼኛው ይሻላል በሚል ነው? የሚለው ሁሉ መታየት አለበት የቅንጅት ጉዳይ ሲነሳ።

እኔ ቅንጅት ውስጥ የተማርኩት ነገር ሰዎችን በርቀት ሲታወቃቸውና ቀርበህ ስታውቃቸው ልዩነቱ የሰማይና የመሬት ያህል ነው። ይህ የባላንጣነት ፖለቲካ ከቅንጅትም በኋላ ለረዥም ጊዜ እንደሚቀጥል ሲገባኝ፣ በዛ ላይ ዕድሜዬም እየሄደ ስለሆነ፤ የግድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ገብቼ ነወይ ለኢትዮጵያ አስተዋፅኦ የማበረክተው? በሚል ከዛ በመነሳት ሚዲያውንና የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም ለአገሬ መሥራት ያለብኝን እሠራለሁ በሚል፣ ከቅንጅት በኋላ የትኛውንም ፓርቲ አልተቀላቀልኩም።

**ግዮን፡- ከፓርቲ ውጭ ሆኖ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ሥርዓቱን በመቃወምና በመተቸት መጓዝ ራስን ለአደጋ ከማጋለጥ ባሻገር፣ ለኮርኳሚዎች አመቺ አይሆንም?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- እኔ እውነትና ትክክለኛ ነው ብዬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባስተላለፍኩት መልዕክት መኮርኮም ነውር አይደለም። በርግጥ ብቻህን ስትንቀሳቀስ ለአምባገነኖች ጥቃት ምቹ ትሆን ይሆናል። ግን እኔ ዛሬ ካሉት ፖለቲከኞች እጅግ በጣም በከፋ ሁኔታ ኢህአፓ ውስጥ አብዩዝድ የሆንኩ ሰው ነኝ። ልክ እንደ ቤተ እምነት ነበረ ፓርቲያችንን የምንወደው፡፡ ኢሕአፓ የሄደበት አካሄድ አመራሩ ብዙ መስዋዕትነት እንድንከፍል ነው ያደረገን። በአጋጣሚ ሆኖ በሕይወት የተረፍነው ጥቂት ብንሆንም የሞቱት ቁጥር የትየለሌ ነው። ዛሬ እናንተ እዚህ ቦታ ሦስት ሰው ሞተ፣ በእከሌ ከተማ ሠው ተሰቀለ ሲባል ትሰማላችሁ፤ በርግጥ ይሄን መጥፎ ነገር ባታዩት ጥሩ ነበር። በእኛ ዘመን እኮ ደረታችን ላይ "ቀይ ሽብር ይፋፋምብኝ" የሚል ጽሑፍ ተለጥፎ አናታችንን ስንበረቀስ ነው የኖርነው። እጅግ ዘግናኝ የሆነ ነገር ነው ሲፈፀምብን የነበረው፤ ያውም ለአንድ ዓላማ ቆመን። ብንሣሣት እንኳን ለኢትዮጵያ ነበር የምንታገለው። ብዙ ስህተቶች ሠርተናል፣ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ግን ምንም ስህተት አልነበረንም።

የብሔሮች ጥያቄን፣ እኩልነት ይከበር የሚለውን መርህ እኮ ያነሣነው እኛ ነን። መሬት ለአራሹ ይሰጥ የሚለውን ጥያቄ እኮ ያነሳነው እኛ ነን። ዛሬ ላይ ሶሊድ የሆኑ መፈክሮች ያወጣ ድርጅት ወይም ግለሰብ ማነው? ዝም ብሎ የድሮውን ይዞ እኮ ነው የሚንቦቸረው፡፡ በነገዳዊ ብሔርተኝነት ተጠልፎ፣ የራሱን አካባቢ እያየ፣ በጎጡ የቀረ ፖለቲከኛ ነው ያለው። እኔ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ብሆን አሁን የምሠራውን ዓይነት ሥራ አልሠራም፡ ►

፡ የትኛውም መድረክ ላይ፣ ማንኛውም ሚዲያ ላይ ተጋብዤ እምቢ ብዬ አላውቅም፡፡ ማስተላለፍ ያለብኝን መልዕክት በአግባቡ ለሕዝብ ከማድረስ ወደ ኋላ አልልም፡፡

**ግዮን፡- ኢሕአፓ ከበርካታ ዓመታት በኋላ ወደ ሀገር ቤት ተመልሷል፣ በቀጣይ ምርጫም ለመሳተፍ እየተዘጋጀ ነው፡፡ የያ ዘመን ትውልድ ከዚህ ዘመን ብዙኃኑ ወጣት ድጋፍ ማግኘት ይችላል?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- ኢ.ሕ.አ.ፓ እንግዲህ ትዝታው ነው ያለው፡፡ እነዚህ ከአሜሪካ ኢሕአፓን ይዘው የመጡትን ሰዎች በመጠኑም ቢሆን በታሪካቸው አውቃቸዋለሁ፤ በጣም ጄኒዩን ሰዎች ናቸው፡፡ ኢሕአፓን በነበረው ቅርፅና ይዘቱ ይዘው ለመቅረብ ያለሙ ከሆነ ቁጭ ብለው ኹለቴ ቢያስቡ ነው የተሻለ የሚሆነው፡፡ ለእዛ ጊዜው ረፍዷልና፡፡

በነገራችን ላይ የድሮው ኢሕአፓ በኢትዮጵያዊነት ላይ አትምጡ ይላል እንጂ፣ በብሔር ጥያቄ ላይ ችግር የነበረው ድርጅት አልነበረም፡፡ ስለዚህ ኢሕአፓ አይምጣ የማለት መብት ስለሌለን መምጣቱን በፀጋ እንቀበላለን፡፡ ግን እዚህ ካሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ተቀራርበው መሥራት የማይፈልጉ ከሆነ፣ በነበረው የድሮ አካሄድ መጓዝ የሚሹ ከሆነ ይቸገራሉ ብዬ ነው የምገምተው፡፡

**ግዮን፡- ሕወሓት መራሹ አምባገነን መንግሥት በሥልጣን ላይ በቆየባቸው 27 ዓመታት የነበረውን አጠቃላይ የኢትዮጵያን እና ሕዝባችንን ገፅታ፣ ፖለቲካውን ጭምር እንዴት ይገልጹታል?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- በኢትዮጵያ እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ አሃዳዊ ሥርዓት ነው የነበረው፡፡ ደርግም ሥነ - ሥርዓት አስከባሪ መንግሥት ነው፡፡ ከዚህ የተነሣ የፖለቲካ ልሂቃን በአንድ ጀልባ ላይ የነበሩበት ሁኔታ ነበር፡፡ ከ1983 ዓ.ም በኋላ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ገዢ የሆነው ርዕዮት ተቀይሯል፡፡ እኛ እኮ ለምሳሌ በአገራዊ ብሔርተኝነት፣ በኢትዮጵያዊነት አጀንዳ ነው ስንታገል የነበረው፡፡ ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የነገዳዊ ብሔርተኝነት አገራዊ ብሔርተኝነቱን ደፈቀው፡፡

ከዚህ ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያ ልሂቃን ሁለት ቦታ ነው የተከፈሉት፡፡ የየብሔሩ ልሂቃን የብሔር መብት በዚህ መንገድ የሚከበር ከሆነ በሚል የየብሔር ድርጅታቸውን ነው የመሠረቱት፡፡ በ1984 ዓ.ም ስልሳ የሚሆኑ የብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ነበሩ፡፡ ሁሉም አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው የተፈለፈሉት፡፡ የብሔር ጉዳይ ውስጥ መግባቱ አይደለም ችግሩ፣ ያለፈውን ታሪክ ለመቅበር አዳዲስ ተረኮች መፈጠራቸው ነበር አሳሳቢው ጉዳይ፡፡ ከዛ በፊት ሰምተናቸው የማናቃቸው የብሔር ተረኮች ተፈጠሩ፡፡ እያንዳንዱ ልሂቅ የራሱን አካባቢ ለማስተዳደር መብት እንዲኖረው፣ ከሥልጣኑ እንዲደርሰው ሲል አንዱን ከሌላው የሚያጣላና የሚያናክስበትን ተረክ ይፈጥር ጀመር፡፡ ይሄ ደግሞ በአገሪቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ ልዩነት ፈጠረ፡፡

ከፋፋይነትን የወለደው የነገደ ብሔርተኝነት፤ የሀብት ክፍፍሉ ራሱ የተዛነፈ እንዲሆን ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ስለ ነፃነት እየተወራ ዛሬ ለምሳሌ ብድግ ብለህ "ይሄ ያነሳችሁት የብሔርተኝነት አጀንዳ ኢትዮጵያን ይጎዳታል" ብለህ ብትናገር "ትምክህተኛ፤ የድሮውን ሥርዓት ናፋቂ" ተብለህ ነው የምትወረወረው፡፡ ኢትዮጵያውያን የጋራ እውነት እንዳይኖራቸው ነው የተደረገው፡፡ በዚህ 27 ዓመት ውስጥ የጋራ እውነት ማለት ኢትዮጵያ እንዴት ትደግ? የሕዝቦች መብት እንዴት ይከበር? የሚሉት መግባባቶችን ያካትታል፡፡ በእነዚህ 27 ዓመታት ግን እንዳንግባባ ተደርገን፣ አንደኛችን ቋንቋ ስንል፣ ሌላኛችን ክልል፣ ድንበር፣ የእኔ ወገን ብዙ ሥልጣን አላገኘም በሚል የተምታታ ነገር ውስጥ ነው የከረምነው ፡፡

ልክ እንደ ባቢሎን ግንብ ሠሪዎች አሸዋ ሲጠይቅ ውሃ፣ ውሃ ሲጠይቅ ድንጋይ እንደሚሰጠው ዓይነት በልዩነታችን ወጥረው፣ በየጥጋችን አስቀምጠው ነው የገዙን ኢሕአዴጎች፡፡ በኃይል ጭምር ነው የገዙን፡፡ ደህንነቱ፣ የፖሊስ ኃይል፣ መከላከያው በተለይ ደግሞ አስፈፃሚው አካል ኢትዮጵያዊያንን እውነታችንን ነው የነጠቁን፡፡ በረዥም ጊዜ ኢትዮጵያ ያፈራቻቸውን የታሪክ እሴቶች መሻት ናቸው ብለን እንድናምን ማጅራታችንን የተያዝንባቸው ዓመታት ናቸው እነዛ ጊዜያት፡፡

**ግዮን፡- አሁንስ ከዛ ስሜት ተላቀናል ማለት ይቻላል?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- አሁን ደግሞ የ27 ዓመቱ መጥፎ የቤት ሥራ ጥላው ያጠላበት የሽግግር ሁኔታ ውስጥ ነው የገባነው፡፡ ያ ክፉ ዘመን እውነታችንን ሲነጥቀን፣ የመደራጀት መብታችንንም ነው አብሮ የወሰደው፡፡ ፖለቲካው ራሱ በባላንጣነት ፖለቲካ ውስጥ እንድንዘፈቅ ነው ያደረገን፡፡ በመሆኑም ለኢትዮጵያ የሚበጅ ድርጅታዊ አቅም እንድንገባ አላደረገንም፤ ቀብሮ እንዳስቀረን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

ሥርዓቱ ራሱ ኪራይ ሰብሳቢ ሆኖ፣ መሬት እየዘረፈ፣ ሥልጣኑን እያከራየ፤ እኛን ኪራይ ሰብሳቢ ብሎ ሲሰድብ ነው የኖርነው፡፡ እያንዳዱ የኢሕአዴግ ባለሥልጣን 10 እና 30 የመሬት ካርታ በዘመድ አዝማዶቻቸው ስም እየያዙ እኛን በመስደብና በማጨናበር ነበር የኖሩት፡፡ አሁን ከዚህ ጨለማ ውስጥ ሊያስወጣን ከፊታችን የቆመው ደግሞ ከእነሱ መሃል የወጣ ሰው ነው፡፡

**ግዮን፡- ወደ እሱ እንምጣ፡፡ ከኢሕአዴግ ጉያ የወጡ የቲም ለማ ቡድን አባላት ወደ ሥልጣን ከወጡ በኋላስ ያለውን ሁኔታ እንዴት ይገልፁታል? የፖለቲካ እስረኞች መፈታታቸው፣ የተለያዩ በሽብርተኝነት የተፈረጁ ድርጅቶች ወደ አገር ቤት መግባታቸው፣ ሚዲያዎች መከፈታቸው በትክክልም የለውጥ ቡድን መጥቷል ማስባሉን እንዴት አገኙት?**

ዶ/ር አለማየሁ፡- በመጀመሪያ ደረጃ አሁን የጠቀስካቸው ነገሮች በሙሉ መልካም ነገሮች ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሮድ ብሎክስ ወይም መንገድ ላይ እንዳትሄድ የተደረደሩ ድንጋዮች ነበሩ፡፡ ለምንፈልገው መሠረታዊ ለውጥ መግቢያዎች ናቸው፤ መታመን ለመፍጠር ማለት ነው፡፡ በእኛና ከኢሕአዴግ ውስጥ ትንሽም ቢሆን አፈንግጦ የመጣውን የለውጥ ኃይል በእሱና በእኛ መካከል በጎ የሆነ መግባባት እንድንፈጥር፣ ተስፋ እንድንይዝ ይሄ መንገድ ላይ የተደረደረ እንቅፋት መነሣት ነበረበት፡፡

በግፍ ያሠርካቸው ዕስረኞች መፍታት ለውጥ አይደለም፤ ማሠርህ ስህተት መሆኑን መቀበል ነው ዋናው፡፡ ከእንግዲህ በኋላ ያለ ፍትህ ማንም አለመታሰሩ ነው ለውጥ የምንለው ነገር፡፡ ሚዲያውን መልቀቅ እኮ ሮድ ብሎክ ነው፡፡ ወያኔ እንደገባ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ በርካታ ጋዜጣና መጽሔቶች በአንድ ጀንበር እንዲወጡ አድርጎ እንደነበር እኮ መርሣት የለብንም፡፡ ደርግ ያስቀመጣቸውን የመንገድ ላይ እንቅፋቶች አንስቶ እኮ ነው ውስጣችን የገባው፡፡ በሕዝብ ተቀባይነቱን ካገኘ በኋላ የሠራንን ግን ሁላችንም አንረሳውም፡፡

**ግዮን፡- ታዲያ አዲሱ የለውጥ ቡድንም የተፈጸመውን ላለመድገሙ ምን ዋስትና ነበር?**

በዶ/ር ዐቢይና ጓደኞቻቸው የሚመራው ከኢሕአዴግ መሀል ያፈነገጠው የለውጥ ኃይል ራሱ አሁን ችግር ውስጥ ነው ያለው፡፡ ኢህአዴግ ውስጥ መከፋፈል በመኖሩ፡፡ ይሄ ኃይል መጀመሪያ ማድረግ የነበረበት እስረኞች እንዲወጡ በሩን መክፈት፣ ፓርቲዎች እንዲገቡ በሩን መክፈት ነውና ያንን አድርጓል፡፡ ከዛ በኋላ ግን ወደ ለውጡ ለመሄድ ይሄ የለውጥ ኃይል ከኢሕአዴግ የመጣ፣ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሲመራ የኖረ፣ ልማታዊ መንግስት እያለ በሙስና በነፈረቀ ቢሮክራሲ እየታገዘ ሢሠራ የነበረ ሥርዓት ውስጥ የመጣ ስለሆነ፣ የለውጡን ሂደት ለመጨረስ የሚረዳ የሽግግር ሥርዓት ለመመስረት የተወሰነ ፍኖተ ካርታ ማስቀመጥ ነበረበት፡፡

ገና ከጅምሩ ይሄንን ነው በሚዲያ ላይ የተናገርኩት፡፡ ፍኖተ ካርታ ያስፈልጋል ብለን በጩህን ቁጥር፣ መጨረሻ ላይ እንደውም "ፍኖተ ካርታ ብለው የሚጠይቁ ግራ የገባቸው ናቸው" እስከማለት የተደረሰበት ሁኔታ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ የመደመር ፍልስፍና ፍኖተ ካርታ ነው የሚሉ ሰዎች ብቅ ብለዋል፡፡ ይሄ መደመር የሚለው ጽንሠሃሳብ ስሙ እንደተጠራ፣ ፍኖተ ካርታ ሆኖ ከሆነ የምንሄደው አካሄድ እንዲህ ነው ተብሎ መነገር ነበረበት፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ መቅረት የለበትም፣ የነበረው የፌደራል አደረጃጀት በፍፁም መለወጥ የለበትም፣ ሕገ መንግሥቱ በፍፁም መነካት የለበትም" የሚሉ ኃይሎች እኮ ኢሕአዴግ (ብልፅግና) ውስጥ ነበሩ፡፡ እነሱን ያልያዘ ለውጥ የተከፋፈለ ቤት ነው የሚሆነው፡፡ መጀመሪያውኑ ፍኖተ ካርታው በመጠኑ ተገልፆ ቢሆን ኖሮ፤ ሥልጣን ላይ ያለው ቡድን የምንፈልገውን ነገር ነው ያደረገው፣ የተወሰነ ተስፋ ሰጥቶን እኮ ፈንጥዘናል በወቅቱ፡፡ ዛሬ ግን ግራ መጋባት ውስጥ ነው ያለነው፡፡ የእርቅና የሰላም ኮሚሽን፣ የድንበር ኮሚሽን ተብሎ ተቋቋመ፤ ግን እነዚህ ተቋሞች እየሠሩ ነው? በእኔ እምነት ከማያቸው ችግሮች አንፃር እየሠሩ ነው ማለት ያስቸግራል፡፡

ግዮን፡- በቀጣይ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት መከተል ስላለበት መንገድ ፣ ከግብፅ ጋር ስለተፈጠረው አለመግባባትና ስለተለያዩ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ስለአገሪቱ አጠቃላይ የፀጥታ መዋቅር የሰጡንን ማብራሪያ በሚቀጥለው ሳምንት ይዘን እንቀርባለን፡፡

# "ፊንፊኔ የእኔ ናት፣ ስትል 'እንተላለቃለን' የሚል ለሞቱ የቀረጠ ሰው ያስፈልጋል"

**አቶ ኤፍሬም ማዴቦ**

**በአርበኞች ግንቦት ሰባት ውስጥ የሕዝብ ግንኙነት ሓላፊ በመሆን የሠሩት፣ በፈታኙ የኤርትራ በረሀ ውስጥ ለሦስት ዓመታት የቆዩት አቶ ኤፍሬም ማዴቦ፤ ካለፈው ሣምንት በቀጠለው ክፍል ሁለት ቆይታችን አሁን ላይ አለ ስለሚባለው የተረኝነት ፖለቲካ፣ ብልፅግና ፓርቲ ህወሓትን ሳይዝ ስላደረገው ጉዞ፣ የብሄርተኛ ልሂቃኖች እሳቤና ፍላጎት በስፋት ይነግሩናል፡፡ በተጨማሪም ቀጣዩ አገራዊ ምርጫ ስለሚኖረው ፋይዳ ፣ የ"ኬኛ" ፖለቲካ አቀኝቃኞች ስለሚቋምጡላት አዲስ አበባ የባለቤትነት ጉዳይ እንዲሁም አገሪቱ ስላለችበት አጠቃላይ ፖለቲካዊ ገጽታ ከግዮን ጋዜጠኛ ሮቤል ምትኩ ጋር ያደረጉት ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ መልካም ቆይታ፡፡**

**ግዮን፡- የጠ/ሚ/ር ዐቢይ ቡድን ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ ብዙዎች ተስፋ ያደረጉበት ለውጥ እየደበዘዘ፣ ልክ እንደ ህወሓት ዘመን አሁን ላይ የኦሮሞ ብሔርተኝነትን የሚያንፀባርቅ፣ የተረኝነት ስሜት እየታየ ነው ይባላል፡፡**

አቶ ኤፍሬም፡- እንደሱ ሲባል እኔም አንዳንድ ቦታዎች ላይ እንደዚህ ዓይነት ምልክቶች ይታያሉ፡፡ ይሄ ነገር ሊመጣ እንደሚችል የሚያሳዩ፣ ኢትዮጵያን ወደ እዛ የሚገፉ ኃይሎች እንዳሉም መረዳት ደግሞ ያስፈልጋል፡፡ በመንግስት መዋቅር (ኦዴፓ) ውስጥ ሆነው፣ ኢትዮጵያ ወደ ተረኝነት ፖለቲካ መስመር እንድትገባ የሚፈልጉ ሰዎች ጭምር አሉ፡፡ ከኦዴፓ ውጭ ያሉ ትላልቅ ኃይሎች፤ ለምሳሌ አሁን ላይ ሕዝብ "እነዚህ ኃይሎች ካልጠፉ ኢትዮጵያ ሰላም አታገኝም" የሚላቸው ኃይሎች በኦዴፓ ሰዎች ጭምር (አሁን ወደ ብልፅግና ቢዋሃድም) ድጋፍ አላቸው፡፡

በግልፅ ሚዲያ ላይ፤ "ልጃችን፣ ወንድማችን" ሲባልም እኮ ሰምተናል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ባሉበትና ይሄንን የሚቃወሙ ኃይሎች ባሉበት፤ እኔ ብሔርተኝነት ወይም ተረኝነትን ከሚያራምደው በተቃራኒ ካለው ቡድን ጋር ነው የምቆመው፡፡ ኹለቱንም መደገፍ ተገቢ አይደለም፡፡

በፖለቲክስ የዛሬውን ትልቁ ጠላትህን ምናልባት ለወደፊት አላምደኸው፣ ዓላማህን ሼር ተደራርገህ፣ የአንተንም ቁስል አስረድተህ፤ አንድ ላይ በመሰለፍ ልትቀጥል የምትችልበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ይሄንን በደንብ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

አንተ የምትለው የተረኝነት ስሜት በግልፅ አለ፡፡ በቅርቡ ዳዊት አብደታና በቀለ ገርባ OMN ቲቪ ላይ ቀርበው "ብልፅግና ለኦሮሞ ሕዝብ የቆመ ፓርቲ አይደለም" ብለው ነበር፡፡ ታዲያ ለማን ነው የቆመው? ኦሮሞ የሌለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ አለ እንዴ? በቀለ ገርባ ይሄንን መንግሥት ወደ ሥልጣን ያመጣው ቄሮ ነው ይላል፤ ምን ማለት ነው ይሄ? የኢትዮጵያ ፖለቲካ የሚኖረው፣ የሚሞተው ለኦሮሞ ነው እንዴ? እነዚህ ሁሉ ኃይሎች የሚባለው የተረኝነት መንፈስ እንዲያንሰራራ የሚሹ ናቸው፡፡


ብዙ ጊዜ ሁሉን ነገር ያመጣው ቄሮ ነው ሲባል እንሰማለን፡፡ ይሄ ስህተት ነው፤ ቄሮ ያመጣው ነገር የለም፤ ሌላውም ያላመጣው ነገር የለም፡፡ በአትሌቲክስ አራት በአራት ዱላ ቅብብሎሽ ውድድር አለ፤ እዛ ውስጥ ማነው ያሸነፈው? ካልክ ሁሉም የቡድኑ አባላት ናቸው፡፡ ሲጀመር የሮጠውም፣ መጨረሻ የሮጠውም አትሌትም እኩል የወርቅ ሜዳሊያ ያገኛሉ፡፡ ቄሮ መጨረሻ ላይ ሮጦ ሊሆን ይችላል፤ የጀመረው ፋኖ ከሆነስ? መሀል ላይ ሚናውን የተጫወተው ዘርማ ከሆነስ? እነዚህ ግለሰቦችና ኃይሎች ግን ይሄን ሁሉ ረስተው ድሉንም፣ ኮንዶሚኒየሙንም፣ ለውጡም ከቄሮ ጋ ስለሚያገናኙ ሰዎች "ተራዬ ነው" ብለው እንዲያስቡ አድርጓል፡፡ እኔ ኤርትራ በረሃ እያለሁ ባህርዳር ላይ በተካሄደው ሰልፍ በአንድ ቀን 55 ሰው መሞቱን እንዴት መርሳት ይቻላል? የነሱስ ነፍስ አይደል? እነሱ ለዚህ ለታየው ለውጥ የከፈሉት መስዋዕትነት በምን ይለካል? ሁሉም በመስዋዕትነት ላመጣው ለውጥ የተረኛ ስሜት ማንፀባረቅ ተገቢ አይደለም፡፡

**ግዮን፡- ጠ/ሚ/ር ዐቢይ የኦዴፓ አባል የነበሩና ከኦሮሞ ማኅበረሰብ የወጡ መሆናቸውን ከግምት በማስገባት ተረኝነቱን ከቄሮ ባሻገር ወደ መንግሥታዊ መዋቅር የሚያሻግሩትስ እንዴት ይታያሉ?**

አቶ ኤፍሬም፡- ጽንፈኞች ዐቢይ አሕመድን ለሥልጣን ያበጣው ቄሮ ነውና፣ ጠ/ሚኒስትሩ ለኦሮሞ ሕዝብ መቆም አለበት ይላሉ፡፡ ዐቢይ የኢትዮጵያ መሪ ነው፣፤የሚቆመው ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለአገሪቷ ነው፡፡ ዐቢይ ለወላይታው፣ ለጉራጌው የሚቆመውን ያህል ለኦሮሞም፣ ለሲዳማውም፣ ለአማራም ሆነ ለትግሬው ይቆማል፡፡

የኢትዮጵያ ፖለቲካ አሁን እየተገፋ ወዳለው የብሔርተኝነት ስሜት ሳይሆን፣ ከዛ እንዲወጣ እና ወደ አንድነት መንፈስ እንዲመለስ ነው ፍላጎታችን፡፡

**ግዮን፡- የኢህአዴግ ሦስት ፓርቲዎችና በተለምዶ አጋር የሚሰኙት ፓርቲዎች በውህደት ብልፅግና ወደተሰኘው ፓርቲ የተለወጡበትን ሂደት እንዴት አዩት?**



አቶ ኤፍሬም፡- ኢሕአዴግ ከግንባርነት ወደ ፓርቲነት እንቀየራለን ብለው ጠ/ሚኒስትሩ መጀመሪያ ላይ ንግግር ሲያደርጉ በመልካም ጎኑ ነው ያየሁት፡፡ እውነቱን ለመናገር ኢትዮጵያን የብሔር ፖለቲካ በእጅጉ አበላሽቷታል፤ ከረዥምም ዘመናት በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ መጥቼ ነገሮችን ስመለከት፣ በዚህ መጠን በጎጠኝነት በሽታ መታመሙ በእጅጉ አሳዝኖኛል፡፡ እዚህ ኢትዮጵያ ተወልዶ ያደገውና የብሔር ፖለቲካ መጥፋት አለበት ብሎ የሚነግርህ፣ ከኢትዮጵያ ሳይወጣ ዕድሜው 40 የደረሰው ሰውም የብሔር ፖለቲካ አበላሽቶናል ይልሃል፡፡ ግን እርሱ ራሱ የሚያወራው የብሔር ፖለቲካ ነው፡፡ አብረህ ስትጫወት ትከርምና በማግሥቱ የሆነ ሰው ሲሾም፤ አማራ ከሆነ "አየህ ኦሮሞ ሾመ"፣ ኦሮሞ ከሆነ ደግሞ "አማራ ተሾመ" ይልሀል፡፡

እንዲህ አስተሳሰባችንና ሁሉ ነገራችን እስኪቀየር ድረስ የብሔር ፖለቲካ አበላሽቶናል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳውም፣ ማሽኑም ብሔርተኝነት ስለሆነ፡፡ የአሁኑ ብልፅግና ፓርቲ፣ አንድ ሰው በተሾመ ቁጥር የእከሌ ብሔር ስለሆነ ነው የሚለውን ስሜት ያጠፋልናል፡፡ ጫፍ ጫፍ የያዘውን የብሔርተኝነት እንቅስቃሴ ያደበዝዛል፡፡

ቀደም ሲል ኢህአዴግ ራሱ እኮ እንደ ኢህአዴግ ▶



አያስብም ነበር፡፡ አሁንም በዛ መንፈስ የኢህአዴጉን መሪ እንደ ኦሮሞ አስቦ፣ እንደ ኦሮሞ ግዛ እያሉት እኮ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ነገር የሚጠፋው በብሔር ያልተዋቀረ አንድ ወጥ ፓርቲ ሲኖር ነው፤ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከዚህ ኹለት ዋልታ ረገጥ ጫፎች ወደ መሀል ማምጣት የምንችለው እንደ ኢ.ዜ.ማ ዓይነት አገር ዐቀፍ ፓርቲዎች ሲቋቋሙ፣ እንደ ብልፅግና ያሉ ፓርቲዎች ሲመሰረቱ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ፓርቲዎች ውስጥ አባል ለመሆን ደግሞ ኢትዮጵያዊ መሆን ብቻውን በቂ ነው፡፡

ኢህአዴግ የራሱ የሆነ በሽታ ያለው በመሆኑ የሚታየው ችግር ሊቀጥል ይችላል፡፡ ኢትዮጵያ በዚህ ወቅት በጣም ትልቅ የሆኑ አራት አምስት አገራዊ ፓርቲዎች ያስፈልጋታል፡፡ የብልፅግና ፓርቲ በዚህ መልክ መምጣት ለኢትዮጵያ ፓርቲ ሥርዓት ዕድገት የሚኖረው አስተዋፅኦ የጎላ ነው፡፡ አሁን እየሆነ ያለውን የሚቃወሙት ጽንፈኛ ብሔርተኞች ናቸው፡፡ ጃዋር መሐመድ ኢህአዴግ ወደ ብልፅግና ሲመጣ "የኦሮሞ ጥቅም ተነካ" ነው ያለው፡፡ ጃዋር ሁሌም ኢትዮጵያን ሳያይ መጀመሪያ ኦሮሞን ነው የሚያየው፤ በቀለ ገርባ ኢትዮጵያን ሳያይ ኦሮሞን ነው የሚያየው፡፡

**ግዮን፡- ከኢትዮጵያ ይልቅ የኦሮሞ ብሔርተኝነት እያራገቡ ያሉት ጽንፈኛ ፖለቲከኞች በአቋም ደረጃ እርስ በርሳቸውስ ይግባባሉ? የምናያቸው የኦሮሞ ፓርቲዎች በብዛት ከኦነግ እየተሰጠቁ፣ እየተነጠሉ የመጡ ናቸውና፡፡**

አቶ ኤፍሬም፡- የሚግባቡ አይመስለኝም፡፡ አሁን በየመድረኩና በየቴሌቪዥን ጣቢያው የኦሮሞ ጥቅም ተነካ እያሉ የሚጮኹትን ወደ ሥልጣን ብታመጣቸው እርስ በርሳቸው ይጋጫሉ፤ ወደ አለመግባባት ነው የሚመሩት፡፡ የታገልነው ለኦሮሞ ነው ማለታቸውን ትተው፤ ጃዋር ወደ አሩሲ ያደላ፡፡ በቀለ ወደ ወለጋ ያደላ፡፡ አንዱ ወደ ቦረና፣ ሌላው ወደ ባሌ ያደላ፡፡ ወደ ታችኛው የጎጠኝነት ስሜት ወርደው በመንደር ማየት ይጀምራል፡፡

ቦረናም ስትለው የእኔ ነው፣ ደምቢ ደሎም ስትለው የእኔ ነው፣ ኦጋዴን፣ ትግራይ፣ ጉራጌ፣ አማራ ስትለው ሁሉም የእኔ ነው የሚል ፓርቲ መፈጠር አለበት የምንለው ለዚህ ነው፡፡ ብሔርተኛ ለጊዜው የተስማማ ቢመስልም መጨረሻው በትውልድ ቀዬ ተከፋፍሎ የኔ የኔ መባባሉ የማይቀር ነው፡፡

**ግዮን፡- የብሔር ፖለቲካ መንሰራፋቱን ወይም የበላይነትን ከአገሪቱ ማጥፋት ይቻላል ብለው ያምናሉ?**

አቶ ኤፍሬም፡- ቀደም ሲል በዚህ ወቅት ያሉት ዋነኞቹ የዜግነት ፖለቲካ ፓርቲዎች ኢዜማና ብልፅግና ናቸው ብለናል፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች ብቻቸውን በአንድ ጊዜ ይሄን የብሔርተኝነት ስሜት ያጠፋሉ ማለት አንችልም፡፡ ምክንያቱም 27 ዓመት ሙሉ የመከፋፈልና እርስ በርስ የመናጨት ሥራ ሢሠራ ነበርና፡፡

አንድ ሶስት ምርጫዎችን እንይ፤ ወደፊት ይሄ ነገር ከአንዱ ወደ ሌላኛው ምርጫ በተሻገርን ቁጥር እየጠራና ችግሮች እየተወገዱ ይሄዳል፡፡ ይህ እንዲሆን ጠንካራ ፓርቲዎች መፈጠር አለባቸው፡፡ እዚህ አገር ተቃዋሚዎችን ተፎካካሪ ይሉታል፤ የማይመች አገላለፅ ነው፡፡ ተቃዋሚ ተቃዋሚ ነው መባል ያለበት፡፡ ፓርላማው ውስጥ ሲገቡ የዛኛውን ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም ይቃወሙታል እንጂ አይፎካከሩም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ አማራጭ ሳይኖረው 27 ዓመት ሙሉ ከኢህአዴግ ብቻ ነበር የሚመርጠው፡፡ አሁን ግን አማራጭ ይኖረዋል፡፡ በዛው ልክ ደግሞ በዚህ ወቅት የብሔር የፖለቲካ ፓርቲዎች እየበዙ ነው፡፡ ግን እርግጠኛ ነኝ የጊዜ ጉዳይ እንጂ ወደፊት ሁሉም ነገር እየጠራ ይመጣል፡፡

ሰዎች ይቺን ምርጫ ብቻ ነው የሚያዩት፡፡ ለቀጣዮቹ 50 እና 60 ዓመታት ነው ማሰብ የሚያስፈልገው፡፡ ምን ያህል የአገራችንን የፖለቲካ ሥርዓት እንደሚያሳድጉት፣ ደካማ የዴሞክራሲ ባህላችንን ምን ያህል እንደሚቀይረው፣ ምርጫን ሰው ከምርጫ በፊትም ሆነ ከምርጫ በኋላ የሚያየው ጨዋታ መሆን ነው ያለበት፡፡

**ግዮን፡- የኢህአዴግ ወላጅ የሆነው ህወሓትን ያልያዘው ውሕድ ፓርቲ ምን ዓይነት ተግዳሮቶች ሊገጥሙት ይችላሉ?**

አቶ ኤፍሬም፡- ሦስቱ ፓርቲዎች ወደ ውህደት ሲመጡ እምቢ ብሎ የመጣው ህወሓት እንደሆነ መርሳት የለብንም፡፡ እምቢ ብሎ የወጣን አካል ጎትተህ አታመጣውም፡፡ ግን የትግራይ ሕዝብ ዕድል በህወሓት ብቻ ነው ብለን ማመን አንችልም፡፡ ለጥቂት ጊዜ ሊያስቸግሩ ይችላሉ፤ እነሱም እኮ ከ40 ዓመት በላይ ከትግራይ ሕዝብ ጋር የኖሩ ናቸው፡፡

ግን ትግራይ ውስጥ እንደ አረና ያሉ ሌሎች ፓርቲዎች ስላሉ፣ የትግራይ ሕዝብ አማራጭ ይኖረዋል፡፡ የግድ ህወሓት ብቻ ትግራይን የመወከል መብት አልተሰጠውም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ እኮ ከሦስት ዓመት በፊት አፉን አይከፍትም፣ በነፃነት አይናገርም ነበር፡፡ የትግራይ ሕዝብም አሁን አፉ በጫና ተለጉሟል፤ እንደ ልብ አፋቸውን ከፍተው ብሶታቸውን የሚናገሩበት ጊዜ ይመጣል ብዬ አስባለሁ፡፡

ህወሓት ብልፅግናን አልቀላቀልም ከማለቱ ባሻገር እንዲህ አደረጋለኹ፣ ይሄን እፈፅማለሁ፣ እያለ የማይጮኸው ጩኸት የለም፡፡ ግን ምንም ዋጋ አይኖረውም፡፡

**ግዮን፡- ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ስር እየሰደደ የመጣው የ"ፊንፊኔ ኬኛ" ፖለቲካን ተከትሎ፣ የሚነሳውን የአዲስ አበባ የባለቤትነት ጉዳይን እንዴት ያዩታል?**

አቶ ኤፍሬም፡- የፊንፊኔ ኬኛ ፖለቲካን በፍጥነት ያራገቡት እንደ በቀለ ገርባና ጃዋር መሐመድ ያሉ ጽንፈኞች ናቸው፡፡ ጃዋር ትልቅ ተከታይ ያለው ሰው ነው፡፡ ወደፊት ጃዋር ሊታሰር፣ በአክራሪዎች ሊገደል፣ ወይም የተለየ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ግን ጃዋር ቢሞትም፣ ዓላማው ግን አይጠፋም፤ የተከለው ሐሳብ አይደበዝዝም፡፡ ይሄን ትልቅ ተከታይ ያለውን ሰው ለማቆም ወደ ዋሽንግተን ዲሲ መሄድ አይጠበቅህም፤ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነህ ከእሱ የሚበልጥ ሰው አደራጅ፡፡ ያኔ ጃዋርም ሆነ ሌሎቹ ጽንፈኞች ማሰብ ይጀምራሉ፡፡

ጃዋር መቆሚያየችን ፊንፊኔ ነው ያለው፤ ተገቢውን አካል ስታደራጅበት ግን መቆሚያውም፣ መጀመሪያውም አዲስ አበባ እንዳልሆነ ያውቃል፡፡ በዚህች ከተማ ላይ የተደራጀ፣ "ፊንፊኔ የእኔ ናት፣ እወስዳለሁ፣ ብትል እንተላለቃለን" የሚል ለሞቱ የቆረጠ ሰው ያስፈልጋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የተደራጀ ኃይል ሀዋሳም፣ ድሬድዋም ሆነ የትም ቦታ እንዳለ ሲያውቅ እንቅስቃሴውን ማቆም ትችላለህ፡፡

እሱ እንዲህ የሚፎክረው OMN ቴቪን ስለያዘ ብቻ አይደለም፡፡ ሂድ ሲለው ወዴት? የማይል የተደራጀ መንጋ ስላለው ነው፡፡ ግደል ሲለው ለምን? የማይል ኃይል ስላለው ነው፡፡ ያንን ኃይል በጩኸት፣ ወይም ስለጠላንና ስለ ሰደብነው አናቆመውም፡፡ ማቆም ብቻ ሳይሆን መግፋት የምንፈልግ ከሆነ፣ በአዲስ አበባ የሁሉም ባለቤትነት ላይ የሚሠራ ኃይል ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ውጭ የአዲስ አበባ ባለቤትነት ጉዳይ ምንም የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነች፤ በተሳሳተ የታሪክ ትርክትና ተራ ፕሮፓጋንዳ መነዳት ተገቢ አይደለም፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

# ወታደሩና አርክቴክቱ የሚንጧት ሊቢያ

በዩክሬን ጦርነት ሰበብ ሩሲያን በማዕቀብ የቀጡት፣ በሶሪያው ጦርነት ሩሲያን የሚያወግዙት የጀርመን፣ የፈረንሳይ፣ የብሪታንያ መሪዎች እና የዩናይትድ ስቴትስ ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ከሩሲያው ፕሬዝዳንት ጋር በቅርቡ በርሊን ውስጥ እንደ ወዳጅ መክረዋል። በሊቢያ እና በሶሪያ ጦርነት ተቃራኒ ኃይላትን የሚረዱት የቱርክ፣ የፈረንሳይ፣ የሩሲያ እና የግብፅ መሪዎች እንደ ፖለቲካ ዲፕሎማሲው ወግ ተነጋግረዋል።

የአንዲት ሊቢያ የአንድ ዘመን ትውልዶች የተፋላሚ ኃይላት መሪዎች ግን ስለገዛ ሐገራቸው መነጋገር አይደለም አንድ አዳራሽ ዉስጥ አብሮ መቀመጥም አልፈለጉም። ምክንያቱም «ልዩነታቸው ስር የሰደደ ስለሆነ» ይላሉ የጀርመኗ መራሒተ መንግሥት አንጌላ ሜርክል።

«ከሁለቱም ጋር በተናጥል ተነጋግረናል። በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለው ልዩነት በጣም ሰፊ በመሆኑ አይነጋገሩም። የጉባኤው ተካፋዮችም አልነበሩም። ይሁንና እዚሁ በቅርብ ነበሩ፤ አንድ ክፍል ዉስጥ ግን አልነበሩም። እንዲያው የዉይይቱን ውጤት በቅርብ እንድንነግራቸው ብቻ እዚሁ በርሊን ነበሩ።» ይላሉ ሜርክል።

የሙዓመር ጋዳፊን ቤተ-መንግሥት የተባበሩት መግሥታት ድርጅት ያስረከባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ፋይዝ አል-ሰራጅ እና ያንን ዘመናይ ቤተ-መንግስት በኃይል ለመቀማት የሚዋጉት የጦር አበጋዝ ኸሊፋ ሐፍጣር የበርሊኑን ጉባኤ ለመታረቂያ ሳይሆን አስታጣቂ ረዳቶቻቸውን ለመማፀኛ ተጠቅመውበታል።

የዓለም ኃያላን በርሊን ላይ ሥለ ሊቢያ ውድመት በተነጋገሩበት ያለፈው ሰሞን የሐፍጣር ጦር 5 የነዳጅ ማምረቻና ማከማቻ ተቋማት ነዳጅ ዘይት እንዳይሸጡ አግዷል። ተቋማቱ በየቀኑ 800 ሺሕ በርሜል ነዳጅ ለውጪ ገበያ ይሸጣሉ። ለሊቢያ መንግሥት 55 ሚሊዮን ዶላር ያስገባሉ። ሐፍጣር እንደ ጦር አበጋዝ ወታደራዊ እርምጃ ሲወስዱ፤ አል ፈራጅ እንደ ሲቢል መሪ የተረፋቸውን አማራጭ ቀሰቀ፤ የተቃውሞ ሰልፍ በትሪፖሊ። የትሪፖሊ ነዋሪዎች ሐፍጣርን ያወግዛሉ። ጠ/ሚኒስትሩም «ተኩስ አቁም ይደረግ መባሉን አልደግፍም። ምክንያቱም ተኩስ አቁሙን ወንጀለኛዉ ሐፍጣር ትሪፖሊን ለመቆጣጠር እና ተጨማሪ ደም ለማፍሰስ፣ ጦር መሳሪያ ለማከማችትና ወታደሮቹን ለማደራጀት ይጠቀምበታልና።» ይላሉ።

ቤንጋዚዎች ባንፃሩ፣ አልሳራጅን ወይም ደጋፊያቸውን ቱርክን ያወግዛሉ። «ተቃውሟችን ለምዕራባውያን፣ ለፀጥታው ምክር ቤትና ለአዉሮፓ ሕብረት መልዕክት ለማስተላለፍ ነው። ቱርክ የኔቶ አባል



ብትሆንም፣ የቱርኩ ፕሬዝዳንት አጋጣሚውን በመጠቀም ጦራቸዉን ወደሊቢያ ለማዝመት ይፈልጋሉ" በማለት እየተናገሩ ነው።

ወታደሩና አርክቴክቱ እነማን ናቸው?

የግብፃዊ እናት-የሊቢያዊ አባት ውጤት የሆነው ኸሊፋ ቤልቃሲም ሐፍጣር በ1960 የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርቱን ለመከታተል ከሰሜን ምስራቃዊቱ የትውልድ መንደሩ አጅዳቢያ፣ የተሻለች ናት ወደምትባለው ደርና ከተማ ሲገባ 17 ዓመቱ ነበር። በዚያው ዓመት ደግሞ ከጥንቷ ጣራቦሊስ ቅኝ ገዢ ከቱርክ ደም የሚወርሱት የንጉስ ኢድሪስ ሐብታም ሚኒስትር መሐመድ አል ሳራጅ የወንድ ልጅ አባት ሆኑ። ስሙኑም ፋይዝ አሉት።

ፋይዝ እንደ ሐብታም ሚኒስትር፣ ከቱጃሮቹ ትምሕርት ቤት ፊደል ሲቆጥር፣ ወጣቱ ኸሊፋ ጦር ትምሕርት ቤት ገባ። በ1969 ሻለቃ ሙዓመር ጋዳፊ በመሩት መፈንቅለ መንግሥት የንጉስ ኢድሪስን ዘውዳዊ አገዛዝ ሲያስወግዱ ወጣቱ የጦር መኮንን ከጋዳፊ ቀኝ እጆች አንዱ ነበር።

ኸሊፋ እንደ ወታደር ምሽግ ገብቶ-እንደ ፖለቲከኛ ቤተመንግስትን የሚያማትረውን የናስር አስተምሕሮን ሲያቀነቅኑ፣ ፋይዝ ግን ትምሕርት ቤት እያማረጡ ዩኒቨርስቲ ለመግባት ይዘጋጁ ነበር። በውልደት ክልስ፣ ባመለካከት ቅይጥ የሆኑት የመስመር መኮንኑ ሶቭዬት ሕብረት ሔደው አብዮታዊ የጦር መኮንንነትን ተምረው ተመለሱ።

በ1973 አረቦች እና እስራኤል ሲዋጉ ሲና በረሐ የነበረውን የእስራኤል ጦር ምሽግ ሰብሮ የገባው የአረብ ጦር አባል በመሆናቸው ተሸልመው ተሾሙ። ኮሎኔል ሆኑ። በ1980 ቻድን የሚወጋውን ጦር እንዲያዙ ሲሾሙ፣ ፈይዝ አልሰራጅ በሥነ-ሕንፃ (አርክቴክቸር) ትምሕርት ከዩኒቨርስቲ ተመረቁ። ኮሎኔል ሐፍጣር ለድል ሲጠበቁ ተማረኩ። ከምርኮ ሲለቀቁ ወደ ሐገራቸው ከመመለስ ይልቅ ሐገራቸውንም መሪያቸውንም ከድተው፣ ለአሜሪካኖች አድረው በዛኢር በኩል ኬኒያ፣ ከዚያም ዩናይትድ ስቴትስ ገብተዉ የኮሎኔል ሙዓመር ጋዳፊን መንግስት ለማስወገድ ይጣጣሩ ገቡ።

የአሜሪካዉ ማዕከላዊ የስለላ ድርጅት CIA መረጃ አቀባይ (ሰላይ) መሆናቸዉ በሰፊዉ መነገር የጀመረውም ያኔ ነው። የኮሎኔል ማዕረጋቸዉን አውልቀዉ ሲቪል ሆኑ። በሊቢያዊነታቸዉ ላይ አሜሪካዊ ዜግነት ደረቡበት። የሥነ-ሕንፃዉ ባለሙያ ፋይዝ አልሰራጅ ግን በዚህ ሁሉ መሐል የሊቢያ የቤቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረባ ሆነው ይሰሩ ነበር።

በ2011 የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) ጦር የኮሎኔል መዓመር ጋዳፊን መንግስት ሲያስወግድ ሊቢያዊዉ፣ አሜሪካዊዉ፣ ሱፍ ከራባት አጥላቂዉ ኸሊፋ ሐፍጣር የጄኔራልነት ማዕረግ ለጥፈዉ ቤንጋዚ ላይ ብቅ አሉ።

ከ2014 ጀምሮ አልሰራጅ የፖለቲካ ኃይልና ተጣማሪ እየቀያየሩ የትሪፖሊን ፖለቲካ ሲዘውሩ ሐፍጣር ከቤንጋዚ ተቀናቃኞቻቸውን ተራ በተራ እያጠፉ ኃይላቸውን ያጠናክሩ ነበር። አልሰራጅ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰየመውን የብሔራዊ ስምምነት መንግሥትን የመሪነት ሥልጣን በ2015 ሲይዙ፤ ሐፍጣር ቶብሩክ የከተመው ምክር ቤት የጦር አዛዥ ሆነው የአልሰራጅን መንግስት ለማስወገድ ይዝቱ ገቡ።

አሁን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሊቢያ ተዋጊዎች ላይ የጦር መሳሪያ ሽያጭ ማዕቀብ ጥሏል። ግብፅ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች፣ ዮርዳኖስ፣ እስራኤል፣ ፈረንሳይ እና ሩሲያ ግን ሕግ ጥሰው ሕጋዊ እውቅና ያለውን መንግሥት የሚወጋውን የኸሊፋ ሐፍጣርን ጦር ከማስታጠቅ የከለከላቸው ሕግ፣ ደንብና ሥነ ምግባር የለም። ባለፈው ታሕሳስ የጥንቷ ጣራቦሊስ የጥንት ቅኝ ገዢ ቱርክ "ሕጋዊውን" የትሪፖሊ መንግስትን ከሐፍጣር ጦር ጥቃት የሚከላከል ጦር እንደምታዘምት ስታስታውቅ ደግሞ የምሥራቁም የምዕራቡም ኃያላን፣ ዓረቡም፣ ይሁዲውም ተነቃነቀ።

የአንካራና የሞስኮ መሪዎች የሊቢያ ተፋላሚ ኃይላትን ተኩስ እንዲያቆሙ ማስገደዳቸው፣ ንቅናቄው ለሰላም ወዳዶች "ሳይደግስ አይጣላም" ዓይነት ሆኖ ነበር። ይሁንና ከሳምንት በፊት ተኩስ አቁሙን በፊርማ ለማፀደቅ ሞስኮ ላይ የተጠራውን ድርድር የጦር አበጋዝ ኸሊፋ ሐፍጣር ማቋረጣቸው ተስፋውን በተስፋ ያስቀረው መስሏል። ከቀናት በፊት በርሊን ላይ የተደረገው ዓለም አቀፍ ጉባኤም የሞስኮውን ጅምር የሚያጠናክር፣ የተኩስ አቁሙንም የሚያፀና መሆኑ በሰፊው ቢነገርለትም ዘላቂ መፍትሄ አይሆንም። የቃላት ጦርነቱም የስምምነቱን ይስሙላ እንጂ ለዘላቂነቱ ዋስትና አይሰጥም።

ኪነ-ጥበብ

# “ርዕስና ጭብጥ የተጠሙት” ፊልሞቻችን ጉዳይ !




የኢትዮጵያ ፊልም ኢንዱስትሪ ዘመናትን ወደኋላ መቁጠር የሚችልበት ረጅም ዕድሜ ያለው ቢሆንም፤ ከቆየበት ዕድሜ አንጻር ይሄ ነው የሚባል የዕድገት ታሪክ የለውም፡፡ እነሚሼል ፓፓታኪስ ዓለምአቀፋዊ የፊልም (ሲኒማ) ደረጃን የሚያሟላ “ኢትዮጵያዊ የአማርኛ ፊልም” የሰሩበትን ዘመን ስናስብ ኢንዱስትሪው የተጓዘበትን የኋልዮሽ እርምጃ እንጂ አንዳች የፊት ተራማጅነት ኖሮት አናገኘውም፡፡ ለምን? ቢሉ… ዝርዝር ጉዳዩ እጅግ ብዙና ውስብስብ ነው፡፡

ለኢትዮጵያ ፊልም ኢንዱስትሪ አለማደግ ይበልጡንም “መቀጨጭ” (ወደኋላ መጎተት) በዋናነት ከሚጠቀሱ መሠረታዊ ምክንያቶች መካከል ብዙሃን የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት የመንግሥት ትኩረት አለመስጠት አንዱ ነው፡፡ ኢንዱስትሪው ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገትና ለገፅታ ግንባታ ያለውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ከግምት ማስገባት ያቃተው (እያወቀም እንዳላወቀ ሆኖ ማለፍን የመረጠው) መንግሥት ኢንዱስትሪውን በማሳደግና በመደገፍ ሁለንተናዊ የሀገር ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ ይልቅ በተቃራኒው እንደቅንጦትና አላስፈላጊ (ወይም ትርፍ ነገር) ቆጥሮ በመንቀሳቀሱ ትልቅ ሆኖ የተጀመረው የሀገራችን ፊልም ታሪክ ዛሬ ላይ ገና “ዳዴ እንደሚል ህፃን መሬት ለመሬት የሚንፏቀቅ” ሊሆን ችሏል፡፡ መደገፍና ማሳደግ ቀርቶ ቢያንስ “ነፃ” እንዲሆን ባለመፈቀዱም ፊልሞቻችን “የፊልም ገበያ” ላይ አተኩረው “የመንደር ጨዋታና የሰፈር ተረብ ላይ ሙጢኝ እንዲሉ” ተገፍተዋል፡፡

በርከት ያሉ የፊልም ደራሲያንና ፕሮዲዩሰሮች እንደሚሉት ኢትዮጵያ ውስጥ በአብዛኛው ፊልም የሚሰራው የገንዘብ ትርፍ ለማግኘት እንጂ የአገራችንን ባህልና አኩሪ ታሪክ ለትውልድ ለማቆየት በማሰብ አይደለም፡፡ በኢንዱስትሪው የላቀ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሱት የሆሊውድ አንቀሳቃሾች የራሳቸውን ሰርተው ጨርሰው፣ የእኛንም ወስደው፤ በፈለጉት መንገድ አበጃጅተው አብቅተው ወደ ሳይንስ ፊክሽን በገቡበት በዚህ ዘመን የእኛ ፊልም ዛሬም ሀብታም ሴት ከደሃ ወንድ ፍቅር ይዟት መንደር ለመንደር “ስትርመጠመጥ” ከማሳየት የዘለለ ፋይዳ ያለው መሳጭ ታሪክ መንገር አቅቶት ሲንደፋደፍ ይታያል፡፡

ተዝቆ የማያልቅ የተፈጥሮና ሠው ሠራሽ ሀብቶች ባላት አገር፣ ከ80 በላይ ቋንቋና ማንነት ያለው ህዝብ በሚኖርባት የባህልና ወግ ሀብታም ምድር በሰፈር ውስጥ ተረብ እና ስላቅ የተሞሉ ፊልሞች ገበያውን ተቆጣጥረውት ማየት በርግጥም ያስቆጫል፡፡ የፊልም ሰሪውም “የተመልካቹም?” ፍላጎት ተመሳሳይ ሆኖ የመገኘቱ እውነት ደግሞ ከማሳዘንም በላይ ሀፍረትን ይፈጥራል፡፡ ለዚህ ሁሉም ተጠያቂ ነው ቢባልም ቢያንስ በተቆርቋሪነት ስሜት ለውጥ ለመፍጠር የሚፈልግ አለመነሳቱ ደግሞ ተስፋ ያስቆርጣል፡፡ የሆነው ሆኖ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ተሠርተው የሚወጡት ፊልሞቻችን ከመጀመሪያው ይዘው የሚነሱት መነሻ ሀሳብ እንቶ ፈንቶ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለእይታ በሚበቁ ጊዜ ይዘው የሚወጡት ርዕስ በራሱ አስገራሚ ነው፡፡ ብዙዎቹ የሀገራችን ፊልም ፀሐፊያን ሲኒማቸውን የሚፅፉት በተመረጠ ርዕስ ስር ሆነው ባለመሆኑ ሲጀምሩ የሰጡትን ርዕስ፣ ጽፈው ሲጨርሱ እንዲቀይሩት የሚገደዱበት ተደጋጋሚ አጋጣሚ ይስተዋላል፡፡ ሀብታሟ ሴት ደሃውን ወንድ በፍቅር ለማጥመድ የምታደርጋቸውን ጥረቶች ለማሣየት ታስቦ የተጀመረ ፊልም ምናልባት መሀል ላይ ከዋናው ገጸ ባህሪ ጓደኛ ጋር በሚፈጠር የፍቅር ታሪክ ሊደመደም ስለሚችል የመጀመሪያው ርዕስ ዋጋ ቢስ ይሆናል፡፡ ስለዚህም ብዙዎቹ ፊልሞች ሲፃፉ እና አልፎም በቀረፃ ጊዜ የሚኖራቸቸው ርዕስ “ጊዜያዊ” ሆኖ ነው ስራው (ቀረፃው) የሚያከናውነው፡፡ በዚያ ላይ ፊልሙን ወደ ገበያ ለማስገባት ያግዛሉ የሚባሉት ፕሮሞተሮችና የሲኒማ ቤት ባለቤቶችም ርዕሱን የማስቀየር ስልጣናቸው ከፍተኛ በመሆኑ ፊልሞቻችን ተሠርተው ካላቁ በኋላ ሌላ ርዕስ ፍለጋ መኳተናቸው የተለመደ ሆኗል፡፡

በዚህ መነሻነት (በፕሮሞተሮቹና የሲኒማ ቤት ባለቤቶቹ) ተፅዕኖ ለአፍ ቀለል ያለ እና በሰፊው የተለመደ ቃል (ርዕስ) ለመስጠት ፍለጋው ይቀጥላል፡፡ ተደጋግሞ እንዳየነውም የታዋቂ መጽሐፍ ወይም የተወዳጅ ሙዚቃ ርዕስ፤ የፊልማችን ርዕስ ሆኖ ብቅ ይላል፡፡ ላምባዲና፣ ሼመንደፈር፣ እቴጌ፣ አስታራቂ፣ ዳገቱ ላይ፣ ሕይወቴ፣ ብርርር፣ ጊዜ ለኩሉ፣ አቡጊዳ… ወዘተ የተሰኙት ፊልሞች ከሙዚቃ ርዕስ የተወሰዱትም ለዚሁ ነው፡፡ ዞር ስትል ደግሞ ፍቅር በዝቶብን ጠብ የተጠማን ይመስል “ይዋጣልን” ይልሃል፡፡ “ሱማሌው ቫንዳም” የሚልም አለልህ፡፡ አበዛኸው አትበሉኝና “ሚስት ጨርሰናል” ብሎ ርዕስ መስጠት ክብረ ነክ ነው፡፡ ሴትን ልጅ እንደ ሸቀጥ ዕቃ ከመቁጠር የዘለለ ትርጉም አይሰጥም፡፡ “በራብሽ” ብሎ ርዕስ መስጠትስ ምን የሚሉት ነው?

የስድብ ቃላትም ርዕስ እንዲሆኑ ይመረጣሉ፡፡ በአፍ ለመናገር የሚያሳፍሩ የስድብ ቃላት የፊልም ርዕስ ሆነው በሚወጡባት ሀገራችን “ትችት ነውር ተደርጎ የታወጀ ይመስል” ማንም በዚህ ጉዳይ ሀሳብ ሲሰነዝር አለመታየቱም ፊልመኞቹ በተግባራቸው እርግጠኝነት እንዲሰማቸው የልብ ልብ ሰጥቷል፡፡ “የሌባ ልጅ” የሚል ርዕስ ያለው ፊልም በመንግሥት ሲኒማ ቤቶች ጭምር ቁጠማ ተጎዝጉዞ፣ ቀይ ምንጣፍ ተነጥፎ ተመልካችን ወረፋ ሲያስጠብቅ ማየት ኢንዱስትሪው የት ድረስ እንደዘቀጠ የሚነግረን እንጂ ሌላ ትርጉም ሊሰጥ አይችልም፡፡

ርዕስና ጭብጥ የተጠሙት ፊልሞቻችን ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በታሪክ አወቃቀራቸው ምንም የሚናገሩት (የሚያስተላልፉት) ጠቃሚ ሀሳብ የሌላቸው ከመሆኑም ባሻገር በቴክኒክ በኩልም አንዳች አዲስ ነገር አያሳዩም፡፡ የተለመደ (የተሠለቸ) አንድ ዓይነት ፊት እና ከቃላት ውጪ የትርጉም ልዩነት የሌላቸውን ንግግሮች ከማስደመጥ የዘለለ ቅንጣት ታክል “ፐ!” የሚያስብል አዲስ አይነት የቀረፃና የዳይሬክቲንግ ጥበብ አናይባቸውም፡፡ ሁሉም ሳይሆኑ በአብዛኛው እንዲያ ናቸው፡፡

ኳስ ሜዳው ላይ የቀበሌ ጽ/ቤት የተገነባበትና ራሱን ዘና የሚያደርግበት ምንም አማራጭ ያጣው ተመልካች ወረፋ ይዞ ገብቶ ያንቀላፋል፡፡ ከሲኒማ ቤት ውጪ ከፍቅረኛው ጋር ስለፍቅር የሚያወጉበት መናፈሻ ያልታደለው ወጣት ትናንት ያየውን የፊልም ታሪክ ዛሬ በሌላ ርዕስ ከመድገም ውጪ አማራጭ የለውምና ከሲኒማ ቤቶች ደጅ ይሰለፋል፡፡ ፊልም ሰሪዎቹ ግን ዛሬም ስለትውልድ መቆርቆርን ማሰብ አይፈልጉም፡፡ ተመልካች መሄጃ አጥቶ እንጂ ፊልማቸው ማርኮት እንዳልመጣ የማሰቢያ ጊዜ ያገኙ አይመስሉም፡፡ ሁሌ ገቢና ወጪያቸውን እንጂ ስለሀገር ገፅታ ግንባታ፣ ስለባህልና ማንነት፣ ወቅታችን ስለሚፈልገው አንድነትና የህዝቦች አብሮ መኖር ደንታ የላቸውም፡፡ ግን …እስከመቼ!

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢው ፊታውራሪ



ብሩክ መኮንን

ሰውየው በአሰላሳይነታቸውና በነገር አዋቂነታቸው ነው ድፍን ጦቢያ የሚያውቃቸው፡፡ በተለይ ደሞ ሀገርና መንግሥት በችግር ውስጥ ሲሆን በሚሰጡት የመፍትሔ ሀሳብና ከችግር ማምለጫ መላ ምክንያት "አባ መላ" የሚል ቅፅል ስም አግኝተዋል፡፡

እኚህ የኂለኛው ዘመን የጦር አዛዥ ለዓመታት "ኢትዮጵያ ትፈርሳለች" ተብሎ ሲሟረት ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን በምክር አንዳንዴም ደሞ ጦር በማዝመት ጭምር ተልዕኳቸውን በብቃት የተወጡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ የጦር ሚኒስትር በመሆን ሀገራቸውን እስከ እለተ ሞታቸው በታማኝነት አገልግለዋል፡፡

ዳግማዊ አፄ ሚኒልክ በሞቱ 13ኛው ዓመት ላለፉት አስራ ሁለት አመታት ሲያደርጉት እንደነበረው የዳግማዊ አፄ ሚኒልክን የሙት ዓመት በማሰብ በመኖሪያ ቤታቸው የአዲስ አበባ ሕዝብን መኳንንቱን መሳፍንቱን ሲያበሉና ሲያጠጡ ለነዳያንም ምፅዋት ሲሰጡ አምሽተው ምሽት ላይ የቤታቸው ሰራተኞች የጦር አዛገሮቻቸው ቤተዘመድ ጋር ሲያወጉ አምሽተው ነው በተወለዱ በ75 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ፤ ፊታውራሪ ኃብተጊዮርጊስ፡፡

ከጥቅምት 6 ቀን 1919 ጀምሮ በካንሴር ዲ ፒሎር የተባለ በሽታ ታመው ለሁለት ወራት እቤት ያዋላቸው ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ከዚህ አለም በሞት እንደተለዩ በመኖሪያ ቤቸው የተሰባሰቡ ሹሞቻቸው መድፍ በመተኮስና ነጋሪት በመምታት ነበር ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሚኒልክና አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን የጦር ሚኒስትራቸው የመሞታቸውን ዜና ያረዱዋቸው፡፡

ልዑል አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን ከቤተመንግስት ተነስተው ወደፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ቤት ተሻግረው አስከሬናቸውን በታላቅ ክብር አሸክመው ወደ ገነተ ፅጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አስወሰዱ፡፡ አልጋወራሹ በፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ሕልፈት በጣም በማዘናቸው የቀብር ስነስርዓታቸው ተገቢው መንግስታዊ ክብር የሚያሳይ ሆኖ እንዲፈፀም ቢትወደድ ፊታቸውንና ክቡር ደጃዝማች ወልደፃዲቅን አዘዙ፡ ፡

የፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ አሽከሮች ከቤታቸው ጀምሮ እስከቤተክርስቲያኑ ድረስ በሠልፉ ቀን እንደሚደረገው ጠመንጃቸውን ይዘው መትረየሶቻቸውን ተጭኖ ሌላው መሳሪያ ሁሉ በተራ በተራ ሆኖ የራስ ወርቃቸውንና ኒሻኖቻቸውና ሜዳሊያዎቻቸው ከባለንቃው አንፋሮ ጋራ በወርቅ ፈርጥ ያጌጡ ጋሻዎቻቸውን ተይዞ ነበር፡፡

ባለቤታቸው ወይዘሮ አልታየወርቅ የባላቸውን ግምጃ ሱሪ በአንገታቸው ይዘው መለከቱ ጡሩንባው እምቢልታው የሐዘን ዜማ እያዜመ አስከሬኑ የያዘው ሰረገላ ዙሪያ እየተመላለሱ ባለቀሱ ጊዜ መኳንንቱም ሕዝቡም በጣም ሲያሳዝኑትና ሲያስለቅሱት ዋሉ፡፡

ታህሳስ 4 ቀን 1919 የቀብር ሥርዓታቸው መፈጸሙን ተከትሎ "የውጭ መንግስታት መልዕክተኞች ከጠዋቱ አራት ሰዓት ከዳግማዊት ንግስተ ነገስት ዘውዲቱ ሚኒሊክና ከአልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን ጋራ በመኖሪያ ቤታቸው ለቅሶ ደርሰው ተመለሱ" ሲል በቀጣይ ሳምንት ታህሳስ ስምንት ቀን 1919 የታተመው የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ሰራተኛ አመት ቁጥር 10 ዕትሙ ዘግቧል፡፡

ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ከአባታቸው አቶ ዲነግዴ በተራ ከእናታቸው ወይዘሮ ኢጁ



አሚር በ1844 ተወለዱ የልጅነት ጊዜያቸውን እዚያው በተወለዱበት አከባቢ ያሳለፉት ኃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ምኒልክ "የሸዋ ንጉሥ" ተብለው እንደነገሱ ግዞታቸውን ለማስፋፈት በተካሄደ ጦርነት በጅባትና ሜጫ በአሁኑ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ልዩ ስሙ ፊልጡ በተባለ ቦታ ተማረኩ፡፡

የማረካቸው የምኒልክ ወታደር አያ አይተንፍሱ ይባላል፡፡ ታዳጊውን ኃብተጊዮርጊን ወደ መኖሪያ ስፍራው በመውሰድ ከልጆቹ ሳይለይ ያሳድገው ጀመር፡፡ በፈረስ ግልቢያ በጉግስና በግብርና ሥራ በጦር ውርወራ የሚወዳደረው የሌለው በማራኪው የመኖሪያ አከባቢ በአጭር ጊዜ ውስጥ ታዋቂ የሆነው ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ብዙም እዚያ ሳይቆይ ነበር፡፡ አፄ ሚነልክ በጦርነት የተማረኩ ልጆችን ወስደው የሚያሳድጉ ሥራ የሚያሰሩ ወታደሮች በአስቸኳይ ምርኮኞቹን ልጆች ወደ ቤተመንግስታቸው እንዲያመጡ የሚጠይቅ አዋጅ ያስነገሩት፡፡

በእርግጥም ከባልቻ ሳፎ እና ከሌሎች በጦርነት ከተማረኩ የምዕራብ ሸዋ አከባቢ ተወላጆች ውስጥ በቤተመንግስት ሹማምንት እውቅና ተቀባይነት አግኝተው ባልቻ አባነፍሶ በቤተመንግስቱ ግምጃ ቤት ኃላፊነት ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ በንጉሰነገስቱ የባልደራሶች አዛዥ በመሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ የንጉሰነገስቱ ባለሟል ለመሆን በቁ፡፡

በአደዋ ጦርነት ወቅት የንጉሰነገስቱ ተከታይ በመሆን የዘመቱት ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ በአድዋ ላይ ባሳዩት ጀግንነት በሚሰጡት ምክርና የነገር አዋቂነት ችሎታቸው የተደነቁት አፄ ሚኒልክም ለኃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ የፊታውራሪነት ማዕረግ በመስጠት ካሏቸው የጦር አዛገሮች አንዱ አደረጓቸው፡፡

በኢትዮጵያ የሚኒስትርነት ሹመት በተጀመረ ጊዜ የጦር ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ፡፡ ከዚያም በኂላ በፊታውራሪነታቸው የራስወርቅ አስረው የራሶችን ማዕረግ ተቀበሉ፡፡ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ በራሳቸው የሚታዘዙ 17 ሺህ ጦር የነበራቸው ሲሆን ምኒልክ የትውልድ ስፍራቸውን የጅባትና ሜጫን ግዛት እንዲያስተዳድሩ ሾመዋቸው ነበር፡፡

አፄ ሚኒልክ በሕመም ምክንያት አልጋ ላይ መዋላቸውን ተከትሎ በሀገሪቱ ያሉ መሳፍንትና መኳንንት ወራሴ መንግስቱ ለእኛ ወገን ሊሆን ይገባል በሚል የስልጣን ሽኩቻ እየታመሰ እያሉ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ከመጠበቅ ከውጭ ሀይሎች ጥቃት የመጠበቅ ኃላፊነታቸውን በብቃት ለመወጣት ከመትጋት በቀር ለስልጣን ሽኩቻው ውስጥ ተሳታፊ ሳይሆኑ ነበር የቆዩት፡፡

ነገር አዋቂው አባመላ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ በወቅቱ በነበረው የስልጣን ሽኩቻ ሳቢያ ለጦር ሰራዊት ደሞዝ ሳይከፈለው ወራት በመቆጠሩ ውስጥ ውስጡን ይታይ የነበረው ፀረ መንግስት እንቅስቃሴ ገና በእንጭጩ መፍትሔ እንዲያገኝ በማድረግ በፈፀሙት ፖለቲካዊ ጥበብ የተሞላ ተግባራቸው በወቅቱ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ መንግስት ባለሙሉ ስልጣን ሚኒስትር የነበረው ፈረንሳዊ ዲፕሎማት መንግስቱ በላከው ሪፖርት አድናቆቱን ገልጿል፡፡

እቴጌ ጣይቱ ብጡል ከስልጣን ተወግደው የባላቸው የዳግማዊ አፄ ሚኒልክ አስከሬን በክብር በሥዕል ቤት ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን ተቀምጠው ወደ እንጦጦ በግዞት ከተላኩ ከወራት በኂላ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ እቴጌይቱን እጅ ለመንሳት እጅ መንሻ ይዘው ወደ እንጦጦ አምርተው ነበር፡፡

እቴጌ ጣይቱ ፊታውራሪ ኃብተጊዮርጊስ ከስልጣን እንዲወገዱ የመከረው ጉባኤ ላይ የነበራቸውን ሚና ስለሚያውቁ ከፍተኛ ቅሬታ ስለነበራቸው ከብዙ መግባባት በኂላ ነበር ሃብተጊዮርጊስ ወደ እልፍኛቸው ገብተው ተቀብለው ያነጋገሯቸው፡፡


ልጅ ኢያሱ ሚካኤል ከስልጣን ከተወገዱ በኂላ አባታቸው በሸዋ ላይ ጦር በማዝመታቸው ዜና እንደተሰማ ወደ ሰገሌ ከመዝመታቸው በፊት እቴጌ ጣይቱ እንዲያማክሯቸው ወደ እንጦጦ ሄደው "ምን እናድርግ" ብለው ሲጠይቁ ሚካኤል ጀግና ነው እናንተ ጦሩ ወደዚያ መሔድ የለባችሁም እሱ ራሱ ወደዚህ ይመጣል እዚህ ተዘጋጅታችሁ ጠብቁት ብለው ምክር ሰጡዋቸው፡ ፡ ይህንንም ተከትሎ ነሐሴ 4 ቀን ደሴ ላይ ከንጉስ ሚካኤል ጋር ተዋግተው የንጉስ ሚካኤልን ጦር ድል አድርገውና ማርከው በድል አድራጊነት ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡

ለዓመታት የሚኒስትሮች ም/ቤት ሰብሳቢ የነበሩት ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ይህ ከሆነ ከ10 ዓመት በኂላ ነበር ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት፡፡ ኃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ከሞቱ በአርባኛው ቀን ቤተዘመዶቻቸውና ወዳጆቻቸው ተሰብስበው በሀገራቸው ወግና ልማድ መሰረት በሟቹ ቤት የአርባ ቀን መታሰቢያ አደረጉ፡፡ በእለቱ አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን ራስ ካሳ ጭምር በፊታውራሪ ቤት በመገኘት ካህናቱን ነዳያኑን ሲያበሉ ሲያጠጡ ዋሉ ጥር 16 ቀን 1919 በንጉስ ወልደጊዮርጊስ ቤት አጠገብ በሰፊው ሜዳ ላይ ትላልቅ ድንኳኖች ተተከሉ፡፡

አልጋወራሹ ከነመኳንንቶቻቸው ከጧቱ 12 ሰዓት ወደ ድንኳኑ ደርሰው በተዘጋጀላቸው ስፍራ ተቀመጡ በዚያን ጊዜ የፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ሰራዊት እንደጦርነት ጊዜ አሰላለፉ ተሠልፎ የጦር መሳሪያውን ሁሉ ተጭኖ የፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ የማዕረግ ልብሶች ዋናዋና ጌጣጌጦች የወርቅ እቃቸው በበቅሎዎቻቸው እየተጫኑ በልዑል አልጋወራሹ ፊት በሰልፍ አለፉ፡፡

ከዚያም በኂላ የፊታውራሪ ኃብተጊዮርጊስ ከመታመማቸው በፊት ተናዘው በፅሁፍ ያስቀመጡት ትዛዛ ወራሾች እንዲሁም አማኞች ባለበት እንዲነበብ ከታላቁ ቤተመንግስት እንዲመጣ ተደርጎ ኑዛዜውን ተነበበ፡፡ ይኸው ኑዛዜም በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ ጥር 21 ቀን 1919 ታትሞ በመውጣት የመጀመሪያው ኑዛዜ ሆኖ በታሪክ ተመዝግቧል፡፡

# ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከ1968- 2012



ሁሴን ከድር

ሰሞኑን በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ዘንድ አዲስ ታሪክ ተመዝግቧል፡፡ ለ44 ዓመታት ሲታሽ የቆየ ‹‹የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች››ን ሕጋዊ ሰውነት የመስጠት ጥያቄ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ምላሽ ያገኘው ባሳለፍነው ሳምንት ነበር፡፡

ይህንን ተከትሎ ባለፈው ቅዳሜ ጥር 14 ቀን 2012 የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች የምስጋና ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል፡፡ በጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የጊዜያዊ መጅሊሱ ሊቀመንበር ሙፍቲሕ ሐጂ ዑመር ኢድሪስ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ባለፉት ግማሽ ክፍለ ዘመን የተጓዙበትን የእድገት ደረጃ በውስን ቃላት አስቀምጠዋል፡፡

በንጉሡ ዘመን በ1961 ቅዱስ ቁርአን በአማርኛ ተተረጎመ፤ በንጉሡ መውደቂያ ዋዜማ 1966 በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመርያ ጊዜ በሚል ታሪክ የሚዘግበው ሰላማዊ ሰልፍ ተደርጎ ሙስሊሙ ለጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ካቢኔ 13 ጥያቄዎችን በማቅረብ ምላሽ መጠባበቅ ጀመረ፡፡ በ1968 ‹‹የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠ/ም/ቤት›› በደርግ የሥልጣን ዘመን መጀመርያ ላይ ተቋቋመ፣ ሦስት የሙስሊም በዓላት (ኢድ አልፈጥር፣ አረፋ እና መውሊድ) ብሔራዊ በዓል ሆነው እንዲከበሩ ታወጀ፣ እዚህ ላይ ትዝታቸውን ከነገሩኝ ጥቂት ሰዎች ያስታወስኩትን ላውጋችሁ፡-

በአጼ ኃ/ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን ለሙስሊም በዓላት በብሔራዊ ደረጃ እውቅና ተሰጥቶት መ/ቤትም ሆነ ት/ቤት ተዘግቶ አይከበርም ነበር፡፡ በዘመኑ የነበሩ ሙስሊሞች የመንግሥት መ/ቤቶች፣ ፍ/ቤት፣ ት/ቤቶች… ክፍት በመሆናቸው ሙስሊሞች በዓላችን ነው ብለው መቅረታቸው ለቅጣት ይዳርጋቸው ነበር፡፡ በተለይ የፍ/ቤት ቀጠሮ ኖሮባቸው ጉዳያቸው በበዓሉ ቀን ከዋለ በዓሉን ትተው ፍ/ቤት በር ላይ የመቆም ግዴታ ነበረባቸው፡፡ ይህ እውነታ ለዚህ ዘመን ሰው እንደ ቀልድ ይቆጠር የይሆናል፡፡ በበዓሉ ቀን በት/ቤቶች አስተማሪዎች ፈተና ሰጥተው ከነበረም ሙስሊም ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸው ላመለጣቸው ፈተና በውጤት እንዲያንሱ ይሆኑም ነበር፡፡ ይህን በተመለከተ በርካታ ጸሐፊያን በሕይወት ታሪክ ዶሴያቸው ላይ አስፍረው እናገኛለን፡፡

ወደ ታሪካዊ ለውጦች ስንመለስ በሚያዝያ 1966 ታላቅ የሙስሊሞች ሰላማዊ ሰልፍ የተገኙ ድሎች እነዚህ ብቻ አልነበሩም፡፡ ‹‹በኢትዮጵያ የሚገኙ እስላሞች›› የሚለው የማናናቂያ መጠሪያም ወደ ‹‹ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች›› ተለወጠ፡፡ ይህ የሚፈጥረው የሞራል መነቃቃት ቀላል አይሆንም፡፡ በመስጅድ ይደረግ የነበረው የሐዘን ወቅት የመድፍ ተኩስ እንዲቀርና መድፍ ለበዓላት ማድመቂያ በማዘጋጀ ሜዳ (በአሁኑ ወቅት የአድዋ ሙዚየም እየተሰራበት የሚገኘው ቦታ ቀድሞ የኳስ መጫወቻ ሜዳና ቅድመ 1983 ለበዓላት ወቅት የበዓል ማብሰርያ መድፍ መተኮሻ ቦታ ነበር) እንዲሆን ተደረገ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት በደርግ የአስተዳደር ወቅት የተገኙ ለውጦች ነበሩ፡፡ ለኢትዮጵያ ሙስሊም መነቃቃት በር የከፈተው የደርግ መንግሥት መሆኑን በአሁኑ ዘመን በሙስሊሙ ታሪክ ላይ አጠንጥነው የሚወጡ መጽሐፍት ያስነብቡናል፡፡

ወደ ሙፍቲሕ ሐጂ ዑመር በየዘመኑ የተገኙ ለውጦችን ትንተና ስናመራ በኢህአዴግ ዘመን ተገኘ ከሚሏቸው ለውጦች አንዱ የሙስሊሙ በሸሪዓ ፍርድ ቤት መዳኘትን ነው፡፡ በእርግጥ ሐጂ ዑመር በዝርዝር ለመግለጽ አጋጣሚው




አላመቻቸው ይሆናል እንጂ የኢትዮጵያ ሙስሊም ባለፉት 28 ዓመታት ከፍተኛ መብቶቹ እንደተከበሩለት እሙን ነው፡፡ (ከሚሊኒየሙ ወዲህ በሥውር የመንግሥት ፖሊሲ የተደፈጠጡም እንዳሉ ሆነው፡፡) በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ መረዳት ‹‹በደርግ ዘመን የሁለቱ ኢድ ሶላቶች (ኢድ አልፈጥር እና ኢድ አልአድሐ) ይሰገዱ የነበሩት በዋና ዋና መስጅዶች ነበር፡፡ በተለይም በአንዋርና ኑር (በኒን አካባቢ /በኒን ማለት አንድ አይሁድ ይኖርበት የነበረ ሰፈር በመሆኑ ነው በሱ ስም አካባቢው የሚጠራው/) መስጅዶች፡፡

በኢህአዴግ የአስተዳደር ዘመን ግን በተለይም ከ1980ዎቹ አጋማሽ ወዲህ የኢድ በዓላት የአዲስ አበባ ሙስሊም በእስታዲየም ዙርያ፣ የየክልሉ ሙስሊሞች ደግሞ በየአካባቢያቸው ሰፊ አደባባዮች እንዲከበሩ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የጁመዓ ሰላት ታሳቢ ተደርጎ በየሳምንቱ አርብ የሥራ ሰዓት ከቀኑ አምስት ከሰላሳ አብቅቶ ሰባት ሰዓት ከሰላሳ የከሰዓት የሥራ መግቢያ ሰዓት እንዲሆንም ተወስኗል፡፡ የፌዴራል መንግሥቱ ለሁሉም አካባቢዎች እራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ መፍቀዱ ሙስሊሞች በብዛት የሚኖሩባቸው ክልሎች ከእስልምና አስተምህሮ ጋር የተሳሰረ ባሕላቸው እንዲያድግ እድል ሰጥቷል፡፡ ይህ ሙስሊሞችን ታሳቢ ያደረገ እድገት ሳይሆን ለክልሎች የተፈጠረ አጋጣሚ ነው፡፡

ሐጂ ዑመር ከ2010 ወዲህ ማለትም ዶ/ር አብይ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ የተገኙ ሁለት ለውጦችንም አውስተዋል፡፡ ወለድ አልባ ባንክ መፈቀዱ እና ይኸው ጥር 9 የሚኒስትሮች ም/ቤት ‹‹የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች›› ከመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፈቃዱ ተሸጋግሮ ወደ ሕጋዊ ሰውነት ያለው የሙስሊሞች ተቋምነት መሻጋገሩ በ1966 ከተጠየቁ አንኳር ጥያቄዎች ዋናው ከ44 ዓመታት በኋላ የተመለሰ ብለውታል፡፡

ለመሆኑ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ሕጋዊ ሰውነት ሲባል እንዴት የሚታሰብ ነው?

በታሕሳስ 14 ቀን 1967 በብሔራዊ ደረጃ ስለሚከበሩ በዓላት ዝርዝር መግለጫ ወጣ፡፡ የሙስሊሙ ትግል ፍሬ ማፍራቱን ያሳየ የመጀመርያ ማሳያ የነበረው ኢስላማዊ በዓላት በመግለጫው መካተታቸው ሲታይ ነው፡፡ በአዋጁ እውቅና የተሰጣቸው 12 የሕዝብ በዓላት መካከል ሦስቱ ከላይ የጠቀስኳቸው የሙስሊም በዓላት ነበሩ፡፡ ለመጀመርያ ጊዜ ታሕሳስ 15 ቀን 1967 በብሔራዊ ደረጃ ዐረፋ /ዒድ አልአድሃ/ ተከበረ በወቅቱ አዲስ ዘመን ጋዜጣ የመጀመሪያ ዜና አድርጎ (leading news) እንዲህ አስፍሮት ነበር፡፡

‹‹አዲስ አበባ ፤ (ኢ.ዜ.አ) በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የእስላም ሃይማኖት መሪዎችና ታላላቅ ሽማግሌዎች ፤ትናንት ከእኩለ ቀን በፊት በ 5 ሰዓት ላይ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ሔደው ኢድ አል አድሐ ወይም የአረፋ በዓል በብሔራዊ ደረጃ እንዲከበር በመደረጉ ምክንያት የተሰማቸውን ጥልቅ የደስታ ስሜት ገልጠዋል፡፡ …›› (አዲስ ዘመን ረቡዕ ታሕሳስ 16 ቀን 1967 ዓመተ ምሕረት)

በዕለቱም ሥራ ተዘጋ፣ ሙስሊሞች የፍርድ ቤትም ሆነ የት/ቤት ጭንቀት ሳይረብሻቸው በዓላቸውን አከበሩ፣ ዘመድ ከዘመዱ ሳይሸማቀቅ ተገናኘ፣ ከሀገር ሀገር ሄዶ ተጠያየቀ፣ የመጀመርያዋ ‹‹ዐረፋ መጽሔትም›› በወቅቱ ወጣቶች ከበዓሉ ቀደም ባሉ ቀናት ተዘጋጅታ ለበዓሉ ተሰራጨች፡፡ ሙስሊሙ በሀገሩ የመኩራት መብቱን ያስከበረለትን ለውጥ አመሰገነ፡፡ በትንሽ ነገር የሚደሰት ቢሆንም ይህ ድል ግን ከብዙ ጥረት በኋላ ያገኘው በመሆኑ እንደ ቀላል የሚመለከተው አልነበረም፡፡

ሙስሊሙን ለማሸማቀቅ እንደቆመ ይታመን የነበረው ሕዝባዊ ኑሮ እድገት መ/ቤት ለሰፊው የኢትዮጵያ ሠራተኞች በሚያገለግል ደረጃ የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚል ተቋቋመ (በዚህ ጉዳይ ላይ በሌላ አጋጣሚ በሠፊው እመለሳለሁ)

እነዚህ ሁሉ እንዳሉ ሆነው የኢትጵያ ሙስሊም ያጣቸው ነገሮች ብዙ እንደሆኑ የታመነ ነበር፡፡ በተለይም የመስገጃ ቦታዎችና የመቃብር ቦታዎችን በተመለከተ ሁሌም ለከፍተኛ መንገላታት ተዳርጎ ለምኖ፣ ተማጽኖ፣ በአስቸጋሪ ቢሮክራሲ ውስጥ አልፎ፣ ተንከራቶ ኩርማን መሬት አግኝቶ በስዋው መስጅድ መገንባት ሲጀምር ተቃዋሚዎች ለሌላ ዙር መንገላታት ሲዳርጉት ኖረዋል፡፡ በአዲስ አበባ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ የተሰሩ መስጅዶች ከቀድሞዎቹ አንጻር በርካታ ቢሆኑም አብዛኞች የተጨናነቁ ከአንድ ሺህ ካሬ ሜትር በታች ያነሱ ሰጋጆችን በበቂ የማያስተናግዱ፣ በግለሰብ ስጦታዎች መሬት ላይ የተሰሩ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመለሱ የሙስሊሙ ጥያቄዎች አሁንም በርካታ ናቸው፡፡ ከሁሉም የሚልቀው ግን የመጅሊሱ ሕጋዊ ሰውነት የማግኘት መብት ነበር፡፡

ከሰሞኑ በሚኒስትሮች ም/ቤት ታምኖበት ወደ ተወካዮች ም/ቤት የተላከው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ሕጋዊ ሰውነት ብዙ መስዋትነት እና የረጅም ዓመታት ጥያቄ የነበረ ነው፡፡ በየጊዜው ሥልጣን ላ ለተቀመጡ የመንግሥት ሹሞች ጥያቄው ቢቀርብም በተለያዩ ምክንያቶች ሲገፋ ኖሯል፡፡ በ2004 ተፈጥሮ የነበረው ዓመታትን የፈጀውና በ2010 ፍጻሜውን ያገኘው የሙስሊሞች ንቅናቄም አንዱ ጥያቄ የመጅሊስ ሕጋዊ ሰውነት ነበር፡፡ በወቅቱ እንደምናስታውሰው ሶስቱ ጥያቄዎች እየተባሉ ከሚጠቀሱት አንዱ ይኸው ጥያቄ በሰኔ 2010 በዶ/ር አብይ ካቢኔ በተመረጡ ዘጠኝ የሙስሊሙ ተቋማዊ ለውጥ አስተባባሪ ኮሚቴዎች አማካይነት ተጠንቶ ለመንግሥት ቀርቦ የነበረ ጥያቄ ነበር፡፡ መጅሊሱን በአዲስ የማወቀሩ ሂደት እንደተበቀ ሆኖ ሕጋዊ ሰውነት እስኪያገኝ ጊዜያዊ ኮሚቴ እነ ሐጂ ዑመርን ያቀፈ መቋቋሙም የሚታወስ ነው፡፡

በቀሪ ጉዳዮች ላይ ከተወካዮች ም/ቤት ምላሽ በኋላ በቀጣይነት የምመለስበት ይሆናል እስከዚያው ቸር እንሰንብት፡፡

# “ወደ መሰረቴ የመመለሴ የኢትዮጵያዊነትን ጥልቅ ምሥጢር መረዳቴ ነው”

አቨቫ ደሴ



በ1970ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ነው፡፡ ወላጆችዋ ከሚኖሩበት የጎንደር ክፍለሃገር ወደ ሱዳን በማምራት በሱዳን በሚገኙ የስደተኛ ካምፖች ውስጥ እየኖሩ ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ እስራኤል የሚወስዱዋቸውን ምሥጢራዊ ተልዕኮ ፈፃሚዎች እስኪያገኙ እንዲጠብቁ ተነግሯቸው ቤቴን ንብረቴን ሳይሉ በተስፋ ብቻ ወደ ሱዳን የተሰደዱ ነበሩ፡፡

በዚያ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ታዲያ ያለበቂ ስንቅ፣ ውሃና መድኃኒት ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትሮችን በእግር በመጓዝ ሱዳን ከገቡት ብዙ ሺህ የቤተ እስራኤላውያን ቤተሰቦች መካከል አሁን በዓለምአቀፍ ደረጃ በሙዚቃ ሥራዎችዋ ተቀባይነት እያገኘች የመጣችው የአቨቫ ደሴ ቤተሰቦች አንዱ ናቸው፡፡

በቅርቡ በታዋቂ አሜሪካውያን የፊልም አክተሮች የተወነበት “ዘ ሪድ ሲ ዳይቪንግ ሪዞርት” ፊልም ላይ በእስራኤል የስለላ ድርጅት የሞሳድ አባላት አማካይነት በሱዳን የተለያዩ የስደተኛ ካምፖች የነበሩ ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን በባህርና በአየር በምሥጢር ወደ ሱዳን የማጓጓዙ ሂደት በአንዱ ተጠቃሚ በመሆን ወደ እስራኤል ገብተው በናዝሬት ከተማ መኖር የጀመሩ ወላጆችዋ የእስራኤልን ሕይወት ከተለማመዱ በኋላ ነው ልጃቸው የተወለደችው፡፡

ከሰሜን ኢትዮጵያ የተለያዩ የገጠር አከባቢዎች ይኖሩ የነበሩ ወደ እስራኤል በሞሳድና በሌሎች ተቋማት አማካይነት የተጓጓዙት ኢትዮጵያዊያን አይሁዶች በመጀመሪያ በ“ኦፕሬሽን ሙሴ” በተባለው ተልዕኮ ወደ እስራኤል ከተጓጓዙ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በ1983 በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ “ኦፕሬሽን ሰለሞን” በተባለ ተልዕኮ 14,386 ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ወደ እስራኤል ከተጓጓዙበት ተልዕኮ በኋላ አብዛኛው ትውልደ ኢትዮጵያውያን በእስራኤላውያን በተለያዩ መልኮች የሚፈፀምባቸውን የዘር መድሎ ጥቃቶች ሳቢያ ለከፋ የማንነት ቀውስ ተዳርገው ነበር፡፡

አቨቫ ደሴ ከአራት እህቶችና ወንድሞችዋ ጋር በናዝሬት በርካታ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች በሚኖሩበት አካባቢ ነበር ተወልዳ ያደገችው ኮል ኢስራኤል ሬዲዮ ስለ አቨቫ ደሴ እንፈራንዝ ጎንደር የተወለዱ ወላጆችዋ ወደ እስራኤል ለመምጣት ስለከፈሉት መስዋዕትነት አንድም ቀን አውግተዋት አያውቁም፡፡ ስለዚህም አቨቫ ተወልዳ ያደገችበትን ሕብረ ብሔራዊ የአይሁድ ማኅበረሰብ ውስጥ እንደ አንድ እስራኤላዊ ነበር ያደኩት ነገር ግን ባደኩኝ ቁጥር እኔ የተሰራሁበት ሶሻል ሜካፕ በነጭ የበላይነት ካፀደቀ ማኅበረሰብ ጋራ ልስማማ አልቻልኩም፡፡

በትምህርት ቤት ሕይወቴ ብዙ መገለሎችና መድሎዎችን ባስተናግድም ስለተገኘሁበት የዘር መሠረት ማሰብ የጀመርኩት የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ግዳጄን ለመወጣት ማሰልጠኛ የገባሁ ጊዜ ከሶቪየት ሕብረት ሪፐብሊኮች ወደ እስራኤል የገቡ ሩስያውያን፣ ዩክሬኖች የመጡበትን ሀገር ማኅበረሰብ ባህልና ቋንቋን ይዘው ሲዘፍኑ ድራማ ሲሰሩ ሳይ “እኔ ማነኝ? ወዴት ነኝ?” ብዬ ማሰብ መጠየቅ ጀመርኩ፡፡

ከዚያ በኋላ ነው ከልጅነቴ ጀምሮ አዳምጣቸው የነበሩትን የሬጌ የካንትሪ ሙዚቃ ስልቶች የተሠሩ ዘፈኖችን ማቀንቀን ትቼ በአማርኛ መዝፈን የጀመርኩት፤ እናም ወላጆቼና ዘመዶቼ ስለትውልድ ሀገራቸው ስለእድገታቸው አኗኗራቸው እንዲነግሩኝ መወትወት ጀመርኩ፡፡

በሚገርም ሁኔታ የበለፀገ ቱባ ባህል እሴቶች ያሉት ሕዝብ ውስጥ የተገኘሁ መሆኔን ካረጋገጥኩ በኋላ በማኅበረሰባችን ውስጥ ያለውን እሴት ማጥናት መረጥኩ፡፡ በተለይ ብሔራዊ ውትድርና እየሰለጠንኩ እያለ በደረሰብኝ የመኪና አደጋ ተኝቼ እያለሁ የአስቴር አወቀ፣ የቴዎድሮስ ታደሰ፣ የኤፍሬም ታምሩ የመሐሙድ አህመድ የጥላሁን ገሠሠ የአለማየሁ እሸቴን ዘፈኖች ለሁለት ዓመታት ያለማቋረጥ ሳዳምጥ ሳጠና ካለሁበት ማኅበረሰብ ባህል ጋር በመለማመድ ግጥምና ዜማ በማዘጋጀት ከእድሜ እኩዮቼ ጋራ አንድ የሙዚቃ ቡድን አቋቋምኩ፡፡

ሀያ ዓመት ቢፈጅም ልክ እኔ ራሳቸውን ማለት ማንነታቸውን ፈልገው ያገኙ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች እንደ አስቴር ረዳ፣ ጊሎ ዋጎ፣ ሌሎች ዘፋኞች የኢትዮጵያን ሙዚቃ ከሂብሩ ሙዚቃ ጋራ በማዋሃድ መዝፈን ጀመሩ፡፡ ይህንንም ፈር ቀዳጅ ተግባርን ተከትዬ እኔም ሥራዎቼን ለሙዚቃ አፍቃሪዎች ለማቅረብ መለማመድ እና ከጓደኞቼ ጋራ “ዘቮይስ” የተሰኘ የሙዚቃ ባንድን አቋቁመን መስራት ጀመርን ትላለች ታዋቂዋ አቀንቃኝ አቨቫ ደሴ፡፡

በመቀጠል ያደረኩት ነገር ቢኖር በቀጥታ ወደ ወላጆቼ የትውልድ ሀገር ኢትዮጵያ ከባልንጀሮቼ ጋር ተጓዝኩ፡፡ ይህ ጉዞዬ ነው ለእኔ ወደ መሰረቴ መመለሴን ያረጋገጠልኝና የኢትዮጵያዊነትን ምሥጢር የማወቂ መጀመርያ ነበር፡፡ “I Want go” የተሰኘውን ዘፈኔን የፃፍኩት ገጣሚ አቀንቃኝ ደራሲ ስትሆን በውስጥ የሚንቀለቀለውን የስሜትና የሐሳብ ሞገድ አውጥተህ ለተደራሲው ማድረስን የመሰለ የእርካታ ጥግ የለም ፤ እኔም ያንን እርካታ አገኘሁ፡፡

“ብዙዎች በእስራኤል ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች በሕይወታቸው ደስተኛ ለመሆን በተሰማሩበት መስክ ስኬታማ ለመሆን የያዛቸው የማንነት ቀውስ (identity crises) ለማሸነፍ ወደሥር መሠረታቸው መመለስ እንዳለባቸው አምናለሁ” ትላለች አቨቫ ደሴ፡፡

በኦፕሬሽን ሙሴ በኦፕሬሽን ሰለሞን፣ በኦፕሬሽን ዳዊት፣ ኦፕሬሽን “ብራዘር” ወደ 50 ሺኅ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ወደ እስራኤል ተጉዘው በዚያ ኑሮ መስርተዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ አሁን በመቶ ሺዎች በላይ የሆነ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን አይሁዶች መንግሥትና ሕዝብ ተገቢውን ቦታ አልሰጠንም በሀገሪቱ እንደዜጋ የሙሉ መብት ተጠቃሚ አይደለንም በሚል በየጊዜው ለተቃውሞ አደባባይ ይወጣሉ፡፡ ከፖሊስ ጋራ ይጋጫሉ ሆኖም እስካሁን ግን ጥያቄያቸው ያለመመለሱን ይናገራሉ፡፡

ስለዚህም አስተያየትዋን የሠጠችው አቨቫ ደሴ “ልክ ነው እኔ ነፍስ ካወቁኝ ጀምሮ ተቃውሞዎች ሲደመጡ ትዕይንቶች ሲካሄዱ እያየሁ ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን እውነታ ለመቀየር በየተሰማራንበት መስክ መታገል አለብን፡፡ ስለዚህም ነው እኔ ራሴን እንደ ሙዚቀኛ ብቻ ሳይሆን እንደ ማኅበረሰብ ለውጥ ተዋናይ የማየው፡፡ ሙዚቃ ሊጫወተው የሚችለው ሚና በመጫወት ማኅበረሰቡ ለመብቱ፣ ለእኩልነቱና ለጥቅሙ መረጋገጥ እንዲንቀሳቀስ የበኩላችንን ሚና ልንጫወት ይገባል፡፡ የራሳችንን ጀግኖች መፈለግ ማወደስ ለዓለምም ማስተዋወቅ አለብን፡፡

እኔና የእኔ ትውልድ እንደወላጆቼ ብዙ ወጣውረድ ቢኖርብንም ከእስራኤል ውጭ ሌላ ቦታ መኖር አልፈልግም አንልም፡፡ ወደ እስራኤል ያደረሰንን አዳጋቹ ጎዳና ስቃይና መከራውን ሊነግሩን ይገባል፡፡ መሠረታቸውን ጭምር ያን ጊዜ ዛሬ ባይሆን ነገ ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን የተሻለች እስራኤል ውስጥ ይኖሩ ዘንድ አያቶቻችሁ እንዲህ ነበሩ ወደዚህም ሀገር መጡ፡፡ እኛንም ወለዱ እናም ዛሬ እናንተ ለምትኖሩባት የተሻለች ዓለም እኛ ያበቃናችሁ ይህንን መስዋዕትነት ከፍለን ነው ልንላቸው ይገባል ብዬ አምናለሁ” ብላለች፡፡

የ31 ዓመቷ ትውልደ ኢትዮጵያዊት እስራኤላዊት አቀንቃኝ አቨቫ ደሴ ሦስት የሙዚቃ አልበሞችን ሠርታለች፡፡ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሚካሄዱ የሙዚቃ ፌስቲቫሎች ላይ በመገኘት ሥራዎችዋን ለሙዚቃ አፍቃሪዎቹ ታቀርባለች፤ በተደጋጋሚ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣትም በርካታ የሙዚቃ ቪዲዮ ክሊፖችዋን ሰርታለች፡፡

ዛሬ በመላው ዓለም ተወዳጅነትና ተቀባይነት ያገኘው የአፍሪካ አሜሪካውያን የሙዚቃ አቀንቃኞች ስኬት ሥራዎች ሁሉ አንድ ቀን ደግሞ የኢትዮ እስራኤላውያን የሙዚቃ ሰዎች ሥራዎች ዓለምአቀፍ ታዋቂነት እንደሚያገኝ ተስፋ በማድረግ ድምፃዊት አቨቫ ደሴ ለኮል እስራኤል ሬድዮ ስትናገር “ዘረኝነት በመፀየፍ ፍቅርን አንድነትን የሚያጎሉ ሥራዎችን መስራትን ቀጥላለሁ ለእኔ አሁን ሙዚቃ ሕይወቴ ነው፡፡ በእረፍት ጊዜዬ የተለያዩ ዘመናት ኢትዮጵያውያን አዝማሪዎች ያቀነቀኑዋቸውን ዜማዎች የበገና፣ ዘለሰኛ ቀረርቶ እና ፉከራዎችን ሳይቀር እየሰማሁ ወደኋላ ተመልሼ ከወላጆቼ መሠረት ጋር ያለኝን ቁርኝት አጠብቃለሁ” ትላለች፡፡

# “ሀብታም ሀገር ይዘን መጠቀም እየቻልን እርስበርስ መፋጀታችን ያሳዝናል ! ”

ዘላለም መርዓዊ



አምቦ ተወልዶ አዲስ አበባ ያደገው የቱሪዝም ዘርፍ “አንቀሳቃሽ ሞተሩ” ዘላለም መርዓዊ ገና ከአፍላነት ዕድሜያቸው ጀምረው የኢትዮጵያን ምልክ ለአለም በማሳየት ራሳቸውንና ወገናቸውን ለተሻለ ደረጃ ካበቁ ጥቂት የሀገር ባለውለታዎች አንዱ ነው፡፡

ስራ ሰርቶ ማደር ከሚቻልበት የጉርምስና ዘመኑ ጀምሮ በብዙ ውጣ ውረዶችና ተስፋ አስቆራጭ የህይወት አጋጣሚዎች ውስጥ እያለፈ፣ በፅናት በመራመዱ ለታላቅ ስኬት የበቃው ዘለዓለም መርዓዊ ከዜሮ ሳንቲም ተነስቶ ዛሬ እስከደረሰበት የሚሊዮኖች ካፒታል የተራመደው “ትልቅ የመሆንን ራዕይ ሰንቆ” መሠናክሎቹን ታግሎ በማሸነፉ እንደሆነ የሚያውቁት ሁሉ ይመሠክሩለታል፡፡ መድረስ የሚፈልግበት እርከን ላይ ለመድረስ መሆን ያለበትን ሁሉ እየሆነ ማለፉንም በተምሳሌትነት ይጠቅሱታል፡፡

ራስ ሆቴል ግቢ የሚገኘው የዘላለም አስጎብኚና መኪና ኪራይ ድርጅት ባለቤት የሆነው “ወጣቱ የስኬት ተምሳሌት” ስለሀገሩ ያለው ፍቅርና የሀገሩን መልክ በአለም ዙሪያ ለማስተዋወቅ የሄደበት ርቀት ራሱን ችሎ ብዙ ትረካዎች ሊወጡት የሚችል የገድል ታሪኩ ቢሆንም እርሱ ግን ስራ ላይ እንጂ ራሱን መንገር ላይ ሲሽቀዳደም አይገኝም፡፡ ትንሽ ሠርተው ብዙ እንዲወራላቸው የሚፈልጉ የዝና ጥመኞች በበዙበትና ካልዋሉበት ሜዳ ገድል ጋር ስማቸው በአቋራጭ እንዲነሳ የሚፈልጉ የእውቅና ረሀብተኞች በተበራከቱበት በዚህ ዘመን እንደዘላለም ያሉት የሀገር ብርቅዬ ልጆች ግን ዛሬም ስራ ላይ ናቸው፡፡ ሀገርንና ወገንን በኢኮኖሚም በስነልቦናም የተሻለ ሆነው እንዲገኙ የሚያደርግ ተልዕኮ አንግበው የነገዋን ታላቅ ሀገር በመስራት ላይ እንደተጠመዱ ናቸው፡፡

የዘላለም ሀገራዊ ውለታ ብዙ ነው፡፡ ለሚወዳት ኢትዮጵያና ለሚያከብረው ወገኑ ክብር ሲል በእርሱ አቅም ብቻ ሊከወን የማይቻልን አንፀባራቂ ተግባር ከብርቱ ድካም በኋላ እውን አድርጓል፡፡ አሁንም ለቱሪዝም ዘርፍ ዕድገትና ሀገራዊ ተጠቃሚነት ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ በእጅጉ እየደከመ ይገኛል፡፡

ከየት ተነስቶ የት ደረሰ፣ ምንስ እየሰራ ነው? የሚለውንና ሌሎችንም ጉዳዮች የግዮኑ አለማየሁ ባዘዘው ከዘላለም ጋር ባደረገው ቆይታ ያስቃኛችኋል፡፡

**ግዮን፡- ስለአገርህ ያለህን ጥልቅ ፍቅር አውቃለሁና እስቲ “ይህችን ታላቅና እጅግ የተከበረች አገራችን ኢትዮጵያን” በአጭር ዐረፍተ ነገር ግለፃት ብትባል እንዴት ነው የምትገልፃት?**

ዘላለም፡- የ3 ሺህ ዘመን የሥልጣኔ ታሪክ ያላት የእነአክሱም የእነላሊበላ የእነጢያ፣ የእነ ጫሞ የእነ ጣና፣ የእነ ሶፍዑመር፣ የእነ ጀጎል፣ የአፄ ፋሲለደስ፣ የእነ ጫምበላላ፣ የእነ አሸንድዬ፣ የእምዬ ምኒልክ፣ የእነ ቴዎድሮስ፣ የእነ ዮሃንስ፣ የእነ ጦና፣ የእነ አባጅፋር፣ የእነ ፉራ… አገር የሆነችውን ይህችን ብርቅና ድንቅ የተከበረች አገር፣ ኢትዮጵያን እንኳን በአጭር ዐረፍተ ነገር ሺህ ገፆች ባሉት መጽሐፍ እንኳን ለመግለፅ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ የብሔር ብሔረሰቦቿን፣ የተፈጥሮ ሀብቷን፣ የሥልጣኔ ታሪኳን፣ የዕምነት መቻቻል ትንግርቷን፣ የጀግንነት ታሪኳን ይህንን ሁሉ ወግና ልማድ እንዴት አድርጌ በአጭር ዐረፍተ ነገር ልገልፀው ይቻለኛል?… ከባድ ነው፡፡

**ግዮን፡- ከባድ ነው አልክ እንጂ ከበቂ በላይ በሆነ መልኩ ጥያቄዬን መልሰኸዋል፡፡**

ዘለዓለም፡- መስሎህ እንጂ የ3 ሺህ ዘመን ተነግሮ የማያልቅ ተፈጥሮአዊና አለምን በአግራሞት አፍ የሚያስከፍት የሥልጣኔ ታሪክ ያላትን አገር በአጭሩ መግለፅ አይቻልም፡፡

**ግዮን፡- የስራ ጅማሮ ዘመንህን ወደ ኋላ ሄደህ አስታውሰንና ወደዚህ ስራ እንዴት እንደገባህ ብታጫውተን?**

ዘላለም፡- ዘላለም ቱር ኤንድ ትራቭል ኤጀንት ከ13 ዓመታት በፊት “ዘላለም የመኪና ኪራይ” በሚል ነው ስራ የጀመረው፡፡ የጀመርነው በአንድ ቱ ኤች በሚባል የድሮ መኪና ነው፡፡ ይሄ መኪና ፈቃድ አውጥተን ቢሮ ከፍተን ስራ ከጀመርን በኋላ የተገዛ እንጂ ድርጅቱ ሲቋቋም የነበረ አይደለም፡፡ በዚህ መኪና ነው እንግዲህ ሠርተን እዚህ ደረጃ የደረስነው፡፡ ጠንካራ ልብና ባዶ ኪስ ይዘን ነበር የተነሣነው፡፡

**ግዮን፡- ስራውን ስትጀምረው የአዋጪነት ጥናት አድርገህ ነው ወይስ ልሞክረው በሚል…?**

ዘላለም፡- ስራው ሲጀመር ከፍተኛ የገበያ ዕድል ማለትም ሰፊ ሊያሰራ የሚችል አዋጭ ሁኔታ እንደነበር አውቀን ነበር፡፡ በወቅቱ ህጋዊ ሆነው የመኪና ኪራይ ስራን በዘመናዊ መልክ ይሰሩ የነበሩት ቢበዛ ከ5 የማይበልጡ ነበሩ፡፡ በአሁን ሰዓት ግን በማስጎብኘትና የመኪና ኪራይ ሥራ ላይ ከ1 ሺህ ያላነሱ ድርጅቶች ናቸው ያሉት፡፡ ይሄ የሚያሣየው የዘርፉን ዕድገትና አዋጪነት ነው፡፡ ስለዚህ እኛ በዚህ ዘርፍ ከቀዳሚዎቹ ጋር ስማችን ሊነሳ የሚችል በመሆኑ ስራውን ስንጀምረው ምንም ዓይነት የገበያ ችግር እንደማይገጥመን እርግጠኞች ነበርን፡፡

**ግዮን፡- አሁን ያለው ዘላለም አስጎብኚና መኪና ኪራይ ድርጅት ከማስጎብኘትና መኪና ማከራየት በዘለለ ምናልባትም ገቢ የማያስገኙ ነገር ግን ለሀገር ትልቅ ፋይዳ ያላቸው ሌሎች ስራዎችንም እንደሚሠራ አውቃለሁ፡፡ ለዚህም ኬር ኤኸ ኢትዮጵያ የተባለውን የቱሪስት ጋይድ ማጋዚን እንደምሣሌ መጥቀስ እንችላለን፡፡ ድርጅታችሁ እንዲህ ያሉ ትርፍ የማያስገኙ ስራዎችን የሚሠራበት ዋነኛ ምክንያት ምንድነው?**

ዘላለም፡- ሁሌም ደጋግሜ እንደምገልፀው ሰዎች በአንድ ስራ ላይ የሚሠማሩት ከዚያ ስራ ተጠቃሚ ለመሆን ነው፡፡ ቢሆንም ግን በምትጠቀምበት ስራህ ዙሪያ ያለውን ማኅበረሰብ መጥቀምን መርሣት የለብህም፡፡ ሀገርህ ሠርተህ እንድታገኝ ምቹ ሁኔታን ስትፈጥርልህ አንተ ደግሞ መልሰህ እሷን የምትጠቅምበትን ሁኔታ መፍጠር አለብህ፡፡ እንስሳ ብቻ ነው ያደገውን ሣር በልቶ የሚተኛው፡፡ ሳር ሲጠፋ በባዶ መተኛት የእንስሳ ባህሪ ነው፡፡ እኛ ከእንስሳ የምንለይ ሰዎች ስለሆንን ከዛሬ ባለፈ ስለነገ ማሰብ ያስፈልገናል፡፡ ከዚህ በመነሣት ለሀገሬም ምን ማበርከት አለብኝ?… አንቱ የሚያስብል ምን ስራ ሰርቼ ማለፍ ይገባኛል?… ነገ ጠዋት ልጆችህ አባታችን ምን ሠርቶ አለፈ የሚል ጥያቄ ሲያነሱ በቂ መልስ እንዲኖራቸው ማድረግን አስበህ መስራት ይኖርብሃል፡፡ አለዚያ ልጆችህም በአንተ አምሣል ለአገር የማያስቡ ሆነው ነው የሚቀሩት፡፡ ስለዚህ የነገ አገር ተረካቢ የሆኑ ልጆችህ በአንተ መንገድ ተጉዘው ለአገራቸው የሚቆረቆሩ እንዲሆኑ ለማድረግ በቻልከው መጠን አንድ አሻራ ጥለህ ማለፍ ይኖርብሃል፡፡

እንግዲህ ከዚህ የተነሳ ነው “ኬር ኤኸ ኢትዮጵያ የተባለ ቱሪስት ጋይድ መጋዚን”ን እና ፖርታል ዌብሳይትና አፕሊኬሽን መጋዚን ለማዘጋጀት የተነሣሁት፡፡ ከተማችን ውስጥ የሚገኙ ቆሻሻ መጣያ የነበሩ ሶስት የሚሆኑ ቦታዎችንም አረንጓዴ ገፅታ የተላበሱ ንፁህና ▶



ማራኪ መስህብ ያላቸው እንዲሆኑ ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ወጪ በማድረግ አስውበናል፡፡ እኚህ ቀድሞ ጠያፍ ገጽታ የነበራቸው ቦታዎች ዛሬ የኢትዮጵያን የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ምሳሌ ባደረጉ ቅርፃ ቅርፆች ተውበው የከተማችን መልካም ገፅታ ማሳያ ሊሆኑ ችለዋል፡፡

**ግዮን፡- "ኬር ኤኸ የቱሪስት ጋይድ ማጋዚን" በዓለም አቀፍ ደረጃ ስላስገኘልህ እውቅና እና ሽልማት ንገረን?**

ዘላለም፡- ይሄ የኬር ኤኸ ኢትዮጵያ መጽሐፍ በተለያየ መልክ ሶስት ጊዜ ወጥቷል፡፡ የእውነት ለመናገር ዕትሞቹ ኢትዮጵያ ብቻ ሣይሆን ዓለምን ያነጋገሩ ነበሩ፡፡ በነዚህ የቱሪስት ጋይድ መጽሐፎች እውቅና እና ትልልቅ የሚባሉትን ሽልማቶች ያገኘሁት ኢትዮጵያ ውስጥ አይደለም፡፡ የመጀመሪያውን ሽልማት ያገኘሁት ትልቋ የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ከሆነችው ጄኔቫ/ስዊዘርላንድ ነው፡፡ ጄኔቫ ድረስ በክብር ተጋብዤ ሄጄ አለም አቀፍ ሽልማት ስሸለም የሠራሁት ስራ ምን ያህል ፋይዳ ያለውና ለዓለም ሁሉ ተደራሽ እንደሆነ ለማየት ችያለሁ፡፡ ሁለተኛው ሽልማት ደግሞ በሰሜን አሜሪካ ሂዩስተን ግዛት የተሸለምኩት ነው፡፡ ይህንንም እዚያው ድረስ በክብር ተጋብዤ ሄጄ ነው የተቀበልኩት፡፡ ሽልማቶቹ ኢትዮጵያን ለዓለም ከማስተዋወቅ በተጓዳኝ ለማኅበረሰብ መስራትን መስፈርት ያደረጉ ናቸው፡፡ በመጽሐፎቹ ውስጥ ከ2 ሺህ በላይ የሚሆኑ በቱሪዝም ዘርፍ ውስጥ ብቻ የተሠማሩ ድርጅቶችን የስልክ እና የኢ-ሜል አድራሻ በነፃ በማውጣታችን ይህም የቱሪዝም ዓለም አቀፍ ትስስርን የሚፈጥር መሆኑ ለሸላሚዎቹ ትርጉም ያለው ሥራ ሆኖላቸዋል፡፡ ኢትዮጵያን ከተቀረው ዓለም ጋር በቢዝነስ የሚያስተሳስርና ሠፊ የስራ ዕድልን የሚፈጥር መሆኑንም አምነውበታል፡፡ መጽሐፉ የኢትዮጵያን የቱሪስት መዳረሻዎች በዝርዝር የሚቃኙና ቱሪስቱን ወዲህ እንዲመጣ የሚያደርጉ ጥንቅሮችንም የያዘ ስለሆነና በዚህም ከአየር መንገዳችን ጀምሮ ሆቴሎቻችን፣ አስጎብኚ ድርጅቶቻችን፣ መኪና አከራዮች፣ ቱር ጋይዶች፣ የቅርፃ ቅርፅ መሸጫ መደብሮችና ሌሎችም በዚህ ዙሪያ ያሉ ተቋማት ሰፊ የገበያ ዕድል የሚፈጠርላቸው በመሆኑ ሸላሚዎቹ ድርጅቶች በእነዚህና በሌሎችም በርካታ ዝርዝር መስፈርቶች ሥራችንን መዝነው ሊሸልሙን በቅተዋል፡፡

**ግዮን፡- የህትመት ጥራቱ እንደ አንድ መመዘኛ የታየ ነበር?**

ዘላለም፡- እውነት ለመናገር ስራውን ለመስራት መጀመሪያ ስንነሣ ሽልማት የሚሰጥ ድርጅት መኖሩን አናውቅም ነበር፡፡ ነገር ግን ከሠራን ላይቀር ህትመቱም ከፍተኛ ጥራት ሊኖረው ይገባል የሚል አቋም ነበረን፡፡ በህትመት ዘርፍ ዓለም አሁን የደረሰበት የቴክኖሎጂ ጥራት ደረጃ ሊኖረው ይገባል በሚል ዌብሳይት እና አፕሊኬሽን ሜጋዚን ጭምር እንዲኖረው አስበንበት ነበር የሠራነው፡፡ እንደምታውቀው በህትመት ቴክኖሎጂ አንፃር አገራችን ገና ብዙ የሚቀራት በመሆኑ መፅሐፉን ከአገር ውጪ ነው ያሣተምነው፡፡ ፅሁፎቹ ልምድ ባላቸው ኤዲተሮች በቂ ጊዜ ተወስዶ የታሸ እና የተቀናበረ ከመሆኑ ባሻገር ፎቶዎቹም በራሳችን ካሜራ ባለሙያዎች የተነሱ ኦሪጅናል ፎቶዎች እንዲሆኑ አድርገን እጅግ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ህትመቶች ሆነው እንዲወጡ ብዙ ደክመንበታል፡፡ ያው ድካማችን ዋጋ ቢስ አልሆነም፡፡ በተለይ የጄኔቫው ሸላሚያችን ሴንቸሪ ኢንተርናሽናል ኳሊቲ ኤራ አዋርድ "የክፍለ ዘመኑ ምርጥ" ብሎ ነው የሸለመን፡፡ አዋርዱ ላይ የተፃፈውም ይህንኑ ነው የሚገልፀው፡፡

**ግዮን፡- ኬር ኤኸ በተከታታይ ሶስት ጊዜ ወጥቶ እንዲህ ያሉ ሽልማቶችን ካስገኘ በኋላ ሊቀጥል ያልቻለበት ምክንያት ምንድነው?**

ዘላለም፡- ቀደም ብዬ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ኬር ኤኸ ኢትዮጵያ በትልቅ አቅም የሚሠራ ነው፡፡ ከፅሁፍ ማዘጋጀትና ከዲዛይን ጀምሮ ለህትመት እስከሚላክበት ድረስ ብዙ ድካምና ጥንቃቄ ይፈልጋል፡፡ ከ40 በላይ ሰዎችም ይሳተፉበታል፡፡ ቀጣዮቹን እስከ ቅፅ 8 ድረስ ያለውን 5 ዕትሞች አጠናቀን ለህትመት ዝግጁ አድርገናል፡፡ በሶስቱ ህትመቶች ግን ከፍተኛ ወጪ በማውጣታችን ከዚህ በላይ የሚያስኬድ የገንዘብ አቅም ሊኖረን አልቻለም፡፡ መጽሔቱ በነፃ የሚታደል እንጂ ለሽያጭ የሚቀርብ ባለመሆኑ ያለስፖንሰር ድጋፍ መቀጠል አስቸጋሪ ነው፡፡ ብታምንም ባታምንም መጽሔቱን ቀረጥ ከፍዬ ከውጪ ለማስገባት መኪና እየሸጥኩ ጭምር ነበር ቀረጥ የምከፍለው፡፡ ለሀገር የሚጠቅምና ለትርፍ የማይሰራ መሆኑ እየታወቀ ከውጪ ታትሞ ሲገባ 43 ከመቶ ታክስ ክፈል ትባላለህ፡፡ መንግሥት ራሱ ሊሰራው የሚገባውን ስራ ሠርተህ ታክስ ክፈል መባል በእውነት ያማል፡፡ በዚህ ሁኔታ በእኛ አቅም መቀጠል ባለመቻላችን ነው የቆመው፡፡

**ግዮን፡- ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ለማሳወቅ እና ችግሩን ለመቅረፍ አልሞከራችሁም?**

ዘላለም፡- ያልሄድንበት፣ ያልገባንበት የመንግሥት መ/ቤት የለም፡፡ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር መ/ቤት የጉዳዩ ዋነኛ ባለድርሻ ነው፡፡ መጽሔቱ የሀገርን በጎ ገጽታ ከማስተዋወቅ ውጪ ሌላ ተልዕኮ የሌለው በመሆኑና ሚ/ር መ/ቤቱ ቢችል ሙሉ ወጪውን መሸፈን ካልቻለም ቀረጡ እንዲነሳ ማድረግ ነበረበት፤ ግን ሊሆን አልቻለም፡፡ ተመላልሰን ተመላልሰን ሲደክመን ተውነው፡፡ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤትን ለማሳመን ብዙ ጣርን፣ ይሄ አልሆን ሲል ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሄደን ጉዳዩን በዝርዝር አስረዳን፡፡ በቃ አልተሳካም፡፡ ይኸው ቆመ፡፡

**ግዮን፡- ቱሪዝም የአገር ኢኮኖሚ ምሰሶ መሆኑና ከዚህ ተጠቃሚ ለመሆን የገፅታ ግንባታ ሥራዎችን መሥራት ወሳኝ መሆኑ በፖሊሲ ደረጃ ተፅፎ በሚገኝበት አገር እንዲህ ያለ ሥራ የሚሰሩትን አለማበረታታት በእውነት ያስቆጫል፡፡**

ዘላለም፡- አለም ሁሉ እየተለወጠ ያለው መልካም ገፅታውን በማስተዋወቅ ነው፡፡ እኔ ኒውዮርክ ከተማን አውቃለሁ፡፡ ኒውዮርክ በፊልም እንደምናያት ውብ እና ፅዱ አይደለችም፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ እንደምናየው ዓይነት ቆሻሻ ቦታዎችም ኒውዮርክ ውስጥ አሉ፡፡ ነገር ግን እነርሱ ምንግዜም በፊልማቸውም፣ በህትመት ውጤቶቻቸውም በቲቪ ፕሮራሞቻቸውም የሚያሣዩት ውብ ገፅታዋን ብቻ ስለሆነ ቱሪስት ከዓለም ዙሪያ ኒውዮርክን ለማየት ይጎርፋል፡፡ እኛ ግን ከኒውዮርክ የተሻለ ሀብት ይዘን ቱሪስቱን ወደዚህ ለመሣብ ተስኖናል፡፡ ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊና እጅግ ውብ የሆነ የብሔር ብሔረሰቦች ስብጥር ያለው ሀብት አለን፡፡ አንድ አገር የእኛን ያክል በታሪክ በባህልና በተፈጥሮ ቅርሶች የታደለ ሊሆን አይችልም፡፡ እኛ ግን እጅግ አስገራሚ የተፈጥሮ አየር ንብረት አለን፡፡ አዲስ አበባ ፀሐይ ሆኖ ምናልባት ከዚህ በመቶ ኪሎ ሜትሮች ቅዝቃዜ እና ዝናብ ሊኖር ይችላል፡፡ ሁለት ወር ሙሉ ፀሐይ የሆነበትን ክልል አልፈህ ወደ ሰሜን ስትሄድ ዜሮ ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ላይ የሚገኝ ቀዝቃዛ አየር ያለበት ቦታ ታገኛለህ፡፡ ይሄ ሁሉ ግን በአንድ በእኛ አገር ብቻ ያለ ነው፡፡ በረዶ ለመስራት ጫፍ የደረሰ የሰሜን ተራራ አካባቢ ባለበት አገር ዳሎልን የመሠለ እሳት ደግሞ ታገኛለህ፤ በዚሁ ወደታች ወደ ባሌ ስትወርድ ደግሞ ብርድ ልብስ ለብሰህ የማይሞቅበት ቅዝቃዜ የአየር ንብረት ውስጥ ትሆናለህ፡፡ ኢትዮጵያ የሌላት ሌላው አለም ያለው ብቸኛ የቱሪስት መዳረሻ ቢኖር የበረዶ መንሸራተቻ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ አለም ላይ ያሉ ሁሉም የቱሪስት መዳረሻ ዓይነቶች እኛ አሉን፡፡ እኛ ብቻችንን ከአለም ጋር የሚያወዳድር ሀብት አለን፡፡ በተፈጥሮ፣ በታሪክ፣ በባህል በሶስቱም የታደልን ነን፡፡ ገፅታችንን ማስተዋወቅ ስላልቻልን ግን ዛሬም የቱሪስት መዳረሻዎቻችን ያለ ጎብኚ ተቀምጠዋል፡፡

ወደ አውሮፓ በሄድኩ ጊዜ የታዘብኩት ነገር በጣም ነው የሚገርመኝ፡፡ አንድ ንጉሣቸው የዛሬ 250 ዓመት የተሻገረበት ድልድይ የቱሪስት መዳረሻ ሆኖ በአስጎብኚያችን ልንጎበኘው ሄደን "ይሄ ድልድይ ከዛሬ 250 ዓመት በፊት ንጉሥ እከሌ የሚባል በዚህ ድልድይ ላይ ተሻግሮ አልፏል" ተብሎ ተነግሮን ተመለስን፡፡ በጣም ነበር የገረመኝ፡፡ እኛ ግን ይሄንን ሁሉ ሀብት ይዘን እናንቀላፋለን፡፡ ጀርመኖች እኮ በሂትለር ዘመን አይሁዶችን ያቃጥሉበት የነበረውን፣ ከነህይወታቸው እሳት ውስጥ ይጨምሩበት የነበረውን አዳራሽ የቱሪስት መዳረሻ አድርገው ገንዘብ ያገኙበታል፡፡ አይሁዶችን እያቃጠሉ ስጋቸውን ለራሳቸው ለአይሁዶቹ ያበሏቸው ነበር ተብሎ በሚነገርህ ቦታ ዘግናኝ ታሪክ ለመስማት የመግቢያ ከፍለህ ትገባለህ፡፡ እኛ ግን ይህንን ሁሉ የታሪክ የባህልና የተፈጥሮ ሀብት ይዘን ከየትኛውም አለም በላይ መጠቀም እየቻልን ከራሳችንም አልፎ ለሌሎች መትረፍ ስንችል በተራ የብሄር አስተሳሰብ ተጠምደን እርስ በርስ መፋጀታችን ያሳዝናል፤ በጣምም ያስቆጫል፡፡

ግዮን፡- በአሁን ሰዓት ምን እየሰራህ ትገኛለህ?

ዘላለም፡- አሁን ከቱሪዝም ኢንዱስትሪው ጎን ለጎን ኬር ኤዝ ኢትዮጵያ የተባለ የቆዳ ውጤቶች ማምረቻና መሸጫ ድርጅቶች ከፍተን በቆዳ ኢንዱስትሪ ኢትዮጵያን እያስተዋወቅን እንገኛለን፡፡ ካዛንቺስ ኢንተርኮንትኔንታል ሆቴል አጠገብ፣ እዚያው አካባቢ ዩኤን ኢሲኤ በር ፊት ለፊት፣ ቦሌ መድኃኔአለም ሞናርክ ሆቴል ፊት ለፊት ገልፍ አዚዝ ህንፃ ስር እንዲሁም ቢሾፍቱ ኩሪፍቱ ወተር ፓርክ ውስጥ መደብሮቻችን ይገኛሉ፡፡ ከቆዳ ምርቶቻችን ጋር እኛን ማግኘት የሚፈልጉ በስልክ ቁጥር 0960846934 መደወል ይችላሉ፡፡

ግዮን፡- ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡

# ስካይ ላይት ሆቴል የኢትዮጵያ ሌላኛው መልክ

ከወ/ሮ ኢሌኒ ተሰማ የኢትዮጵያ ስካይ ላይት ሆቴል ም/ሥራ አስኪያጅ (Dpt GM) ከግዮን ጋዜጠኛ ሙሉጌታ አክሊሉ ጋር በሆቴሉ ዙርያ ያደረጉት ቃለ መጠየቅ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ግዮን፡- የስካይ ላይት ሆቴል ሥራውን መቼ ጀመረ? ምን ያህል የመኝታ ክፍሎችስ አሉት?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- ሆቴሉ ሥራውን የጀመረው በፈረንጆቹ አቆጣጣር ጃንዋሪ 27/2019 ዓ.ም ነው፡፡ ሆቴሉ 373 የመኝታ ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ የፐሬዘደንሻል ክፍልን ጨምሮ 27 የላቁ (ስዊት) ክፍሎች አሉት፡፡ በኢትዮጵያና አዲስ አበባ በርካታ የበዛ "ስዊት" ክፍሎች ያሉት የኢትዮጵያ ስካይ ላይት ሆቴል ነው፡፡ 27ቱ የስዊት ዓይነቶች፤ Presidential Suite, Grand Suite, Executive Suites, Corner Suites, Superior Suites የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡

**ግዮን፡- ጥቂት ስለ "ፕሬዚዲየንሻል ስዊት" ብትነግሪን?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- "ፕሬዘደንሻል ስዊት" የተሰኘው ባለሁለት መኝታ ቤት ሲሆን፤ የመጀመርያው ፕሬዝዳንት፣ ጠ/ሚንስትር የሚያርፍበት ነው፡፡ ሁለተኛው የመንታ ክፍል ደግሞ ተጠባባቂዎቻቸው ወይን ቤተሰቦቻቸው የሚያርፉበት ነው፡፡ ክፍሉ ትልቅ ከመሆኑ አንጻር ራሱን የቻለ ሳሎን፣ ምግብ በመመገቢያ፣ ቢሮ እና ትንሽ ማድቤትን ያካተተ ነው፡፡

**ግዮን፡- ከሌሎች ደረጃቸውን ከጠበቁ ሆቴሎች በምን ይለያል?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- የኢትዮጵያን ስካይ ላይት ሆቴል ከሌሎች ደረጃቸውን ከጠበቁ ሆቴሎች ለየት ያደርገው፣ 373 የመኝታ ክፍሎች ያሉት (2ኛው ማስፋፊያ ሲጠናቀቅ ከ1000 የመኝታ ክፍሎች በላይ ይኖሩታል፡፡ በምስራቅ አፍሪካ ትልቁ የቻይና ሬስቶራንት በኢትዮጵያ በስካይ ላይት ሆቴል አለ፡፡ ደረጃውን የጠበቀ የኢትዮጵያ ባህላዊ የምግብ አዳራሽ ያለው መሆኑ፣ በከተማችን ከሚኒሊየም አዳራሽ ቀጥሎ ትልቁ የስብሰባ አዳራሽም መያዙ፣ የተሟላ የሄልዝ ክለብ (የታይ ማሳጅን ጨምሮ) መስጠታችን፣ ከኤርፖርት በቅርብ ርቀት መገኘቱ፣ የሴፍቲና ሴኪዩሪቲ ሲስተሙ ለየት የሚያደርገውና ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ሆቴሉ ባለቤትነቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በመሆኑ የመለያ ብራንዱ ወይም ሎጎ ላይ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ አርማ አለው፡፡ የሆቴሉ ብራንድ ስም "የኢትዮጵያን ስካይ ላይት ሆቴል ነው፡

**ግዮን፡- የህንፃ ግንባታውን ዲዛይኑ ምን ያህል ጊዜ ፈጀ?**



ወ/ሮ ኢሌኒ፡- በፍጥነት ተገንብቶ 3 ዓመት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ስራ ጀምሯል፡ ፡ ህንፃውን የገነባው IVC የሚባል የቻይና ኮንስትራክሽን ካምፓኒ ነው፡፡ ባሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ትልቁ ሆቴል ሲሆን ፤ የፌዝ 2 ግንባታ ሲጠናቀቅ በአፍሪካ ትልቁ ሆቴል ይሆናል፡፡ 2ኛው ተጨማሪ ሆቴል ከ600 በላይ የሚሆን የእንግዳ ማረፊያ ክፍሎችና ብዛት ያላቸው የምግብና መጠጥ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ የኢትዮጵያ ስካይ ላይት ሆቴል ከሎኬሽኑ፣ ህንጻ ዲዛይኑ፣ የመኝታ ክፍሉ ዲዛይን፣ የኮንፈረንስ አዳራሹ በአጠቃላይ ሆቴሉ ለቢዝነስ ትራቭለሮች እንዲስማማ ሆኖ የተሰራ ነው፡፡ ስካይ ላይት የተባለበት ምክንያት ዋናው ሎቢ ጣርያው መስታወት ነው፡፡ ብርሀን በቀጥታ ይገባል፡፡ በአጠቃላይ የህንጻው ዲዛይን የአውሮፕላን ቅርፅ እንዲሆን የተሰራ ሲሆን የሁለተኛው ፌዝ ሲጠቃለል ሙሉ የአውሮፕላኑን ቅርፅ ያሟላል፡፡ ሃያት ሬጀንሲ አዲስ አበባ "ሲቲ ሆቴል" ነው፡ ፡ ሎኬሽኑ እና አቀማመጡ የሲቲ ሆቴል እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

**ግዮን፡- የስካይ ላይት ውጫዊውና ውስጣዊው ገጽታውን እንዴት ትገልጪዋለሽ?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- መግቢያዎቹ 2 ክንፎች (አቅጣጫዎች) አሉት፡፡ ግቢውን ከመንገድ ላይ ስታየው ሰፋ ያለና የሚያምር አቀማመጥ አለው፡፡ በአካባቢው ጋር ስታልፍም ዓይንን የሚስብ ዕይታ ይፈጥራል፡፡ የቤቱ የውስጠኛው ክፍል ትልቅ ቦታ ላይ አርፏል፡፡ በውጭው ዓለም ብዙ እንዲህ አይታይም፡፡ በውጪው ዓለም እኔ የሰራሁበት ሆቴል ከምድር ጀምረህ ታች ስትሄድ ቢሮ አካባቢ "ኪችን" አለ፡፡ ስካይ ላይት ግን በአካባቢው ስታልፍ ምቾት ይሰማሃል የተጣበበ አይደለም፡፡ በደንብ ታስቦበት የተሰራ ነው፡፡ በውስጡ 7 የሚሆኑ የፉድ አውትሌቶች አሉት፡፡ ትልቁ "ሆልደይ ዳይኒንግ" (Grand Kitchen) ሬስቶራንት አለን፡፡ ኢንተርናሽናል ቡፌ ለደንበኛው ምሣ፣ ቁርስ፣ እራት የሚቀርብበትና ሆቴሉን ተመራጭ አድርጎ ለመዝናናትም ሆነ ለተለያዩ ፕሮግራሞች ለመጠቀም ቡክ አድርጎ ለሚመጡ እንግዶች የሚጠቀሙበት በጣም ትልቁ አዳራሽ ሎቢ ላይ ይገኛል፡፡ "lobby lounge" የሚባል "Coffee Shop" አለን፡፡ መጠጦችንም ያቀርባል፡፡ ሰዎች የሚገናኙበት ቦታ ነው፤ በረንዳም አለው ሻይ ቡና፣ ኬኮችን፣ ቀለል ያሉ ምግቦችንና ሳንዱቾችን በማቅረብ እናገለግላለን፡፡

**ግዮን፡- "VIP lounge" የሚባለውን እንዴት ትገልጪዋለሽ?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- አቀማመጡ (ቪው) በጣም የሚያምርና ዘመናዊ ነው፡፡ የሚሰጠው አገልግሎት የባር ነው፡፡ ይሁንና ምግብን እናቀርባለን፡፡ 2 ፕራይቬት ሩሞች አሏቸው፡ ፡ ለምሣሌ ሰዎች ለስብሰባ ሰወር ያለ ቦታ ከፈለጉ 8ኛ ፎቅ ላይ ሄደው ከሁለቱ በአንዱ ላይ መጠቀም ይችላሉ፡፡

**ግዮን፡- "ሲግኒቸር" (የፊርማ) ሬስቶራንቶች የተሰኙት የሚሰጡት አገልግሎት ምንድን ነው?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- ትልቁ ባህላዊ ጣዕም የኢትዮጵያ ሬስቶራንት ነው፡፡ ዋነኛውና ሲግኒቸር የምግብ አዳራሽ ነው፡፡ እስከ 250 ሰው መያዝ ይችላል፡ ፡ ከጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ ሁልጊዜ ክፍት ነው፡፡ በቅርቡ ተከፍቶ በጣም በሚስብና ማንነታችንን በሚገልፅ መልኩ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ 2ኛው ሲግኒቸር ሬስቶራንት የቻይና ሬስቶራንት ነው፡፡ በጣም ትልቅ ነው፡ ፡ 5ዘመናዊ ፕራይቬት ክፍሎች አሉት፡፡ በቻይና ባህላዊ ጥበብ የተዋበ ነው፡፡ ፊት ለፊቱ የመመገቢያ አዳራሽና ፕራይቬት ሩም አለው፡ ፡ በአዲስ አበባ ትልቁ ዘመናዊ የቻይና ምግብ አዳራሽ ነው፡፡ በምሥራቅ አፍሪካም ትልቁ ነው፡፡ በደንብ ተጠንቶበት የተሰራ ነው፡፡

በግሌ በጣም የምወደው ይህ ክፍል ዙሪያውን መስታወቱ የሚያሳየው (Face) የሚያደርገው ወደ ሄልዝ ክለብ ሚኒ ጎልፍ ወይም ግሪን የሆነ ሜዳ ላይ ያለ ሣሩ ላይ ነው፡፡ የራሱ የመፀዳጃ ቤት አለው፡፡ ጠረጴዛው ስለሚሽከረከር የሚሰራው በሪሞት ነው፡፡ የመንግስት አካል ከቻይና ሲመጣ ብዙ ጊዜ ያንን ክፍል ነው የምንጠቀመው፡፡ ምግቡም ደግሞ ኦርጂናል የቻይና ምግብ ነው ተሰርቶ የሚቀርበው፡



: የቻይና መጠጦችም አሉ። ሄልዝ ክለብ ሪክሬሽን ውስጥ ባር አለን። ጎጆ ናት ገና አልከፈትናትም፣ ግሬን አፕል ሄልዝ ክለቡን ከወር በፊት ነው ተከፍቶ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው። ጁስ ውሃ እና ቀለል ያሉ ግሪል የሆኑ የሳንዱች ምግቦን ለሚጠቀሙ ወደ ጤና የተጠጉ ምግቦችን አዘጋጅተን ለማቅረብ ነው። “ፑል ባር” እንለዋለን። በቅርቡ የምንከፍተው “ብሉ ጃዝ” የተሰኘ አገልግሎት የሚሰጥ የጃዝ ባር አለን። ባሩ ትልቅ ዘመናዊና ተመራጭ የሚሆን ነው። መቀመጫው ሰፊና ለVIP የተለየ ቦታ አለው። ውስጡ በጣም ያምራል፣መድረኩ ሰፊና መብራቱ ልዩ ነው።

**ግዮን፡- ሆቴሉን ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- የኮንፈረንስና የኢቨንት ፋሲሊቲው በአዲስ አበባ 1ኛ ነው። ግራንድ ቦል ሩማችን በመቀመጫ በደንብ የተደራጀ ሆኖ እስከ 2000 እንግዳን ያስተናግዳል። በ‹‹ኮክቴል ጠረጴዛ እናድርገውና በቁም ይሁን›› ብንል እስከ 4000 ሰው ማስተናገድ ይችላል። የ “ቦል ሩም” የምንለው በ5 ይከፋፈላል። በአንድ ጊዜ 5ዓይነት ኢቨንቶች (ፕሮግራሞች) መካሄድ ይችላሉ።

ገና ከመግባታችን በፊት ግራና ቀኙን VIP Holding Room የምንለው እኛ ጋር ብቻ ነው ያለው። ጥሩ በሆነ ምቾትን በሚሰጥ ሶፋ የተዘጋጀና የራሱ የሆነ መፀዳጃ ያለው በመሆኑ ብዙ ጊዜ VIPዎች ከመንግስት ከፍተኛ ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች (በተለይ ከኢትዮጵያ ውስጥ) ሲመጡ ወደ ኤቨንቱ ከመቀላቀላቸው በፊት ሰዓታቸው እስከሚደርስ የሚነጋገሩበት የፕራይቬት 2ክፍሎች አሉን። በተለይ ሚኒስትሮች ሲመጡ ሰዓታቸው እስከሚደርስና እስከሚወጡ የሚጠቀሙበት ክፍል ነው።

ወጣ ስንል “ፎየር” የምንለው እንግዳ መቀበያው በጣም ሰፊ ነው። ብዙ ጊዜ የቡና እረፍት የሚስተናገድበት ነው። እዚያው በቀኝ በኩል ደግሞ 3ዴይ ላይት የምንላቸው የደንበኞች ስብሰባ ክፍሎች አሉን። አጫጭር ለሆነ ስብሰባዎቹ የሚጠቀሙበት ካምፓኒዎች ናቸው። ከ80 — 100 እንግዳ የመቀበል አቅም ያላቸው ክፍሎች አሉት።

**ግዮን፡- ይህ ሆቴል የተከፈተበት ዓላማ ምንድን ነው?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ በጣም ውጤታማ የሆነ አገር ያኮራ ተቋም ነው። እድገቱ፣ ፍጥነቱና እይታው አፍሪካን አልፎ ዓለም አቀፍ ደረጃ የደረሰ አየር መንገድ ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለአገራት ትልቅ አስተዋፅዖ አድርገዋል ከሚባሉት ተቋማት በብዙ መልኩ 1ኛውና ታላቁ ነው። በኢኮኖሚ እድገትም ላይ ሆነ፣ ቱሪስትን በማምጣት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሕዝቡን ለማገልገል፣ ለሌሎች የሥራ ዕድል በመፍጠርና ከ16ሺ በላይ ተቀጣሪ ሠራተኛ ያለው ካምፓኒ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ትልቅ ድርጅት ነው። ብዙም ንግድ ክፍሎች (ቢዝነስ ዩኒትስ) አሉት። የድርጅቱ ማናጅመንቶች ካስቀመጡት ዕቅድ ውስጥ 1ኛው ቱሪዝምና ትራቭል ማስፋፋት ነው። ይህ ዕቅድ ደግሞ ሆቴሉን እንዲገነቡ አድርጓል። ትክክለኛውን የቱሪዝምና ትራቭልን ሰርቪስ ለመስጠት የሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪ መሟላት አለበት። ይህ ደግሞ ሀገሪቷ በቱሪዝምና ትራቭል እንድታድግ ትልቅ ድርሻ አለው።

**ግዮን፡- የህይወት ፍልስፍናሽ ምንድነው?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡ በየቀኑ አዕምሮዬን ሰውን እንዳልጎዳሁ እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ። ሁሌም የማምነው በደግነትና በቸርነት ነው። ባህሪዬ ሆኖ ቂም አልይዝም፣ ይገኘውም ወደ ሌላ ቦታ አልሄድም፣ ትልቅ ትንሽ ሳልል ሁሉንም እኩል ማገልገል እፈልጋለሁ። ወደ አልጋዬ ከመሄዴ በፊት ዛሬ ማንን ጎዳሁ? በሚል ራሴን እጠይቃለሁ። ተናግሬ ምናልባት ያስቀየምኩት የመሰለኝ ካለ ሳልረሳ ማስታወሻ ላይ ፅፌ በነጋታው ሄጄ ስሜው የተቆጣሁበትን ምክንያት አስረዳዋለሁ።

**ግዮን፡- የማትረሺው ገጠመኝ ካለ ?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- ጠዋት 2ሰዓት ተነስቼ እስከ ሌሊቱ 10 ሰዓት ለ4 ወራት ያህል የምሰራበት ጊዜ ነበር። ቁርስ፣ ምሳም ሆነ እራት መብላቴን ረስቼ ልጆች ‹‹አልበላሽም›› ብለው ያስታውሱኝ የነበረውን ውብ ጊዜ በደስታ አስታውሰዋለሁ።

**ግዮን፡- መልዕክት አለሽ?**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- መለወጥ የማንችለው ትልቁ ነገር የመኪና ፓርክ ብዙ የለንም። ግራና ቀኙን በሲስተማቲክ የተሻለ ለማድረግ እየጣርን ነው። በሆቴል ደረጃ ያለማቋረጥ መስራት ያለበት ሰርቪስ ስታንዳርድ ላይ ነው። የ5 ስታር ሰርቪስ የለም እንዳይባል ጠዋት ማታ ስለሚቀረን እንደ አገርና እንደካምፓኒ… ሀበሻም ሆነ የውጭ ዜጋ ቢገባበት ሆቴሉ የተከፈተበት ዓላማ እንግዳን ማስተናገድ የሚለውን የሆቴሉን ህግ በደንብ ሰራተኞቹ ተምረው፣ ብቁ ሆነው፣ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጥ እንፈልጋለን። አዲስ ከመሆናችን አኳያ ብራንድ የምንላቸው ሆቴሎችም ላይ እንኳ ክፍተት አለ። በእኔ በኩል በቲም ማናጅመንቱ ልጆቹን ብቁ ማድረግና ሙያቸውን አክብረው ወደየት መድረስ እንደሚችሉ ማሳየት፣ መምከር፣ ፍላጎታቸውን አውቆ የሚጓዙበትን አቅጣጫ በማሳየት ከታች ጀምሮ ያሉ ሰራተኞችን በግሌ እመክራቸዋለሁ። ወደ 500 ሰራተኞቹንም አውቃቸዋለሁ፣ ክፍተታቸውንና ጥንካሬያቸውንም ስለማውቅ በትሬሊንግና ይበልጥ ውጤታማ የሚሆኑበትን እጠቁማለሁ። ለሀገር ለካንፓኒው ጠቃሚ ይሆናሉ? ወደፊት ከላይ ያለውን አመራር ቦታ ይቀመጣሉ? የሚለውን በማሰብ ግንዛቤን እንዲጨብጡ አደርጋለሁ።

የሆቴል ባለሙያ ተማሪ ነን ለሚሉ በሙሉ ሮኬት ሳይንስ አይደለም። ሆቴል ውስጥ መስራትና ማስተዳደር የሚጠይቀው የሆስፒታሊቲ ፀባይ ሊኖርህ ይገባል። ተቀጥረህ ስትገባ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የምግብ ክፍል ኃላፊ፣ አስተናጋጅ… ብትሆን የምታረገው አጎንብሰህ እንግዳን መቀበል ነው። የኛ አገልግሎት የጽዳት ሰራተኛም አጎንብሶ ቆሻሻ መልቀም አለበት፣ የተበላበትን የተጠጣበትን አጎንብሶ ማፅዳት አለበት። በሆስፒታሊቲ ሁሉንም ሰው አንድ የሚያደርገው እንግዳ መቀበል ነው። ሰውን ማክበርና፣ ሁሌም መሳቅና ትህትና ከሌለህ ከባድ ነው። ሆቴል ውስጥ የሚታደገው በፍላጎትና በፀባይ ጠንክሮ በመስራት ነው።ደግነት፣ ቸርነት፣ በመልካምነት ቅንነት እንክብካቤ ማድረግንና ሥራውን ጠንክሮ መስራትና መውደድን ይጠይቃል። ብዙ ዓመት በአንድ ሆቴል ላይ በተቀጠሩበት ደረጃ ሌላ ሆቴል የሚገቡትን መሽከርከር በመሆኑ ዕድሜያቸው ሲገፋ መድከም ስለሚመጣ የነገ ተረካቢን እናጣለን። ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ዳይሬክተርና በምግብ ዙሪያና በመሣሠሉት ዲሲፒሊን ተጨምሮበት ህልምና ግብ ካለ ወደፊት ከውጭ የሚመጡ ባለሙያዎች በሀገራችን ባለሙያዎች ይተካሉ።

**ግዮን፡- ስለነበረን ቆይታ በግዮን አንባቢና ዝግጅት ክፍል ስም አመሰግናለሁ።**

ወ/ሮ ኢሌኒ፡- እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

ከዝግጅት ክፍሉ፡- የኢትዮጵያ ስካይ ላይት ሆቴልን አስመልክቶ ጥንቅር ስንሰራ ፎቶ ግራፍ በማንሳት የተባበሩንን ፎቶግራፈር ከበደ መክብብን እናመሰግናለን።





# ሱፐር ጎል
## የቋንቋና የኮምፒውተር ት/ቤት

አድራሻችንን ልብ ይበሉ

- እንግሊዘኛ ቋንቋ አቀላጥፈው መናገር ለሚፈልጉ
- French- Chinese-Arabic
- ግዕዝ-AfaanOromo ሌሎችንም የውጭ......
- ወደ ውጭ ሀገር ለመሄድ ላሰቡ፤ IELTS-TOEFL.....
- ለቤት እመቤት እና ለሠራተኞች ቅዳሜና ዕሁድ እንሰጣለን
- Basic and Advanced Computer Courses
- Auto CAD-ms-project Etabs -Adobe Photoshop - Inroad - Peechtree Accounting -Civil3D -IFRS

በቡድን በግል

በዚህም የ 8 ዓመታት ልምድ ያካበትን መሆኑን ተማሪዎቻችን ምስክሮቻችን ናቸው።

ሙሉ እውቅና ያለው

0921 77 65 14/0913 59 66 53

አድራሻ፦ ቁ 1 አምስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ፊት ለፊት

ቁ 2 መገናኛ አደባባይ ሙተባበር ህንፃ 3ኛ ፎቅ ቢ. ቁ. 310

ሱፐር ጎልን ሳይጎበኙ የሚማሩበት አይወስኑ!!